# የሰባኪ መመሪያ

የቅጂ መብት © 2017 by Hands to the Plow, Inc.

አሳታሚ–ሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ

Published by Hands to the Plow, Inc.

P.O. Box 567 • Webster, WI 54893

First printing, 2017

የመጀመሪያ ህትመት 2017

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

አሳታሚው የጽሁፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር

የዚህ እትም የትኛውንም ክፍል በሙሉ ወይም በከፊል ማባዛት

ወይም በሙሉም ሆነ በቁንጽል ማባዛት በኤለክትሮኒክስ

ውጤቶች መቅረጽና ማራባት ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

በዚህ ትርጉም ሥራ በሙሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እና ጥቅሶች የተወሰዱት በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በብርሃንና ሰላም በ1962 ከታተመው የመጽሐፍ ቅዱስ እትም መሆኑን ለአንባቢያን በቅድሚያ ማስታወቅ እንወዳለን።

ትርጉም
ሚያዝያ 2023
በመጋቢ ፍቅሬ ኃይለማሪያም ኖርቻ
ሚዙሪ ሰሜን አሜሪካ

## አስተዋጽዖ አበርካቾች

**ቶም ኬልቢ – የጥናት ማስታወሻዎች**
*ፕሬዚዳንት፣ ሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ ሚኒስትሪስ (Hands to the Plow Ministries, Webster, WI USA)*
**ማርክ ያገር – ዲዛይን እና ሕትመት**
*የፈጠራ ዳይሬክተር (Creative Director, DKY, Inc., Mpls, MN USA)*
**ሎሪ ሰጆኩስት – ምርት**
*የምርት ሥራ አስኪያጅ (Production manager, DKY, Inc., Mpls, MN USA)*

---

ውድ አንባቢ ሆይ፣

ኦሪት ዘፍጥረት 50 ምዕራፎች አሉት። ይሁን እንጂ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ የዘፍጥረት አራት ምዕራፎች ብቻ ለመዳሰስ ተሞክሯል። ለምን እነዚህን አራት ምዕራፎች ብቻ ለመዳሰስ መረጥኩኝ? ምክንያቱም ዘፍጥረት 5–50 ያሉትን ምዕራፎች አስፈላጊ ስላልሆኑ አይደለም፤ ይልቁንም እነዚህ አራት ምዕራፎች ለየት ያለ ጠቀሜታ ስላላቸው ነው እንጂ። በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ የመጀመሪያዎቹ አራት ምዕራፎች ናቸውና! እነዚህ ምዕራፎች ለየት ያሉ ናቸው ምክንያቱም ለአንባቢው እግዚአብሔርን ያስተዋውቃሉና! እነዚህ ምዕራፎች ለየት ያሉ ናቸው ምክንያቱም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ስለተከናወነው ነገር ይናገራሉና። እነዚህ ምዕራፎች ለየት ያሉ ናቸው ምክንያቱም የሰውን ሕይወት ከኃጢአት በፊትና የሰው አመልካከቱና አላማው በኃጢአት ሳይጨልም የነበርውን ሁኔታ ይናግራሉና። እነዚህ ምዕራፎች ለየት ያሉ ናቸው ምክንያቱም የመቤዠትን ታሪክ ጅማሬ ለአንባቢዎች ያስረዳሉና። እነዚህ ምዕራፎች ለየት ያሉ ናቸው ምክንያቱም በብሉይ እና በሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በብዛት ጥቅም ላይ ውሏልና ውይም ተጠቅሰዋልና። እነዚህ ምዕራፎች በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ውሏል። በመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ክፍል አንድ ብቻ (1–41) ያሉትን ማለት ነው፤ ለምሳሌ መዝሙር 1፣ 8፣ 15፣ 19፣ 24፣ 29፣ እና 33 ን ይመልከቱ! እንደዚሁም ደግሞ በነቢያት እነዚህን ምዕራፎች በተደጋጋሚ ጠቅሰዋል። ኢየሱስም እነዚህን ምዕራፎች በተደጋጋሚ ተጠቅሟል። ሐዋሪያትም ቢሆኑ እነዚህን ምዕራፎች ደጋግመው ጠቅሰዋል።

እነዚህን ምዕራፎች በቅርበት ማጥናት የሚያስገኘው ጥቅም ብዙ ነው። የነቢያትን መልዕክት የበለጠ ለመረዳት ያስችላል። እንደዚሁም ደግሞ የመዝሙረዳዊት መልዕክት ጎልቶና በልጽጎ እንድናይ ይረዳናል። ኢየሱስ ስለ ብዙ ጉዳዮች የተናገርው ሐሳብ በቀላሉ ለመረዳት ያስችለናል። እንደዚሁም ደግሞ የጳውሎስ

ነገረ መለኮታዊ ክርክሮች የበለጠ ግልጽ እንዲሆኑ ያደርጋል። በተጨማሪም የራዕይ መጽሕፍ መጨረሻም ጣፋጭ ያደርገዋል። እንግዲህ እነዚህ ምዕራፎች ስለ እግዚአብሔር እውነተኛ ግንዛቤ መሠረት የሚያስጨብጡ ናቸው። በተለይም እግዚአብሔርን በፍጥረቱ ላይ ያለውን ዓላማ ማለትም ሰዎች፣ ጋብቻ፣ ኃጢአት፣ ሰይጣን፣ ፍርድ፣ ቤተክርስቲያንና እንደዚሁም ደግሞ ክርስቶስን ለመረዳት እነዚህ ምዕራፎች መሠረታዊ ናቸው።

ይህ የሰባኪ መመሪያ የሚጀምረው በዘፍጥረት 1–4 ባለው ጽሑፍ እና ማስታዋሻዎች ላይ ነው። እንደዚሁም ደግሞ የሚያበቃው በራዕይ 21፡1–22:5 ባለው ክፍል ጽሑፍና ማስታወሻዎች ነው። እነዚህ የራዕይ ማስታዎሻዎች የተካተቱበት ምክንያት የመጨረሻዎቹ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ከመጀመሪያዎቹ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ጋር በቅርበት የተሳሰሩ በመሆናቸው ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች እና የመጀመሪያዎቹ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ሁሉንም ቅዱሳት መጽሐፍት ከዳርና ዳር አንድ ላይ ደግፈው እንደያዙ እንደ መጽሐፍ መጀመሪያና መጨረሻ ናቸው። አንባቢው እነዚህን ሁለት የዳር ምዕራፎች መረዳት ለተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንና እንደዚሁም ደግሞ በእነዚህ ሁለት የዳር ምዕራፎች መካከል የሚገኙትን – ብዙ ብዙ ምዕራፎችንም ለመረዳት ጠንካራ መሠረት ይሆንለታል። የእነዚህን የመጀመሪያና የመጨራሻ ምዕራፎች የጥልቅ ጥናት ውጤቶች አንዱ ሁሉንም ምዕራፎች ያካተተ የነገረ መለኮት ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እድገት ይሆናል ማለት ነው! እነዚህን ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ማወቅ ሁሉንም ቅዱሳት መጽሐፍት ለማወቅ ለምናደርገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ይኖረዋል።

በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱት ማስታወሻዎች ፍጹም አይደሉም። ነገር ግን ማስታወሻዎቹ ስለሚናገሩት የቅዱሳት መጽሐፍት ግን ፍጹም ናቸው። በእነዚህ ማስታወሻዎች ውስጥ ያሉትን ጉድለቶች በክርስቶስ ያለውን ያልተገደበውን የእግዚአብሔርን ውበት እንዳያዩ እንድይከለክልዎት እጸልያለሁ። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሚያጠኑበት ጊዜ ክርስቶስ ጠንካራ እርዳታ እንዲያደርግሎት እመኛለሁ። ደግሞም እነዚህን እውነቶች በሚያጠኑበት ጊዜ እምነቶዎ እንዲበርታ እንደዚሁም በክርስቶስ የሆነ ደስታ እንዲሞሉ እጽልያለሁ። ከዚህ ባለፈ ደግሞ በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች አማካኝነት ወንጌልን ለማወጅ በሚተጉበት ወቅት የእግዚአብሔር ጠንካር እርዳታ እንዲሆንሎት እመኛለሁ! እነዚህን ቃላቶች በጽሑፍ ብቻ እንዲቀመጡ ሳይሆን እንዲታወጁም ያስፈልጋልና።

ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

ቶም ኬልቢ
ህዳር 11 2017

# ይህን መመሪያ እንዴት መጠቀም እንደሚገባ

1. ይህ መጽሐፍ የዘፍጥረት 1–4 ያለውን ክፍል የሚያካትት ነው። መጽሐፉ ደግሞ በተለያዩ ክፍሎች ተከፋፍሎዋል። ደግሞም በዚህ ጥናት ውስጥ ከእያንዳንዱ ክፍል በፊት ስለክፍሉ አጠቃላይ ዕይታ የሚያስረዳ አጭር መግለጫ ተካቶበታል።

2. ከአጠቃላይ እይታው በኋላ አንባቢው የኦሪት ዘፍጥረት ቃሎችን ያገኛል። ይህም በገጹ **በላይኛው ክፍል** መጀመሪያ ላይ ይገኛል።

3. ይህ መጽሐፍ የጥናት ማስታወሻዎችን ያካተተ ሲሆን እነዚህንም ማስታውሻዎች ከሚጠናው የዘፍጥረት ክፍል የተወሰዱ ቃላቶችን ወይም ጥቅሶችን ወይም ክፍሎችን የሚያመለክት ነው። እነዚህንም የጥናት ማስታወሻዎች ደግሞ የሚገኙት በገጹ **ግርጌ ማስታወሻ** ላይ ነው። እነዚህ የግርጌ ማስታወሻዎች ስብከት አይደሉም። ነገር ግን በስብከት ዝግጅት ወቅት ሰባኪውን የዘፍጥረትን ትርጉም የበለጠ እንዲረዳ እዲያግዙት ታቅደው የተጋጁ ናቸው እንጂ።

4. **በግርጌ ማስታወሻዎች** የሚገኘው ጥናት እያንዳንዱ በቁጥር ተለይቶ ተቀምጧል። ቁጥሮቹም በቀይ ቀለም ተለይተዋል። እነዚህም ቀይ ቁጥሮች ደግሞ **በላይኛው ክፍል** ከሚገኘው ከዘፍጥረት ከተወሰዱት ቃሎች ከተሰየመው ቁጥር ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

5. የጥናት ማስታውሻው አንዳንዴ ከሌላ ቅዱሳት መጽሐፍት የትወሰዱ ጥቅሶች ሊዘረዝር ይችላል። እነዚህም ጥቅሶች የተወሰዱት አንዳንዴ ከብሉይ ኪዳን ሌላ ጊዜ ደግሞ ከአዲስ ኪዳን ሊሆን ይችላል። እነዚህ ከሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተወሰዱት ጥቅሶች ከምናጠናው የኦሪት ዘፍጥረት ክፍል ጋር የተያያዙ በመሆኑ ምክንያት በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል።

# ዘፍጥረት 1–4 ን ሲያነቡ ማስታውስ ያለብዎት 25 ነገሮች

1. **የዘፍጥረት መጀምሪያ ምዕራፎች ልክ እንደሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም የተጻፉት ለተወሰነ ምክንያት እና አንድ የተወሰነ ዓላማ ለማሳካት ነው።** እነዚህ ምዕራፎች ልክ እንደ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎችም እግዚአብሔር በቸርነቱ ለሰዎች የሰጠው ስጦታ ነው። እነዚህ ጽሑፎች ዓላማ አላቸው፡ ልክ እንደሌሎችም ክፍሎች "በክርስቶስ የሚገኘውንም ድነት በእምነት ለማግኘት ጥበበኛ ያደርጎት ዘንድ" በዕቅድ የታሰቡ ናቸው። እነዚህ የአራት ዘፍጥረት ምዕራፎች የእግዚአብሔር እስትንፍስ ያለባቸው ናቸው። ደግሞም እነዚህ መጻሕፍት "የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፤ የእግዚአብሔር መንፍስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምሕርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላልው ምክር ደግሞ ይጠቅማል" (2 ጢሞቴዎስ 3፡14–17 ይመልከቱ)። በሌላ አባባል ደግሞ፤ እነዚህ ምዕራፎች ሰዎች እውነተኛውን እግዚአብሔር እንዲያመልኩ ለመርዳት የታሰቡ ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ ምዕራፎች ስለእያንዳንዱ የፍጥረት ገጽታ ሳይንሳዊ ማብራሪያ ለሰዎች ለማቅረብ የተጻፉ አይደሉም። በድጋሚ መግለጽ የምንፈልገው ግን እነዚህ ምዕራፎች የተጻፍት ከሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ስዎችን ወደ ክርስቶስና በክርስቶስ ወደሚገኘው ብስለት እንዲመሩ ታቅዶ የተጻፉ መሆናቸውን ነው። ስለዚህ እነዚህ ምዕራፎች የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል አንዱ ክፍል ናቸውና ችላ ሊባሉ አይገባም። ይልቁንም እነዚህ ክፍሎች መልዕክታቸው መደመጥ አለበት ለመልዕክቱም መታዘዝም ይገባል ማለት ነው። በተጨማሪም ከእግዚአብሔር የተገኙ በመሆናቸው እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ናቸውና ሊሻሩ አይገባም (ዮሐንስ 10፡35 እና ቲቶ 1፡2 ይመልከቱ)።
2. **በዘፈጥረት ውስጥ ያሉትን የመጀምሪያዎቹ ምዕራፎች ተርት አይደሉም።** በዘፍጥረት ውስጥ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል በጊዜና በታሪክ ውስጥ የተፈጸሙ እውነተኛ ሰዎችን፣ እውነተኛ ቦታዎችን እና እውነተኛ ክስተቶችን የሚመለከት ነው። ይህ በብዙ ምክንያቶች ግልጽ ተደርጓል። ከእነዚህም ውስጥ ሰባቱን እንደሚከተለው ቀርቧል። አንደኛ፣ እነዚህ ቃላት እውነተኛ፣ ቦታዎች እና ክስተቶች እንደሚያመለክቱ ለማመን የመጀመሪያው ምክንያት ሙሴ በተጠቀመበት ዓይነት ቃላቶችና የአጻጻፍ ዘይቤ ውስጥ መካተቱ ነው። ሙሴ አዳምና ሔዋንን ተረት አድርጎ አላቀረባቸውም። ሙሴ ይህን ማደርግ ቢፈልግ ኖሮ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች እንደ ተርት አደርጎ ለማቅረብ ሊጠቀምባቸው የሚችለው መንገዶች ነበሩት። ነገር ግን ሙሴ ይህን አላደረገም። ይልቁንም አዳምና ሔዋንን እንደ እንውነተኛ ሰዎች አቅርቦዋቿል። ይሁን እንጂ አንባቢዎች

የሙሴን ቃላት በዚህ መንገድ ማንበብ ትክክኛ መንገድ መሆኑን ካስገረማቸው ትክክለኛነቱ ለመረዳት የኋለኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች (በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳንም) መመልከት ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ የኋለኞቹ መጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ለአንባቢዎች እነዚህን ምዕራፎች እንዴት ማንበብ እንደሚቻል ምሳሌ ይሰጣሉና። በዘፍጥረት ምዕራፎች ውስጥ ስለ ተጻፉት ክስተቶች የኋለኞቹ ጸሐፊዎች በሚጽፉበት መንገድ በመመስረት፤ ሙሴ እየተናገረ ያለው በጊዜ እና በታሪክ ውስጥ ስለተፈጸሙ እውነተኛ ሰዎች፣ ቦታዎች እና እውነተኛ ክስተቶች እንደሆኑ አድርገው እንደጻፉ ግልጽ ነው። ሁለተኛ፣ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሌሎች መጽሐፍትም አዳም በእርግጥ መኖሩን አስረግጦ ይናገራሉ (1 ዜና መዋዕል 1:1 እና ሆሴዕ 6፡7 ይመልከቱ)። ሦስተኛ፣ እንደዚሁም ደግሞ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም አዳምና ሔዋን በእውነት እንደ ኖሩና ታሪኩም እውነተኛ እንደሆነ ይናግራሉ (ለምሳሌ የጳውሎስ መረዳት በሐዋሪያት ሥራ 17፡26፤ 2 ቆሮንቶስ 11፡3 እና 1 ጢሞቴዎስ 2፡13–15 ይመልከቱ)። አራተኛ፣ ኢየሱስ ራሱ የዘፍጥረት መጀመሪያ ምዕራፎች  ስለተጻፉት ክንውኖች በትክክል እንደተፈጸሙ ተናግሯል (ማቴዎስ 19፡1–12 ይመልከቱ)። በሌላ አገላለጽ እርሱን እንድንመስል የተጠራነው ኢየሱስ ራሱ የአሪት ዘፍጥረት ክንውኖች እውን መሆናቸውን ያምን ነበር። እኛ ደግሞ ኢየሱስን በተግባሩ ብቻ ሳይሆን በእምነትም እርሱን እንድንመስል የተርጋገጠ ነው። አምስተኛ፣ በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ከአዳም ጋር ተነጻጽሯል። እርሱ የመጨረሻው አዳም ተብሎ ተገልጿል (1 ቆሮንቶስ 15፡45)። የፊተኛው አዳም ተረት የሆነ ቢሆን ኖሮ በተፈጥሮ ሰዎች የመጨረሻው አዳም የተባለውንም – ኢየሱስ ጥያቄ ውስጥ ለመክተት ይገደዱ ነበር። ስለዚህ የመጀምሪያው አዳም ባይኖርና ሥራውንም በትክክል ያለተከሰተ እና ለዘለቄታውም ችግር የሚፈጥር ቢሆን ኖሮ ታዲያ እንዴት በመጨረሻው አዳም በኢየሱስ በተከናወኑ ድርጊቶች መተማመንና ማመን እንችል ነበር (ሮሜ 5:12–21 እና 1 ቆሮንቶስ 15፡45–49 ይመልከቱ)? ነገር ግን በተቃራኒው በመጨረሻው አዳም (ኢየሱስ) የተከናወነው እውነታ የመጀመሪያውን አዳም (አዳም) እውነተኛነት እንድንቀበል ያበረታታናል። ስድስተኛ፣ ኢየሱስ በአካል ከአዳም ጋር እንደሚመሳሰል ተናግሯል (ሉቃስ 3፡38 ይመልከቱ)። አዳም እውነተኛ ሰው ካልሆነ እንዴት ኢየሱስ እውነተኛ ሰው እንደሆነ እምነት ሊኖረን ይችላል? እንደዚሁም ደግሞ ኢየሱስ እውነተኛ ሰው ካልሆነ ስለመዳናችን እርግጠኞች መሆን አንችልም ምክንያቱም መዳናችን ከኢየሱስ እውነተኛ ሰው መሆን ጋር የተቆራኘ ነውና። በተቃራኒው ግን ሰዎች የኢየሱስ ሰው መሆን እንደ ማይጠራጠሩ ሁሉ የኢየሱስ ቅድመ አያቱንም የአዳምን እውነታነት መጠራጠር የለብንም። ሰባተኛ፣ እግዚአብሔር ራሱ ሰማይንና ምድርን እንደ ፈጠረ

ደጋግሞ ተናግሯል (ኢሳ 45፡18 ይመልከቱ)። ስለዚህ በእግዚአብሔር ካመንን በቅዱስ ቃሉ በተገለጸው መሰረት ሰማይና ምድርን እንደፈጠረ ደግሞ እናምናለን።

3. **በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *በአሁኑ ጊዜ* ሕዝቡን ማዳን እንደሚችል በእግዚአብሔር ኃይል እምነት የሚኖረን በእግዚአብሔር ፍጥረት *ባለፉት ጊዜያት* ከተከናወኑት ነገሮች ሁሉ ጋር የተያያዘ ነው።** እኛ እንደ እግዚአብሔር ሰዎች እውነቱን ማወቅ እና ማመን ያለብን ዋናው ምክንያት እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ሲፈጥር በሩቅ ያደረገው ነገር ዛሬ ያድነን ዘንድ እግዚአብሔርን እየጥራነው ነው። እግዚአብሔር በአሁኑ ወቅትም ልንታመንበት እንችላለን ምክንያቱም እርሱ ባለፉት ዘመናት ድንቅ ሥራዎችን የሠራ ያው አምላክ ነውና። በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ይህን ያደረጉ ምሳሌ የሚሆኑን ብዙ ሰዎች አሉ። ለምሳሌ የመዝሙረ ዳዊት የአሳፍ ቃላት በመዝሙር 74፡9–17 የተጻፈውን ይመልከቱ። አሳፍ በብዙ መከራ ያለፈ ቢመስልም ነገር ግን እግዚአብሔር ዓለምን በመፍጥር ባደረጋቸው ተአምራቶች አሳፍ እግዚአብሔር ንጉሥ እንደሆነና ሕዝቡንም የማዳን ኃይል እንዳለው በማመን ይናገራል። አሁን ያለው የአሳፍ ተስፋ የተመሰረተው በቀደሙት ዘማናት በተከናወኑ የእግዚአብሔር ታላላቅ ሥራዎች ላይ ነው። በተጨማሪም መዝሙር 121፡2 እና 124፡8 ን ይመልከቱ።

4. **እግዚአብሔር አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በመፍጠር ወደፊት በሚፈጽመው ሥራ ላይ ሊኖረን የሚችለው እምነት እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ባለፉት ዘመናት እንደፈጠረ ከማመናችን ጋር የተያያዘ ነው።** ክርስቲያኖች አንድ ቀን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ደግሞ ይፈጥራል ብለው እግዚአብሔርን ይታመናሉ። ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ወደፊት ይህን እንደሚያደርግ እምነት እንዲኖራቸው ደግሞ የሚያደርጉበት ምክንያት ቀደም ሲል እግዚአብሔር ይህን ስላደረገ ነው! ስለዚህ በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ ምዕራፍ 21–22 በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር ማመን ማለት፤ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1–2 ውስጥ በእግዚአብሔር የመጀመሪያ የፍጥረት ሥራ ከማመን ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው።

5. **እግዚአብሔር ሰማይና ምድር በመፍጠር የፈጸማቸው ተግባራት ከሌሎች አምላክ ተብለው ከሚጠሩት ሁሉ ለይተውታል።** የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው። ሌሎች አማልክት ሊታዩ የሚችሉት እንደ አማልክት (ማለትም እንደ ጣኦት) ነው፤ ወይም ምንም የማይታዩ ናቸው (ማለትም ሰዎች እነዚህን አማልክት ያመልካሉ ነገር ግን ከእነርሱ ጋር ምንም ዓይነት መመሳሰል የላቸውም) ደግሞም ምንም ነገር የሰሩ አይደሉምና። ይልቁንም አማልክቶቹ ራሳቸው የተሰሩት በሰዎች ነውና። ለምሳሌ ኢሳይያስ 40፡12–26 ይመልከቱ።

6. **በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔርን ማመስገን ባለፈው እርሱ ከሰራው የፍጥረት ሥራ ጋር የተያያዘ ነው።**

ሰዎች የተጠሩት የእግዚአብሔርን ድንቅ የፍጥረት ሥራዎች ላይ እንዲያሰላስሉ እና ስለጥበቡ፣ ታላቅነቱና ኃይሉ እርሱን እንዲያመሰግኑ ነው። ለምሳሌ መዝሙር 104ን ይመልከቱ።

7. **ኦሪት ዘፍጥረት የተጻፈው በሙሴ ነው።** የአዲስ ኪዳን ደራሲዎች ግልጽ ያደረጉት ነገር ቢኖር በኦሪት ዘፍጥረት፣ በኦሪት ዘፀአት፣ በኦሪት ዘሌዋውያን፣ በኦሪት ዘኍልቊ እና በኦሪት ዘዳግም የሚገኙትን ቃላት ጸሐፊ ሙሴ መሆኑን ነው ( ማርቆስ 12፡19፤ ሉቃስ 20፡28፤ ዮሐንስ 1፡45፣ 5፡ 46 እና ሮሜ 10፡5 ይመልከቱ)፤ እንደዚሁም ደግሞ ሙሴ መዝሙር 90 ናንም ጽፏል። ሙሴ ጠንቃቃ የታሪክ ምሁር ነው። በእነዚህ የዘፍጥረት የመጀመሪያ ምዕራፎች ውስጥ ስለ ሰማይና ምድር አፈጣጠር፣ የኃጢአት ጅማሬ፣ የክርስቶስ መምጣት የተስፋ ቃል እና ከእግዚአብሔር መልካም ሥፍራ ውጪ የሆነ ሕይወት ጅማሬ ገልጿል። ሙሴ ግን የታሪክ ምሁር ብቻ አይደለም። ከጽሁፎቹ በመመሥረት እሱ የእምነት ሰው እንደሆነም ግልጽ ነው (የሙሴ ቃል በመዝሙር 90 ይመልከቱ)። ሙሴ ምንም እንኳን ከክርስቶስ መምጣት በፊት የኖረ ቢሆንም ስለክርስቶስ መምጣት ግን ያውቅ እንደነበር ማወቅ አስፈላጊ ነው (ለምሳሌ ዘዳግም 18፡15–19፣ ዮሐንስ 1፡45 እና 5፡46 ይመልከቱ)። ሙሴ ለክርስቶስ ጥልቅ ፍቅር ነበረው፤ እምነቱም ክርስቶስ ላይ ነበር፤ የጻፈውም ትኩረትን ወደ ክርስቶስ ለመሳብ ነው (የሐዋሪያት ሥራ 3፡18–26፤ ዕብራውያን 11፡26–27 እና 1 ጴጥሮስ 1፡10–12 ይመልከቱ)። ሙሴ ቃሎቹን ሲጽፍ እንደሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እሱም የነገረ መለኮታዊ ዓላማ ነበረው። የሱ ዓላማ የሰማያትንና የምድርን አፈጣጠር መዘርዘር (ዘፍጥረት 1–2) ወይም ደግሞ ከአብርሃም በፊት ስለነበረው ምድር (ዘፍጥረት 1–11) ጉዳይ መዘርዘር ብቻ አልነበረም። የሙሴ ግብ ግን ሰዎች በክርስቶስ ላይ እምነታቸውን እንዲያሳርፉ መምራት ላይ ነበር።

አዲስ ኪዳን እንደ ሚመሰክረውም ሙሴ በግብፅ ከሚገኘው ባለጠግነት ሁሉ ይልቅ በክርስቶስ የሚገኘውን የሚበልጥ በልጽግና እንደሆነ ይቆጥር ነበር (ዕብራውያን 11፡26–27 ይመልከቱ)። ሙሴ ለክርስቶስ ከነበረው ፍቅር የተነሳ የመከራን ሕይወት መረጠ! አንባቢ ሁልግዜ ሊያስታውሰው የሚገባ ነገር ቢኖር የሙሴ ዓላማ እንዲያው በቀላሉ ስለሰማይና ምድር የሚመለከት ታሪክ ለሰዎች መረጃ ለመስጠር ማስተማር ወይም ደግሞ ስለ አብርሃም ወይም ስለ ይስሐቅ ወይም ስለ እሥራኤል ሕዝብ ወይም ስለ ማድሪያው ድንኳን እውነታዎች መተንተን አልነበርም። ነገር ግን ሙሴ አንባቢዎቹ የሱን ጽሑፎች በጥንቃቄ እንዲመለከቱት እና ካነበቡትና ከሰሙትም ነገር የተነሳ እምነታቸውን በክርስቶስ ላይ እንዲያደርጉ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ኢየሱስ እንደ ተናግረውም፤ በሙሴ ጽሑፎች የሚያምን አንድ ሰው በእርግጥ በክርስቶስ እምነት እንዲኖረው ይመራዋል ምክንያቱም ሙሴ የጻፈው ስለክርስቶስ ነውና (ዮሐንስ 5፡45–47

ይመልከቱ)። ጥንቁቅ አንባቢ ሙሴ ትምህርቱን እንዴት እንዳዘጋጀ ይመረምራል ደግሞም ይህንንም ግብ ለማሳካት ሙሴ የጻፋቸውን ቃላት በጥንቃቄ እንዳዘጋጀም ይረዳል።

8. **የኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ብቻውን እንዲነበብ የታቀደ አይደለም ይልቁንስ ከዘፍጥረት ቀጥለው ከሚገኙት አራቱ መጽሐፍት ጋር አብሮ የሚነበብ ነው እንጂ።** በሌላ አጋላለጽ፤ በሙሴ የተጻፉት አምስቱ የተለያዩ መጻሕፍት ( ኦሪት ዘፍጥረት፣ኦሪት ዘፀአት፣ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኋልቁ እና ኦሪት ዘዳግም) በእውነቱ እንደ አንድ መጽሐፍ ናቸው፤ ስለዚህም አንድ ትልቅ መጽሐፍ ይወጣቸዋል ማለት ነው። ሙሴ የዚህን አንድ ትልቅ መጽሐፍ አምስቱን ክፍሎች ሲያደራጅ በአይምሮው የነበርው አንድ አላማ ብቻ ነው። አሁንም ያ ዓላማ እምነታቸው በክርስቶስ ላይ እንዲያደርጉ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ መምራት ነው (ሉቃስ 24፡25–27፣ 24፡44–49፤ ዮሐንስ 5፡ 45–47፤ የሐዋሪያት ሥራ 3፡18–24 እና 1 ጴጥሮስ 1፡10–12 ይመልከቱ)። ሙሴ ይህን ዓላማ በዚህ አምስት የተለያዩ ክፍሎች ባሉት አንድ ትልቅ መጽሐፍ ውስጥ እንዴት እንደ ሚፈጽምው መረዳት ደግሞ የሰባኪ ደስታና ግዴታም ነው።

9. **ልክ ዘፍጥረት የትልቅ መጽሐፍ የመጀምሪያው ክፍል እንደሆነ ሁሉ አዳንድ ጊዜ (የአምስቱ መጻሕት ክፍሎች ደግሞ "የሙሴ መጽሐፍ") በመባል ይታወቃሉ፤ ይህም አምስት ክፍሎች ያሉት የሙሴ መጽሐፍ (ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ኦሪት ዘዳግም) ማለት ነው (የጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ) የመጀምሪያ ክፍል ነው።** ደግሞም ሁሉንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአንድነት የሚስማሙ ናቸው። ለምሳሌ እንዴት የነህሚያን ተግባራት በሙሴ መጽሐፍት በተገለጸው መሠረት እንደሆነ (ነህሚያ 1፡8–11 ይመልከቱ)። ነህሚያ ከሙሴ የተለየ ታሪክ እየተናገረ አይደለም። በሙሴ መጽሐፍ የተጀመረውን በመቀጠል ነው የሚናገረው። በመሆኑም የዚህን ሁሉ ክፍሎች ታሪክ እንዴት እንደ ተቀናጀ ማወቅ እና ለሰዎችም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገረውን እንዲያስታውሱ በማሳሰብ መስበክ የሰባኪ ደስታና ግዴታም ነው።

10. **በኦሪት ዘፍጥረት 1–3 ያለው ክፍል ከራዕይ መጽሐፍ መጨረሻ ምዕራፎች ጋር ተመሳሳይ ነው።** በብዙ መንገድ የዘፍጥረት መጽሐፍና እና የራዕይ መጸሐፍ ተመሳሳይ ናቸው። በሌላ መልኩ ደግሞ በጣም የተለያዩ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚነገረው ታሪክ የሚጀምረው ሰማያትንና ምድር ሲፈጠሩ ነው (ዘፍጥረት 1–2 ይመልከቱ)። ታሪኩ የሚያበቃው ደግሞ አዲስ ሰማያትንና አዲስ ምድር ሲፈጠሩ ነው (ራዕይ 21–22 ይመልከቱ)። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚጀምረው ሰዎች በአንዲት ትንሽ የኤድን ገነት ውስጥ አንድ ዋንኛ ወንዝና በውስጡም የሕይወት ዛፍ ባለበት ሲኖሩ ነው። ታሪኩ የሚያበቃው ደግሞ ሰዎች በጣም ትልቅ በሆነ የኤድን ገነት ዓይነት ከተማ ወስጥ ትልቅ ወንዝና በወንዙም ዳርቻ የሕይወት ዛፍ ተተክሎ ሲኖሩ ነው። ታሪኩ የሚጀምረው

ሰዎች ከሕይወት ዛፍ እንዳይበሉ እንደ ተከለከሉ በማሳየት ሲሆን፤ የሚያበቃው ደግሞ ሰዎች ከሕይወት ዛፍ እንዲበሉ ተፈቅዶላቸው ነው። በዘፍጥረት 2 የመጀምሪያው ጋብቻ በዓል ያሳያል። በራዕይ 21 ደግሞ የክርስቶስ ጋብቻ ከሙሽራዋ ከቤተክርስቲያን ጋር የሚከበር በዓል መሆኑን ያስረዳል። ኦሪት ዘፍጥረት የሚጀምረው በአዳም ሊፈረድበት በተገባው ነገር ግን እንዲያመልጥ በተፈቀደለት እባብ ነው። የራዕይ መጽሐፍ የሚያበቃው ግን እባቡ በኋለኛው አዳም (ኢየሱስ) ተፈርዶበትና ወደ ዘላለማዊ እስር ቤት ሲወረወር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ላይ የኤድን ገነት ቦታው ትንሽ ነው፤ በውስጡም ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ። በመጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ ግን የኤድን ገነት ቦታው ሰፊና ደግሞም ከሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች በተወጣጡ ሰዎች የተሞላ ነው! ስለዚህ በዚህ ትልቅ መጽሐፍ ውስጥ (ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ራዕይ) ድረስ የተጻፈውን ታሪክ መርምሮ መረዳት የሰባኪው ደስታና ግዴታም ነው።

11. **ደራሲው አንባቢዎቹ እንዲገነዘቡት የሚፈልገው ስለእሱ የሚጽፈው እግዚአብሔር ብቻውን አምላክ መሆኑን ነው።** በሙሴ ዘመን የኖሩ ሰዎች ብዙ አማልክቶችን ያመልኩ ነበር። ሆኖም በእነዚህ ምዕራፎች ግን ሙሴ የሚናገረው ስለ አንድ አምላክ ብቻ ነው። በዘፍጥረት 1–4 ላይ የተገለጸው እግዚአብሔር ግን ውስን ኃይል ያለው የሆነ ትንሽ የአንድ አካባቢ አምላክ አይደለም። እሱ የበቆሎ አምላክ፣ ወይም የመራባት አምላክ፣ ወይም የማዕበል አምላክ ብቻ አይደለም። ነገር ግን እርሱ የእነዚህ ሁሉና የሌሎችም ነገሮች አምላክ ነው። እግዚአብሔር የሁሉም ነገር አምላክ ነው። ነገር ግን እርሱ እግዚአብሔር የአንድ ትንሽ ሀገር ወይም በአንድ በተወሰነ በሰዎች ቡድን ላይ ብቻ አምላክ አይደለም። እግዚአብሔር በሁሉም ነገር ላይ አምላክ ነው! ሙሴ ስለእርሱ የሚጽፍለት እግዚአብሔር ግን ሁሉን የፈጥረና ሁሉንም የሚቆጣጣር ፈጣሪ አምላክ ነው። የዚህ ዘመን ሰዎች በጥንት ዘመን ከነበሩት ስዎች ይልቅ የሰለጠኑ መስሎ ስለሚታያቸው ሌሎችን አማልክት እንደ ማያመልኩ ሊናግሩ ይችላሉ፤ ነገር ግን ነገሩ እንደዛ አይደለም። ምንም እንኳን ሰዎች ጣዖታትን ባያመልኩም ቅሉ አሁንም ሌሎች ብዙ ነገሮችን (ማለትም ገንዘብ፣ ወሲብ፣ ስልጣን እና ሀብት) የመሳሳሉትን ያመልካሉ። እነዚህ የተዘረዘሩት ነገሮች ምንም እንኳን በሚወዱዋቸው ሰዎች ዘንድ ጣዖት ተብሎው ባይጠሩም ነገር ግን በሕይወታቸው ውስጥ እንደ ጣዖት የሆነ ገዢ ኃይል ናቸው። የተፈጠርነው እንድናመልክ ነው። እውነተኛውን አምላክ የማናመልክ ከሆነ ደግሞ ሌሎችን አማልክት እናመልካለን ማለት ነው። ስለዚህ ታማኝ ሰባኪ ሰዎች እውነተኛ ባልሆኑና ማዳን በምይችሉ አማልክት ላይ ያላቸውን እምነት እንዲተው ጥሪ ያደርጋል ደግሞም ሰዎች በዘፍጥረት ላይ በተገለጸው አንድ አምላክ ላይ እምነት እንዲኖራቸውም ጥሪ ያደርጋል።

12. ዘፍጥረት የሚጀምረው እግዚአብሔር ሁሉንም ቦታዎችን፣ ሁሉንም ነገሮች እና ሰዎችን ሁሉ በመፍጠር ነው። ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከአንድ ሀገር የሆነ ለተወሰነ ብሔረሰብ አምላክ ብቻ አላመሆኑን ያሳያል። ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ማምለክና ማመስገን አለባቸው ምክንያቱም ፈጣሪያቸው ነውና። በተለይም ከእሥራኤል ሕዝብ ታሪክ በፊት የሁሉም ሰዎች የአፈጣጠር ታሪክ መምጣቱ ጠቃሚ ነገር ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር በሥጋ ዝምድና የተገናኙ ሰዎች አምላክ ብቻ አይደለም። በዘፍጥረት የተገለጸው አምላክ በሁሉም ቦታ በሰዎች ሁሉ ሊመለክ የተገባው ነው። በምድር ላይ ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ውጭ የሆነ ሥፍራ የለም። ስለዚህ በምድር ላይ የሚኖር የሰው ዘር በሙሉ እርሱን ማምለክ ይኖርበታል። ከዚህ ባሻገር በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ይህንን እውነተኛ አምላክ ማምለካቸውና መታዘዛቸውን መሠረት ያደረገ ፍርድ ይሰጣል (የሐዋሪያት ሥራ 17፡24–31 ይመልከቱ)።
13. በዘፍጥረት 1 እና 2 ላይ የተነገሩት ነገሮች የተፈጸሙት ኃጢአት ወደ ዓለም ከመግባቱ በፊት ነው። ሆኖም ሙሴ ደግሞ የጻፈው ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባ በኋላ ለሚኖሩ ሰዎች ነው። ከኢየሱስ በስተቀር የሙሴ አንባቢዎች አንዳቸውም ቢሆን ከኃጢአት ውጪ መሆን ምን እንደሚመስል አያውቁም። የሙሴ የመጀመሪያ አድማጮች በምድረ በዳ ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚጓዙ ሰዎች ነበሩ። በመሆኑም በኤደን ውስጥ በነበርው የአትክልት ሥፍራ ውስጥ ምን ዓይነት ሕይወት ይኖር እንደነበር ማሰብ ብቻ ችለው ነበር ይሆናል። እንግዲህ ዛሬም የሙሴ አንባቢዎች እንደሙሴ የመጀመሪያ ተደራሲያን ናቸው። አንባቢዎች ዛሬ የሚኖሩት ከገነት አትክልት ሥፍራ ውጭ በሆነ ኤደን ውስጥ ነው። ስለዚህ ሁሉንም የሙሴ አንባቢዎች (ያለፉት እና የአሁን) ቢሆን ከአትክልት ቦታው ውጭ እየኖሩ ነው እና በአዳም ኃጢአት ምክንያትም ኃጢአተኞች በመሆናቸው (ሮሜ 5፡ 12 ይመልከቱ) ብዙ የኃጢአት ጫና፣ ሕመም፣ ችግርና ስቃይ አሳልፈዋል።
14. ግጥሞች የዘፍጥረት እና የሙሴ መጽሐፍቶች ዋና ባሕሪያት ናቸው። ግጥም ከተራ ትረካ የሚለይበት ምክንያት ቃላቶችና የቃላቶች ዘይቤ በልዩ መንገድ ስለሚያጣምር ነው። ግጥም ማለት በዙሪያው ካለው ጽሑፍ ጎልቶ የሚወጣና የማይረሳ መሆን አለበጥ። በመጀመሪያዎቹ አራት ምዕራፎች ብቻ፣ በዘጥረት 1፡27፣ 2፡4፣ 2፡23፣ 3፡14–19 እና 4: 23–24 ላይ ግጥሞች ይገኛሉ። ስለዚህ ሰባኪዎችም ይሁኑ አስተማሪዎች ግጥሞችን እንዴት እንደሚተረጉሙ፣ በስብከታቸውና በትምህርታቸው ውስጥ እንዴት እንድሚያካትቱ መገንዘብ አለባቸው። ግጥሞች ችላ ሊባሉ አይገባም። ምክንያቱም ግጥሞች በራሳቸው ልዩ መንገድ የጽሑፉን ዋና ዋና ሐሳቦች ማጠቃለያ ስለሚሰጡና የአንድ ውስን ንባብ ክፍል ዋና ጭብጥ ስለሚያሳዩም ነው። ከዚህም ባሻገር፣ ክርስቶስንና የወንጌል መልዕክት ለማወጅ ብዙ ጊዜ ጠቃሚ ምንባቦች ናቸው። ስለዚህ በግጥም

ውስጥ ያለውን መልዕክት መረዳትና መልዕክቱንም ማወጅ የሰባኪው ግዴታና ኃላፊነት ሊሆን ይገባል።

15. **የአንባቢው ትኩረት በጽሑፍ በተሰጠን ቃል ላይ መሆን አለበት።** በዘፍጥረት 1–4 ላይ ሙሴ የዘገበውን ነገር የሚያረጋግጡ በሕይወት ያሉ የዓይን እማኞች ማግኘት አይቻልም። በሙሴ ዘመንም ቢሆን ማንም በሕይወት አልነበረም። ስለዚህ በዘፍጥረት 1 ላይ የተጻፉትን ክስተቶች የተመለከተ ማንም የለም። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተገለጹትን ነገሮች በፊልም ተቀርጾም አልተሰጠንም። እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ሲፈጥር የተከናወነውን ነገር የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ የለንም። የተሰጠን *ቃል* ብቻ ነው። ስለዚህ ለተሰጠን ቃል እንደ የከበረ የእግዚአብሔር ስጦታ አድርገን በመመልከት መጠንቀቅ አለብን። ከቃሉ የተሻለ እግዚአብሔር ሊሰጠን የተገባ ነገር ቢኖር ኖሮ እንደሚሰጠን እርግጠኞች መሆን እንችላለን። ነገር ግን እግዚአብሒር በቸርነቱ በመጽሐፍ መልክ ቃሉን ሊሰጠን ወደደ። ቃሉ የተጻፈው ደግሞ *እምነት* እንዲሆንልን ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ችላ ማለት እና ከቃሉ ጀርባ የተከናውኑትን ነገሮች እንደገና ለመፍጠር መሞከር ፈታኝ ነገር ነው። ሆኖም ግን እንዲህ ዓይነቱ ሂደት የተሰጠንም ነገር አይደለም። መረዳት ያለብን የእግዚአብሔር ቃል እንደተሰጠን ነው። እግዚአብሔር በሙሴ በኩል የተናገረውን ልንታመን ይገባናል። ጥንቁቅ ሰባኪ በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል የሰዎችን ትኩረት በመሳብ እየተሰበከ ባለው እግዚአብሔር ላይ ሰዎች ደግሞ እምነት እንዲኖራቸው ጥሪ ያደርጋል።

16. **የሙሴ መጽሐፍ (ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም) እግዚአብሔር ከመፍጥር ያለፈ ነገርን እንደሚሠራ ይገልጻል።** አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እግዚአብሔር የፈጠረውን ደግሞ ማጥፋት ይችላል። ራሱ የፈጠረውን መልሶ ሲያጠፉ በዘፍጥረት 6–8 (በኖኅ ዘመን የጥፋት ውሃ)፣ በዘፍጥረት 19 (በአብርሃምና በሎጥ ዘመን የሰዶምና የገሞራ ጥፋት) እና በዘፀአት 2–12 (በሙሴ ዘመን የግብፅ ጥፋት) መመልከት ይቻላል። እንደ እውነቱ ከሆነ በግብፅ ውስጥ የወረደው መቅሰፍት ለአንባቢያን በዘፍጥረት 1 ላይ ስለተከናወነው የመፍጠርን ተቃራኒው ምን እንደሚመስል ለማስታውሰ የተደረገ ይመስላል። ሁሉም ነገር እንዲወድም በማድረግ ወደ ትርምስ እንደመመለስ ያህል ነበር የሆነው። እግዚአብሔር ፍጥረቱን መልሶ እንደሚያጥፋ የሚገልጸው እያንዳንዱ ዘገባ በክርስቶስ ዳግም ምጻዓት ወቅት ስለሚኖረው የሰማያትንና የምድር ጥፋት ትንሽ ስዕል ነው (2 ጴጥሮስ 3፡1–13 ይመልከቱ)። እነዚህ ጥቃቅን የፍጥረት ጥፋቶች ሰዎች ከኃጢያታቸው ንስሃ እንዲገቡ እና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ወደ እግዚአብሔር ዞር እንዲሉ የሚያደርጉ ናቸው።

17. **የማደሪያው ድንኳን በኤደን ውስጥ የሚገኝ ትንሽ የአትክልት ቦታ ሥሪት ይመስላል።** ምንም እንኳን ሰዎች ከመጀምሪያው ከኤደን ገነት ቢባረሩም፤ በእግዚአብሔር ቸርነት እግዚአብሔርና

ሕዝቡ አብረው የሚኖሩበትን አዲስ ቦታ እንዲገነቡ የእሥራኤልን ሕዝብ ጠራቸው። ይህም አዲስ "ኤደን" የማደሪያው ድንኳን ተብሎ ተጠራ (ዘፀአት 25–31 ይመልከቱ)። በድንኳኑ ውስጥ የተገኙትን ምስሎች መሠረት በማድረግ (ማለትም ፍራፍሬ፣ ዛፎች፣እንስሳት፣ የከበሩ ድንጋዮችና እንቁዎች እና ኪሩቤልም) የመሳሰሉትን ስንመለከት ደግሞ የማደሪያው ድንኳን በኤደን የነበረውን የአትክልት ስፍራ ምትክ እንዲሆን ታቅዶ የተሠራ ይመስላል። የመደሪያው ድንኳን እግዚአብሔርና ሰዎች በፍጹም ተስማምተው የሚኖሩበት ቦታ ሆነ። በሌላ በኩል ደግሞ እርግጥ ነው የማደሪያው ድንኳን የኤደን የአትክልት ስፍራ ፍጹም ነጸብራቅ ነበር ለማለት አያስደፍርም። ለምሳሌ በኃጢያት ምክምንያት የማደሪያው ድንኳን ማን መቼ ወደ እሱ እንደሚገባ ብዙ ገደቦች ነበሩበት። ስለዚህ የማድሪያው ድንኳን ቢኖርም፣ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አሁንም የሚከለክል መሰናክል ነበር። ይህም መሰናክል በመጋረጃ ተመስሎ ነበር። መጋረጃው ደግሞ በጨርቁ ላይ የተሰራ የኪሩቤል ምስል ነበረበት። ይህም አዳምና ሔዋን ወደ አትክልት ስፍራው እንዳይመለሱና ከሕይወት ዛፍም እንዳይበሉ ወደ ኤደን በሚወስደው መንገድ ላይ የተቀመጠውን ኪሩቤል ለሰዎች ለማስታወስ ይመስላል (ዘፍጥረት 3፡24 ይመልከቱ)። በመቸረሻም የማደሪያው ድንኳን ይበልጥ ቋሚ በሆነ መዋቅር ማለትም በቤተ መቅደሱ ተተካ። ቤተ መቅደሱም የታሰበው በኤደን የነበረውን የአትክልት ቦታ ሰዎችን ለማስታውስ ነው። ይህም ቤተ መቅደስ ልክ እንደ ማደሪያው ድንኳንም ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደው መንገድ አሁንም ለስዎች ክፍት እንዳልሆነ የሚያሳይ መጋረጃን አካትቷል። በመቸረሻም በኢየሩሳሌም ይገኝ የነበረውንም ቤተ መቅደስ ፈርሷል። ይህም መቅደስ በሌላ ተተክቷልና። ያ ቤተ መቅደስም ልክ በኤደን ውስጥ እንደ ነበርው የአትክልት ቦታ ይመስል ነበር። ነገር ግን ወደ ሕይወት ዛፍ የሚውስደው መንገድ ለሰዎች ገና እንዳልተከፈተ የሚያሳይ መጋረጃ ያካተተ ነበር። በመጨረሻውም ይህም ቤተ መቅደስ የመጨረሻ በሆነው ቤተ መቅደስ ተተካ – እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐንስ 2፡18–22 ይመልከቱ)። እርሱ እግዚአብሔርና ሰዎች ፍጹም በሆነ አንድነት አብረው የሚኖሩበት "ቦታ" ነው። ኢየሱስ ሲሞት በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበረውን መጋረጃ ከላይ ወደታች መቀደዱ አስፈላጊ ነገር ነበር። ከእንግዲህ በኋላ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ምንም አይነት ግድግዳ አይኖርምና! ወደ እግዚአብሔር እና ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደው መንገድ አሁን ሙሉ በሙሉ ክፍት ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር ኢየሱስ ስለስዎች ሲሞት ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ዘግተው የነበሩትን ኪሩቤል እንደአስወገዳቸው ያህል ነው። ኢየሱስ ልክ እንደ በኤደን ገነት ይገኝ እንደነበረው የአትክልት ስፍራ ፍጹም ፍሬያማ ነው። ወደ እርሱ የሚመጡት ደግሞ ፍሬያማ ናቸው ምክንያቱም "በክርስቶስ ስለሆኑ" (ዮሐንስ 15፡1–17 ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች

በክርስቶስ ውስጥ በኤደን የሚገኘውን የአትክልት ቦታ የተወሰነ ፍሬ ቢለማመዱም የክርስቶስ ሥራ ሊያመጣው ያለውን መልካም ነገር ሁሉ ገና አላዩም። አንድ ቀን ፍጥረት እንኳን ከኃጢአት ውጤቶች ሁሉ ነፃ ይወጣል (ሮሜ 8 ይመልከቱ)። ይህም የሚፈጸመው ኢየሱስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ነው ( ራዕይ 21–22 ይመልከቱ)። በዚያን ጊዜ ክርስቲያኖች አዳምና ሔዋን እንኳን አይተውት የማያውቁት ነገር ይኸውም በምድር ሁሉ ላይ ሊዘረጋ ያለውን የኤደን ገነት ዓይነት የአትክልት ቦታ ያጋጥማቸዋል! ዛሬ የኤደንን ፍሬያማነት የምንለማመድው በእምነት ነው። በዚያ ቀን ግን እኛ በዓይናችን ፊት ለፊት እናየዋለንና!

18. **ምድር ለሰዎችና ለእጽዋት እና ለእንስሳት መኖሪያ ብቻ ከመሆን እጅግ የላቀ እንድትሆን ታስቦ ነበር።** በተለይም ሰማያትንና ምድር የሕያው እግዚአብሔር መቅደስ እንዲሆኑ ታስቦ ነበር። እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን እርሱ የሚመለከበት “ቲያትር” አድርጎ ነው የፈጠረው። በሰማይና በምድር ያለ እያንዳንዱ ነገር ያለማቋረጥ ውዳሴውን እንዲዘመር የታሰበ ነው (መዝሙር 148 እና ዕንባቆም 3፡3 ይመልከቱ)።
19. **አሪት ዘፍጥረት 1 ፣ 2 እና 3 ለአንባቢው ዓለምንና የዓለምን ታሪክ እንዴት መመልከት እንዳለበት ያስረዳሉ።** ስለዚህ እነዚህ ምዕራፎች ሊነበቡ፣ሊታመኑ እና ሊተገበሩ ይገባል። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙት እውነቶች የዓለምን አመለካከት እና የሚያነቧቸው ሰዎች ድርጊት መቅረጽ አለባቸው።
20. **ሙሴ የጻፈው ስለክርስቶስ ነው።** በሙሴ አምስት ክፍል መጽሐፍ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ቁጥር እና ምዕራፍ የኢየሱስ ታሪክ አካል ነው። ሉቃስ 24፡25–27፣ 24፡44–47፤ ዮሐንስ 1፡45 ፤ 5፡ 39–47፤ የሐዋሪያት ሥራ 26፡22–23፣ 28፡23 እና 1 ጴጥሮስ 1፡10–12 ይመልከቱ።
21. **እግዚአብሔር አይለወጥም።** በዘፍጥረት 1–4 (እና በብሉይ ኪዳን በሙሉ) የተገለፀው እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ከተገለፀው እግዚአብሔር ጋር አንድ ነው (ያዕቆብ 1፡17 ይመልከቱ)። ስለዚህ ዓለምን የፈጠረው እግዚአብሔር እስከ አሁንም ዓለምን በመቆጣጠር አለ (የሐዋሪያት ሥራ 17፡22–34 ይመልከቱ)።
22. **ብሉይ ኪዳን በዚህ ዘመንም ላሉ ክርስቲአይኖች ተጽፏል።** የአዲስ ኪዳን ደራሲዎች ሰዎችን ቅዱሳት መጽሐፍት እንዲያነቡ እና እንዲያምኑ ሲያበረታቱ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሱ ነበር። ይህም ግልጽ ነው ምክንያቱም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ገና አልተጻፉም ነበርና፤ (ሮሜ 4፡22–25፣ 15፡4፤ 1 ቆሮንቶስ 10፡6–11 እና 2 ጢሞቲዎስ 3፡14–17 ይመልከቱ)።
23. **የዘፍጥረት መጽሐፍ የእግዚአብሔር ፀጋ ምሳሌ ነው ምክንያቱም ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ከአዳምና ከሔዋን በኋላ ለሚኖሩ ሰዎች ነውና።** የመጀመሪያዎቹ ሰዎች የእግዚአብሔርን መልካም

ቃል አልተቀበሉም። እነርሱንም የተከተሉ ሁሉ እንዲሁ ያደርጉ ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ሊያጠፋ ይችል ነበር። እግዚአብሔር ግን በምሕረቱ ለኃጢአተኞ ሰዎች ቅዱስ መጽሐፍ ሰጠ። አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር በቀጥታ እንደ ተሰጣቸውና የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ ያስፈልጋቸው እንደ ነበር ሁሉ ዛሬም ሰዎች በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል ወደ እኛ የመጣውን የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ አለባቸው።

24. **የዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች በምሳሌ የተሞሉ ናቸው።** ምሳሌ ማለት ሰው፣ ቦታ ወይም አንድ ነገር በብዙ መንገዶች፣ ከተለየ እና የበለጠ ጠቃሚ ከሆነ ሰው፣ ቦታ ወይም ነገር ጋር ተመሳሳይ የሆነ ማለት ነው። ምሳሌ በትንሹ የአንድ ነገር ጥላ እንደ ማለት ነው። ለምሳሌ አዳም የክርስቶስ ምሳሌ ነው። እርሱ በብዙ መንገድ እንደ ክርስቶስ ነው። ለዚህም ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ ኢየሱስን "ኋለኛው አዳም" ብሎ የጠራው (ሮሜ 5፡12–14 ይመልከቱ)። በአዳምና በሔዋን መካከል የነበረውን ጋብቻ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን ማካከል ሊሆን ያለውን "ጋብቻ" ምሳሌ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ በክርስቶስና በቤተክርስቲያን መካከል ስላለው ግኑኝነት መናገር ሳይጀምር ስለ ምድራዊ ጋብቻ መናገር አይችልም ነበር (ኤፌሶን 5፡22–33 ይመልከቱ)። በዘፍጥረት 2 ከገነት የሚፈሰውን ወንዝ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው (ዮሐንስ 7፡37–39 እና ሕዝቃኤል 47፡1–12 ይመልከቱ)።

25. **የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ለማምለክ አለመፈለግ ታላቅ ኃጢአት ነው።** እግዚአብሔር ታጋሽ ነው። ሰዎችንም ሁሉ ወደ እርሱ እንዲመጡና እንዲያመልኩት ይፈልጋል። እዲያመልኩት ሲልም ነው ወደ ሰዎች የቀረበው። ስለዚህ እግዚአብሔርን ላለማምለክ እና ላለማመስገን እንቢ ማለት ትልቅ ወንጀል ነው (ሮሜ 1፡18–21 ይመልከቱ)።

## ዘፍጥረት 1፡1–2፡3

ሙሴ የዘፍጥረት መጽሐፍ ባደራጀበት መንገድ ተመርኩዘን ስንመለከት ዘፍጥረት 1፡1–2፡3 በዘፍጥረት 2፡4 ለሚጀምረው የሰማይና የምድር ታሪክ እንደ **መግቢያ** እንዲሆን ታስቦ የተጻፈ መሆኑን እንረዳለን (በዘፍጥረት 2፡4 ላይ ያለውን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ)። የሰማይና የምድር ታሪክ እስከ ራዕይ 20 መጨረሻ ድርስ አልተጠናቀቀም! በራዕይ 21 ላይ አዲስ ታሪክ – የአዲሲቱ ሰማይንና የአዲስቱ ምድር ታሪክ ይጀምራል! በመጽሐፉ ውስጥ ያለው **መቅደም** አንባቢው ታሪኩን በትክክል እንዲያነብ የሚረዳ አስፈላጊ የጀርባ መረጃ ለአንባቢው ይሰጣል። በአጭር አገላለጽ በዘፍጥረት 1፡1–2፡3 ላይ ለአንባቢው የሚሰጠው ይህንኑ ነው። ስለዚህ በዘፍጥረት 2፡4 ላይ የሰማይና የምድር ታሪክ ከመጀመሩ በፊት አንባቢ በዘፍጥረት 1፡1–2፡3 ያሉትን ነገሮች ማወቅ አለበት። ዘፍጥረት 1፡1–2፡3 የሰማይና የምድር ታሪክ መጀምሪያ እንደ ትልቅ ስዕል ነው። በዘፍጥረት 2፡4–25 ደግሞ ተመሳሳይ ታሪክ በቅርብ እይታ ተሰጥቶናል።

ዘፍጥረት 1:1–2:3 ስለ "ሰማያትና ምድር" አፈጣጠር ይናገራል። በእነዚህም ጥቅሶች ውስጥ አንባቢው በዓለም ታሪክ ውስጥ የሚሰራውን ፍፁም ስላሴ የሆነውን አምላክ "እንዲያይ" ተፈቅዶለታል። አንባቢው የሚያየውን መሠረት በማድረግ እሱ ወይም እሷ የእግዚአብሔርን ኃይልና ባህሪ በማሰብ ማሰላሰልና ስለ ሥራውንም በአንክሮት ሊያመሰግኑት ይገባል (ሮሜ 1፡21 ይመልከቱ)። ደግሞም አንባቢው በእነዚህ የመከፈቻ ጥቅሶች ላይ በተጻፉት ነግሮች በመመስረት፤ እግዚአብሔር አጽናፈ ዓለሙንና በውስጡ ያሉትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረበትን ዓላማ አጥብቆ ሊያስበበት ይገባል።

በዘፍጥረት 1:1–2:3 ውስጥ የእግዚአብሔር ባህሪ ምን እንደሆነ ለአንባቢው **አልተነገረም** ይሁን እንጂ (የእግዚአብሔር ባሕርይ እንደ ዘፀአት 34፡6–7 ባሉ ምንባቦች ውስጥ በግልፅ ተገልጿል)። ይልቁንም ለአንባቢው እግዚአብሔር በንግግሩና በተግባሩ ምን **እንደሚመስል** እንዲያይ ተደርጓል። በተለይም ሙሴ ስለ እግዚአብሔር የተናገራቸው ቃላት እግዚአብሔር ጥበበኛ፣ ኃያል፣ ፈጣሪ፣ደግ፣ ለጋስ፣ አፍቃሪ እና ፍትሐዊ መሆኑን ያሳያሉ። አንባቢው በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የግዚአብሔርን ቃል እና ድርጊቶች ሲያነብ እነዚህን ነገሮች ሊማር ይችላል።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍጥረት ከሰብአዊነት አንፃር የማየት አዝማሚያ ያላቸው ቢሆንም ሰማያትንና ምድርን ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ለማየት መሞከር አስፈላጊ ነው። ሰማይና ምድር የእግዚአብሔር

መቅደስ እንዲሆኑ የታሰቡ ከመሆናቸውም በላይ እግዚአብሔርም የሚመለክበት ቦታ ናቸውና። ስለዚህም ነው በሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ሰማይና ምድር ከመቅደሱ ጋር የተነጻጸሩት።

*መቅደሱ እንደ አርያም ሠራ፤ ለዘላለምም በምድር ውስጥ መሠረታት* (**መዝሙር 78፡69**)።

ምንም እንኳን በዘፍትረት 1፡1–2፡3 ላይ ያለው እያንዳንዱ ቃል (እና መላው መጽሐፍ ቅዱስ) እውነት ነው፤ ይሁን እንጂ እነዚህ የመጀምሪያዎቹ ጥቅሶች እንደ ሳይንስ መጽሐፍ እንዲያገለግሉ የታሰቡ አልነበሩም። ደግሞም እነዚህ ጥቅሶች  ስለ አጽናፈ ሰማይ እና ምድር ሳይንሳዊ እውነታዎችን ለማብራራትም የተጻፉ አይደሉም። በተጨማሪም እነዚህ ጥቅሶች የተጻፉት የተፈጥሮ ነገሮች የሚሰሩበትን መንገድ ከሳይንሳዊ እይታ አንጻር ለማብራራትም አይደለም። እንግዲህ እነዚህ ጥቅሶች ሳይንስን ለማስተማር የታቀዱ ካልሆኑ ምን ለማስተማር ታስቦ ነበር ይሆን? በዋንኛነት እነዚህ ጥቅሶች የተጻፉት ስለ እግዚአብሔር አንዳች ነገር እንዲናገሩ ታስቦ ነው። እግዚአብሔር የዘፍጥረት 1፡1–2፡3 ዋና ነጥብ ነውና። እነዚህ ጥቅሶች የተጻፍት በጣም በተሰበረ ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን በእግዚአብሔር እምነት እንዲኖራቸው ወደ ሕያው እግዚአብሔር ለመምራት ነው።

በዚህ ዘመን እኛ አንባቢዎች እንደ መሆናችን መጠን እነዚህን ቃላት ሲነበብላቸው ከሰሙት የመጀመሪያዎቹ ሰዎች በተለየ ዘመን እንደምንኖር መረዳት ይኖርብናል። በተለይም አሁን የምንኖርበት የስልጣኔ ዘመን እንደ መሆኑ መጠን የዘፍጥረትን ቃላት በምንሰማበት ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ስለ ዘፍጥረት 1 ስናስብ ምናልባትም ዝግመተ ለውጥ ደግሞ እናስብ ይሆናል። እነዚህ ጥቅሶች ፈጣሪ እንደሌለና ነገሮች በአጋጣሚ የተገኙ ናቸው ከሚለው ዘመናዊ እምነት ጋር እንዴት እንደሚስማሙ እናስብ ይሆናል። ይሁን እንጂ በሙሴ ዘመን (ከግብፅ በምድረ በዳ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲጓዙ ከነበሩት እሥራኤላውያን) እነዚህ ጥቅሶች መጀመሪያ ሲነበብላቸው ስለ ዝግመተ ለውጥ ሐሳብ አልነበራቸውም እንዲህ የሚያስብም ማንም እንዳልነበረ ደግሞ ግልጽ ነው። ኦሪት ዘፍጥረት በተጻፈበት ዘመን ማንም በዝግመተ ለውጥ የሚያምን አልነበረም፤ ስለዚህ የእነዚህ ጥቅሶች ዓላማም ዝግመተ ለውጥን ውድቅ ለማድረግ አልነበርም።

በሙሴ ዘመን የነበሩ ሰዎች በዝግመተ ለውጥ ባያምኑም፣ ይህ ማለት ግን የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ ያምኑ ነበር ማለት ደግሞ አይደለም። በሙሴ ዘመን ይኖሩ የነበሩት አብዛኞቹ ሰዎች ሌሎችን አማልክት ያመልኩ ነበር። ከእነዚህም አማልክት አንዳንዶቹ በራሳቸው በሰዎች የተሰሩና በሰው አምሳያ የተቀረጹ ነበሩ። ይህም ደግሞ የዘፍጥረት 1፡26–27 ተቃራኒ ነው። ሰዎች እንደ አምላክ

ቆጥረው ያመልኩዋቸው ከነበሩት ጥቂቶቹ እንደ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣አሦች፣ወፎች፣ ተሳቢ እንሣት እና የተለያዩ አጥቢ እንስሳት የመሳሰሉት ነበሩ። ይሁን እንጂ የኦሪት ዘፍጥረት ጥቅሶች ግን አንዳቸውንም አምላክ እንዳልሆኑ ያሳያሉ። አንድ አምላክ ብቻ አለ። እርሱም ሁልጊዜ ያለና የሚኖር ነው። ስለዚህ እነዚህ የዘፍጥረት ጥቅሶች የአንዱ እውነተኛ አምላክ ታሪክ በከፊል ይናገራሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰዎችና ስለ ፍጥረት የሚናገርው እግዚአብሔር እንዲነገር በሚፈልገው መንገድ ነው። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የጥንት ሰዎች ለመቀበል የሚታገላቸው መረጃ አለ። እንደዚሁም ደግሞ የአሁኑ ዘመናዊ ትውልድም ለመቀበል የሚያዳግተው በእነዚህ ጥቅሶች የተገለጥጹ መረጃዎች ደግሞ አሉ። ይሁን እንጂ በሁለቱም ሁኔታዎች ቢሆን ሰዎች እግዚአብሔር በተናገረው ነገር መታምን አለባቸው። እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ እምነት እየጠራ ነውና።

እነዚህ ጥቅሶች የሰው ልጆች ያላቸውን የአቅም ገደብ ያሳያሉ። የማናውቀው ትልቅ ነገር አለ። በእርግጥ ሰዎች በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ያለውን መረጃ በእግዚአብሔር ካልተገለጠላቸው በስተቀር ሊረዱት አይችሉም። እነዚህን እውነታዎች መረዳት የሚቻለው ከእግዚአብሔር በሚገኝ ጸጋ ብቻ ነው። ስለዚህ ጥንቁቅ አንባቢ የሙሴን ቃላት አንብቦ ምን እንደሆነ ለመረዳት ይጥራል በእነዚህም ጥቅሶች በምን ላይ አጽንዖት እንደሚሰጥ ለማወቅ ይጣጣራል። ከዚህ በተጨማሪ ጠንቃቃ አንባቢ ሙሴ ሰዎች ሁሉ እንዲያመልኩት የሚፈልገውን አምላክ ደግሞ ያመልካል።

ኦሪት ዘፍጥረት 1፡1–2:3

## ዘፍጥረት 1

1[1] በመጀመሪያ፣ [2]

[1] ኦሪት ዘፍጥረት 1፡1–2:3 በጣም የተዋቀረ ነው። ከመጀመሪያው ጥቅስ ጀምሮ ስንመለከት ይህ ክፍል በጥንቃቄ መጻፉን የሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ለምሳሌ በቁጥር 1 ላይ (በዕብራይስጥ) የተጻፉ ሰባት ቃላት አሉ። እነዚህ ሰባት ቃላት ደግሞ የፍጥረትን ሰባት ቀናት ያስተጋባሉ።

[2] “በመጀመሪያ” የሚለው ቃል የሁሉም ነገር መጀመሪያ እንደ ማለት አይደለም። ሙሴ እየተናገረ ያለው ሰማያትንና ምድርን የተፈጠሩበት እንዲሁም በውስጣቸው ያለውን ሁሉ የተጀመሩበት ጊዜ ማለቱን ነው። ይህ ታሪክ ሲጀምር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞም እንደ ነበሩ ማወቅ አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነውና። መጀምሪያም መጨረሻም የለውም (መዝሙር 93፡1–2 ይመልከቱ)። ኦሪት ዘፍጥረት 1፡1–2:3 እግዚአብሔር ከየት እንደመጣ ወይም ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው በፊት ምን እንዳደረገ አያብራራም። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የተነገረው ታሪክ ይህን የተመለከተ አይደለም። ሆኖም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ስለተፈጸሙት ክንውኖች ተጨማሪ መረጃ በሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ማግኘት ይቻላል (ለምሳሌ ዮሐንስ 17፡5፣ 24 እና ኤፌሶን 1፡3–6 ይመልከቱ)።

ሐዋሪያው ዮሐንስም ወንጌሉን ለመጻፍ ሲጀምር “በመጀምሪያ” የሚለውን ቃል ተጠቅሟል። ዮሐንስ በዘፍጥረት 1፡1 ያሉትን እነዚህን ቃላት በመጠቀም አንባቢዎቹን ስለ ኢየሱስ ማንነት እንዲያስቡ እና ኢየሱስን ከፍጥረት ታሪክ ጋር እንዲያገናኙት እንደሚፈልግ ግልጽ ነው (ዮሐንስ 1፡1–2 ይመልከቱ)። በተጨማሪም 1 ዮሐንስ 1፡1 ይመልከቱ።

እግዚአብሔር[3]

[3] **በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (እና በአጽናፈ ሰማይ) የመጀመሪያው ጥቅስ የሚያስተዋውቀው በጣም አስፈላጊው ገፀ ባህሪ፤ እግዚአብሔርን ነው።** በኦሪት ዘፍጥረት 1፡1–2:3 ብቻ የእግዚአብሔር ስም 35 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። ይህ በጣም አስደማሚ ቁጥር ከመሆኑም በላይ ለአንባቢው በጣም ከአቅም በላይ እንዲሆን የታሰበ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ጸሐፊዎች ስምን  ብዙ ጊዜ አይደጋግሙም። ጸሐፊዎች በተለምዶ ለአንባቢው ማን እንደ ተጠቀሰ ካሳወቁ በኋላ ወደ ተውላጠ ስም (ማለትም "እሱ") ወደ ሚለው ይቀይራሉ። ምንም እንኳን ሙሴ ይህን ታሪክ ሲናገር "እሱ" የሚለውን ተውላጠ ስም ሊጠቀም የሚችል ቢሆንም ቅሉ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ስም ደጋግሞ ለመጠቀም ሲመርጥ እንመለከታለን፤ ምክንያቱም ክፍሉ አጽንዖት የሚሰጠው እግዚአብሔር የምንባቡ ዋና ነጥብ እንደሆነ እና እነዚህንም ነገሮች ያደረገው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ለማስረዳት ስለፈለገም ጭምር ነው።

ሙሴ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ እግዚአብሔር መኖሩን ለማረጋገጥ ጥረት አያደርግም። ይህ ደግሞ የማይቻል ጉዳይ ነውና፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ሕልውና ለማረጋገጥ ከእግዚአብሔር የሚበልጥ እውነት ያስፈልጋልና። ከሁሉም ነገር በፊት እግዚአብሔር ነበረ፤ ስለዚህ የእርሱን መኖር ለማረጋገጥ ሌላ ምንም ነገር ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም። በእምነት በእግዚአብሔር ልንታምን ይገባል እንጂ። ዘፍጥረት 1፡1 እግዚአብሔር እንዳለና ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ **አስቀድሞ ያስረግጣል**። ይህም እንደገና እምነትን ይጠይቃል። ምንም እንኳን ይህ እውነት በአንባቢው ዓይን ሊታይ ባይችልም እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከመጀመሪያው ጥቅስ ጀምሮ አንባቢው ስለ እግዚአብሔር እውነቱን እንዲያምን እየተጠየቀ ነው።

ዘፍጥረት 1፡1 እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ ይናገራል። ይህ ማለት ደግሞ ሌሎች "አማልክት" (ማለትም ጣዖታት) ዓለምን ወይም በዓለም ላይ ያለውን ምንም ነገር አልፈጠሩም ማለት ነው። ሌሎች አማልክት እንዲህ ዓይነቱን ነገር ለማከናወን አቅም እንደሌላቸው በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በሙሉ ተብራርቷል።

በዘፍጥረት 1፡1 በአማርኛ "እግዚአብሔር" ተብሎ የተተረጎመው ስም በዕብራይስጥ **ኤሎሂም** በመባል ይታወቃል። ይህ ስም በሙሴ መጽሐፍ (ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም) ባለው ክፍል 699 ጊዜ ያህል ጥቅም ላይ ውሏል። ይሁን እንጂ በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ለእግዚአብሔር መጠሪያነት ጥቅም ላይ የዋለው በጣም የተለመደ ስም አይደለም። ይልቁንም በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ በጣም የተለመደው የእግዚአብሔር ስም **ያህዌ** የሚለው ሲሆን (ይህም "ጌታ") ተብሎ ተተርጉሟል – ይህንኑ ለማጉላት በተለይም በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች በአብይ ሆሄ ሲጻፍ በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ከጎኑ በአማርኛ ፊደላት "ያህዌ" ተብሎ ተመልክቷል። በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ **ያህዌ** የሚለው ስም 1,581 ጊዜ ያህል ጥቅም ላይ ውሏል። ያህዌ የሚለው የእግዚአብሔር "የግል" ስሙ ነው። **ኤሎሂም** የሚለው ስም ደግሞ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ያለውን ግላዊ ግኑኝነት አንጽዖት አይሰጥም። ስለዚህ ኤሎሂም የሚለው እንደ አጠቃላይ ስም ነው። ይህም ማለት ደግሞ **ኤሎሂም** ለመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲዎች ሁኔታው የበለጠ የግል ስም ጥቅም ላይ እንዲውል በማይፈለጉበት ጊዜ ለመጠቀም ተፈጥሯዊ ምርጫ ነው። ሌሎች የእግዚአብሔር ስሞች በሌሎች ሁኔታዎች ውስጥ ጥቅም ላይ ይውላሉ ማለት ነው። ለምሳሌ፣ ከዘፍጥረት 2፡4 ጀምሮ ባለው ክፍል **ያህዌ ኤሎሂም** (በአማርኛ "ጌታ አምላክ" ወይም በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ደግሞ "እግዚአብሔር አምላክ") ተብሎ ተተርጉሞ ለእግዚአብሔር የተለየ ስም እንደሆነ ተደርጎ ጥቅም ላይ ውሏል። ከዘፍጥረት 2፡ 4 ጀምሮ ጥቅም ላይ የዋለው የተለያየ ስም የሚያመለክተው የተለየ የእግዚአብሔር ማንነት ወይም ባህሪ ላይ ያተኮረ መሆኑን ነው። በሙሴ መጽሐፍ  "ጌታ አምላክ" ወይም "እግዚአብሔር አምላክ" የሚለው 29 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል።

በሌላ በኩል ደግሞ **ኤሎሂም** ብዙ ቁጥር ያለው የዕብራይስጥ ስም መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይህ ማለት የዚህ አይነት ፍጻሜ ያላቸው የዕብራይስጥ ቃላት በመደበኛነት ከአንድ በላይ የሆኑ ነግሮችን ያመለክታሉ ማለት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ለምን በዚህ ስፍራ ጥቅም ላይ የዋለው የእግዚአብሔር ስም ብዙ እንደሆነ ይከራከራሉ። ይሁን እንጂ በጣም ቀላሉና አጥጋቢ ማብራሪያ የሚሆነው እግዚአብሔር ከአንድ በላይ መሆኑን መረዳት ነው። ሆኖም ግን፤ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው ግስ ቁጥር ("**ፈጠረ**") የሚለው ነጠላ ነው። ስለዚህም በዚህ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔር ብዙ ቁጥር ያለውና ደግሞ አንድ እግዚአብሔር መሆኑን እንማራለን። **እንግዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከመጀመሪያው ቁጥር የሥላሴ ፍንጭ የተመለከትን ሲሆን** (በተጨማሪም በዘፍጥረት 1፡26 እግዚአብሔር እንዴት እንደተጠቀሰ ይመልከቱ)! አንዳንዴ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ሙሴ ይህን ማለት አይችልም ምክንያቱም እግዚአብሔር ከአንድ በላይ መሆኑን ገና አልተረዳም ነበርና በማለት ይከራከርሉ። አንዳንዶች እንደሚሉት ከሆነ ይህ እውነት ለረጅም ጊዜ አልተገለጠም ነበረ። በቃሉ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ብዙ ቁልፍ ነገሮች ቢኖሩም እስከ ኢየሱስ መምጣት ድረስ አልተገለጡም ነበር፤ ይሁን እንጂ ይህ ማለት ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት የትኛውም እውነት አይታወቅም ነበር ማለት አይደለም። እንደ ሐዋሪያው

ጴጥሮስ ከሆነ ደግሞ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ብዙ ሰዎች ከሚያምኑት በላይ ያውቁ እንደነበረ ነው (1 ጴጥሮስ 1፡10–12 ይመልከቱ)። አሁንም ይህ ማለት ሙሴ ስለ ሥላሴ በግልፅ ሊተነትን ይችል ነበር ማለት አይደልም። ነገር ግን ይህ ማለት ሙሴ እግዚአብሔር በአንድም በብዙ ቁጥርም ሊገለጽ እንድሚችል ያውቅ ነበር ማለት ነው። **ሙሴ ስለ ሥላሴ የተረዳው ገና በጥቂቱ በመሆኑ ያየውን ለማወጅ ይጠነቀቅ ነበር።**

ሰማይንና ምድርን[4] [5] [6]ፈጠረ። [7]

---

[4] “ሰማያትና ምድር” የሚለው ሐረግ ሁለት የተለያዩ ቦታዎችን ያመለክታል። ነገር ግን (እዚህ ቦታና በሌሎችም በርካታ ቅዱሳት መጽሕፍት) ውስጥ ለአንባቢ አንድ ነገር እንዲያስተምሩ ታስቦ እነዚህን ሁለት ቦታዎች አንድ ላይ ተጽፈው እንምለከታለን፤ ይህም **እግዚአብሔር የሁሉም ነገር ፈጣሪ** መሆኑን ለማስገንዘብ ነው። ይህ አንድ ሰው (በአማርኛ) “የሂሳብ ሥራን ከ ሀ እስከ ፐ ታውቃለች” ከሚልው ጋር ተመሳሳይነት አለው። በዚህ ምሳሌ የምንረዳው በአማርኛ ፊደላት ውስጥ የመጀመሪያው እና የመጨረሻው ፊደላት ስለአንድ ሰው አንድ ነገር ለማስተማር ማለትም ስለሂሳብ አያያዝ ሁሉንም እንደ ምታውቅ ለመናገር ሆሄያቱ አንድ ላይ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ማለት ነው። ስለዚህ ይህች የሂሳብ ሥራ አዋቂ ሁሉንም ነገር ታውቃለች ስንል ከ (ሀ) እስከ መጨረሻው (ፐ) እና በመካከላቸው ያለውን ሁሉ (ለ፣ሐ፣ መ፣ ሠ፣ ረ፣ ሰ፣ ወዘተ) ሁሉ ታውቃለች ማለት ነው! በዘፍጥረት 1፥1 ላይም ተመሳሳስይ ነው። እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ሲል ደራሲው ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ ይናገራል። እግዚአብሔር ያልፈጠረው ነገር የለም። እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ መሆኑ ከሁሉም ነገር ጋር በምንገናኝበት መንገድ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ይህም ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ንብረት መሆኑን መረዳት መቻል አለብን። ለዚህም ነው “የሰማይና የምድር ባለቤት ነው” ተብሎ የተጠራው (ዘፍጥረት 14፡19፣ 22 ይመልከቱ)። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ “ሰማያትንና ምድር” እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋሉ ማጥናት ለሰባኪ ወይም ለአስተማሪ ትልቅ እገዛ ሊያደርግ ይችላል። በተጨማሪም ዘፈጥረት 2፥1፣ 2፡4፣ 14፡19፣ 14፡22፤ ዘፀአት 20፡11፣ 31፡17፤ ዘዳግም 4፡26፣ 30፡19፣ 31፡28፤ 2 ነገሥት 19፡15፤ 2 ዜና 2፡12፣ ዕዝራ 5፡11፤ መዝሙር 69፡34፣ 113፡6፣115፡15፣ 121፡2፣ 124፡8፣ 134፡3፣ 146፡6፤ ኢሳይያስ 37፡16፤ ኤርሚያስ 10፡11፣ 23፡24፣ 32፡17፣ 33፡25፣ 51፡48፤ ኢዩኤል 3፡16፤ ዕንባቆም 3፡3፤ ሐጌ 2፡6፣ 2፡21፤ ማቴዎስ 5፡18፣ 11፡25፣ 24፡35፤ ማርቆስ 13፡31፤ ሉቃስ 10፡21፣ 16፡17፣ 21፡33፤ የሐዋሪያት ሥራ 17፡ 24፤ 2 ጴጥሮስ 3፡7 እና ራዕይ 14፡7።

ሰማያዊ ምስሎች እንደነ (ኪሩቤል) እና ከምድር ደግሞ (ፍራፍሬ፣ አበባ፣ ዛፎችና እንስሳት) በቤተ መቅደሱ ውስጥ መገኘታቸውን ልብ ማለት ያስፈልጋል (1 ነገሥት 6–8 ይመልከቱ)። ይህም ቤተ መቅደሱ የሰማይና የምድር ትንሽ ገጽታ እንዲሆን ታስቦ እንደ ነበር ማሳያ ይመስላል። በሌላ አነጋገር ደግሞ ሰማይና ምድር የተፈጠሩት እግዚአብሔር የሚመልክበት ቤተ መቅደስ እንዲሆኑ ነው። ይሁን እንጂ አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጣሳቸው ምክንያት ይህ ለሰማያትና ለምድር የታቀድው ዓላማ አልተፈጸመም። የኋለኛው አዳም ኢየሱስ የመጣው ሰማይና ምድር አስቀድሞ እንደታሰበው ይሆኑ ዘንድ ነው፤ ደግሞም እንደ እግዚአብሔር መቅደስ አገልግሎት በመስጠት ሁሉም ነገር እግዚአብሔርን ማምለክ ይችል ዘንድ ነው (መዝሙር 148፡3–5፣ 150፡6፤ ኢሳይያስ 11፡9 እና ዕንባቆም 2፡14 ይመልከቱ)።

[5] ዘፍጥረት 1፥1–2፡3 ስለ “ሰምይና ምድር” **መጀመሪያ** ታሪክ ይናገራል። እንደዚሁም ቅዱሳት መጽሐፍት ስለ ሰማይና ምድር **ፍጻሜ** ይናገራሉ (ማቴዎስ 24፡35፤ ማርቆስ 13፡31 እና 2 ጴጥሮስ 3፡1–13 ይመልከቱ)። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ አዲስ ሰማይና ምድር በብዛት ይናገራሉ። ለምሳሌ ያህል ኢሳይያስ 65፡17፤ ሮሜ 8፤ 2 ጴጥሮስ 3፡13 እና ራዕይ 21–22 መመልከት ይቻላል።

[6] እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን እንዲፈጥር ያደርገው አንዳችም ምክንያት እንዳልተነገረን ልብ ማለት ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን እንዲፈጥር ያስገደደው ማንም ወይም ምንም አልነበረም። በፍጥረቱ በኩል መሟላት የነበረባቸው ምንም ጉደለት አልነበረውም። እንደዚሁም አንድን ችግር ለመፍታት ምንም ዓይነት አስገዳጅነት አልነበረበትም። ስለዚህ እግዚአብሔር ምድርን (እና ሰዎችንም) የፈጠረው በራሱ በሆነ ምክንያት ነው። የተጻፈውም የሚያስረዳን እግዚአብሔር በራሱ ምርጫ እንዳደረገ ነው። ስለዚህ በምድር ላይ ያለ እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር ምድርን ለመፍጠር ያነሳሳው መልካም አላማዎች ለይቶ ማወቅ ደስታውና ግዴታው ነው። እንደ እድል ሆኖ ግን እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የፈጠረበትን መልካም አላማውን በብዙ ቅዱሳት መጽሐፍት ተገልጾአል። ለምሳሌ ያህል ዘፈጥረት 1፡26–28፤ ኢሳይያስ 43፡6–7፤ የሐዋሪያት ሥራ 17፡26–27 እና ኤፌሶን 1፡10 ይመልከቱ።

[7] በዚህ ጥቅስ “ፈጠረ” ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለእግዚአብሔር ብቻ ጥቅም ላይ ውሏል። እግዚአብሔር ብቻውን ፈጣሪ ነው። ይህ **የዕብራይስጥ ቃል ከሰዎች ሥራ ጋር ፈጽሞ አይገናኝም**፤ (በተጨማሪ ዘፍጥረት 1፡21፣ 1፡27፣ 2፡3፣ 2፡4፣ 5፡1–2፣ 6፡7፤ ዘፀአት 34፡10፤ ዘኍልቁ 16፡30፤ ዘዳግም 4፡32፤ መዝሙር 51፡10፣ 89፡ 12፣ 89፡47፣ 102፡18፣ 104፡30፣ 148፡5፤ መክብብ 12፡1፤ ኢሳይያስ 4፡5፣ 40፡26፣ 40፡28፣ 41፡20፣ 42፡5፣ 43፡1፣ 43፡7፣ 43፡15፣ 45፡7፣ 45፡8፣ 45፡12፣ 45፡18፣48፡7፣ 54፡16፣ 57፡19፣ 65፡17–18፤ ኤርሚያስ 31፡22፤ ሕዝቅኤል 21፡30፣ 28፡13፣ 28፡15፤ አሞጽ 4፡13 እና ሚልክያስ 2፡10 ይመልከቱ)። ይህም እግዚአብሔርንና ጥበቡን፣ ኃይሉን እና ሥራውን እንዴት እንደምንረዳ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ስለፈጠረ ደግሞም የሰማይንና የምድር ባለቤት በመሆኑ ምክንያት በእነርሱ ውስጥ ስለሚፈጸሙት ክንውኖች በጥልቀት ይከታተላል። እግዚአብሔር ደግሞ

2 ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበርባትም፤[8] ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር።[9]

---

ፈጣሪያቸው እንደመሆኑ መጠን ሁሉም የእርሱ አጋልጋዮች ናቸው፤ መዝሙር 119፡89–91 ይመልከቱ። በተጨማሪም ደግሞ ኤርሚያስ 27፡4–5 እና 1 ቆሮንቶስ 6፡13፣ 19–20 ይመልከቱ።

[8] እግዚአብሔር **ሆን** ብሎ ምድርን ያለ መልክና ባዶ አድርጎ ፈጠረው። ነገር ግን ሁሉ ነገር የተሟላበት ሙሉ በሙሉ አድርጎ ሊፍጥረውም ይችል ነበር። ምድርን በዚህ መንገድ የፈጥረው ለምንድነው? እንግዲህ በዚህ መንገድ ያደረገው ሰዎች እግዚአብሔር በአለም ውስጥ እንዴት እንደሚሰራ ማየት እንዲችሉ ይመስላል። በእነዚህ የመጀመሪያ ጥቅሶች ውስጥ **እግዚአብሔር (በቁጥር 3) በቃሉ እና (በቁጥር 2) ደግሞ በመንፈሱ ነገሮችን እንዳስተካከለ እንማራለን** ። ክርስቶስ ደግሞ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ ዮሐንስ 1፡1–17 ይመልከቱ።

“ባዶና አንዳች አልነበረባትም” የሚሉት ቃላት በዕብራይስጡ ብርቅዬ ቃላት ናቸው። ደግሞም የግጥም ቃላት ሲሆኑ (**ቶሁ** እና **ቦሁ** በምባል ይነበባሉ)። የግጥም ቃላት በመሆናቸውም በቀላሉ ለማስታውስ ይጠቅማል ማለት ነው። በተጨማሪም ቆየት ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲዎች እነዚህን ብርቅዬ የግጥም ቃላት ሲያነቡ ዘፍጥረት 1፡2ን እንዲያስታውሱ የዘፍጥረት ደራሲ እንደሚፈልግ ፍንጭ ይሰጣል። ነቢዩ ኤርሚያስም  እነዚህን ቃላት በኤርሚያስ 4፡23 ላይ ጠቅሷል። የእግዚአብሔር ሕዝብ የጣዖት አምልኮት ምድርን ወደ “ቶሁ እና ቦሁ” (“ባዶና አንዳች ያልነበረባት”) ሁኔታዋ እንድትመለስ እንዳደረጋት ያውጃል። ይህ በጣዖት አምልኮት ምክንያት የሆነ እርግማን ነው! ነቢዩ ኢሳይያስም ደግሞ በኢሳይያስ 34፡10–11 ላይ እነዚህኑ ቃላት ጠቅሶ እንመለከታለን። ነብዩ ኢሳይያስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች “ቶሁ እና ቦሁ” እንደሚሆኑ ያውጃል። ይህም በአመፃቸው ምክንያት የሆነ እርግማን ነው። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ከ “ቶሁ እና ቦሁ” ግዛት ለማውጣት እግዚአብሔር ይጠቀምባታል።

[9] መንፈስ ቅዱስ በውሃው ላይ ሰፍፎ ነበር። እንግዲህ በዚህ ሥፍራ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ዕቅዶች እንዲፈጽም የእግዚአብሔር ቃል እስኪመጣ እየጠበቀ ያለ ይመስላል። እግዚአብሔር በመንፈሱ ካልሆነ በቀር ምንም አያደርግምና (ለምሳሌ የሐዋሪያት ሥራ 11፡28፣ 13፡4፣ 15፡8፣ 16፡6፤ ሮሜ 2፡29፣ 8፡ 13፣ 15፡13፣ 15፡16፤ 1 ቆሮንቶስ 6፡11፣ 12፡9 እና 12፡11 ይመልከቱ)። የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ ሁልጊዜ አብረው የሚሰሩት ፍጹም በሆነ መስማማት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ አሁንም በዓለም ላይ እየሰራ ነው። መንፈስ ቅዱስ ከእንግዲህ ወዲህ የእግዚአብሔርን ቃል እየጠበቀ “መስፈፍ”  አያስፈልገውም። አሁን በኢየሱስ ላይ “አርፏል” ስለዚህም ከክርስቶስ ጋር የተያያዙ ነገሮች ሁሉ ከበተስጀርባው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ደግሞ አላቸው ማለት ነው፤ ማርቆስ 1፡9–11 እና ዮሐንስ 3፡34 ይመልከቱ። በዘፍጥረት 1፡2 ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተገናኘው የዕብራይስጥ ግስ እና የግስ ቅርጽ ያለው “መስፈፍ” የሚለው ቃል በዘዳግም 32፡11 ላይም ጥቅም ላይ ውሏል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይህ ተመሳሳይ ግሥ በዚህ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለው ብቸኛው ቦታ በዚህ በዘዳግም ክፍል ላይ ነው። ዘዳግም 32፡11–12 ላይ እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን “ቶሁ” ውስጥ እንዳገኛቸውና እንዲንከባከባቸውም ከቶሁ ቦታ ወደ ተሻለ ስፍራ (የተስፋይቱ ምድር!) እንዲያመጣቸው በላያቸው ላይ እንደሰፈፈ ይናግራል። ስለዚህ እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር የገቡበት ሂደት ከዘፍጥረት 1፡2 ጋር የሚነጻጸር ነው። ሁኔታው ተመሳሳይ ታሪክ ነው! ምክንያቱም እነዚህ ሁለት ክፍሎች ሰዎችን  ከቶሁ ወደ እግዚአብሔር መልካም ሥፍራ ማምጣት የመንፍስ ቅዱስ አንዱ ተግባር እንደሆነ የሚያስተምሩ ይመስላልና። በአሪት ዘፍጥረት ይህን አድርጓል፣ ደግሞም ለእሥራኤላውያን እንዲሁ አድርጎላቸዋል፣ ዛሬም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ደግሞ ይህንኑ ተመሳሳይ ነገር እያደረገ ነውና!

3 እግዚአብሔርም፡ –[10] ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ።[11]

4 እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደ ሆነ አየ፤[12] እግዚአብሔርም ብርሃንንና ጨለማን ለየ።

5 እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው፡ ጨለማውንም ሌሊት አለው። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ
“አንድ ቀን።”[13] [14]

---

[10] ከዘፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ የእግዚአብሔር ቃል አንፆት ሰጥቶበታል።እግዚአብሔር ዝም አላለም። እርሱ የሚናገር አምላክ ነውና። በቃሉ ይፈጥራል። በቃሉ ያስተምራል። በቃሉ ይባርካል። በቃሉ ያዛል። በቃሉ ነገሮችን መልካም ወይም ክፉ አድርጎ ይተረጉማል። በቃሉ ይፈርዳል። እነዚህ የመጀመሪያ ምዕራፎች እግዚአብሔር በቃሉ የተናገራቸው ነገሮች ሁሉ እንደሚፈጸሙ ያሳያሉ። ለዚህም ነው ሙሴ ደጋግሞ “እንዲሁም ሆነ” የሚለው። ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙና ደግሞም እንዲታዘዙ ተጠርተዋል። መዝሙረኛው በመዝሙር 29 ላይ ስለ እግዚአብሔር ኃይለኛ ድምፅ ሲናገር ስለዚህ ክፍል (እና ሌሎችም) እያሰበ ይሆናል።

[11] በቁጥር 14–19 እንደ ተመለከተው እግዚአብሔር ፀሐይን ከመፍጥሩ በፊት በቁጥር 3 ላይ ብርሃንን ፈጥረ ይላል። ስለዚህ ፀሐይ በዓለም ላይ ለነበረው ጨለማ እንደ መፍትሄ አልቀረበም።ይልቅስ በዓለም ላይ ለነበረው ጨለማ መፍትሄ ተደርጎ የተወሰደው ከእግዚአብሔር ከራሱ የሚመጣው ብርሃን ነው። ይህም ደግሞ ሰባኪዎች እንደነ ዮሐንስ 1፡4–9፣ 8፡12፣ 9፡5 እና 2 ቆሮንቶስ 4፡4–6 የመሳሰሉትን የአዲስ ኪዳን ምንባቦች ወዲያውኑ እንዲያስታውሱ ያደርጋቸዋል። በእነዚህ ሁሉ ክፍሎች ውስጥ ኢየሱስ ብርሃን እንደሆነ ተገልፆአል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ጀመረው የሚጨርስ መሆኑን ልብ ማለት አስፈላጊ ነው። አዲስ ፍጥረት አለ፣ እና ለዚህ አስዲ ፍጥረት ብርሃን ለመስጠት ፀሐይ አያስፈልግም፤ ምክንያቱም “ለከተማይቱም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት ሙብራትዋም በጉ ስለ ሆነ፤ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጓትም ነበር። አሕዛብም በብርሃንዋ ይመላለሳሉ፤ የምድርም ነገሥታት ክብራቸውን ወደ እርስዋ ያመጣሉ፤” ይላል (ራዕይ 21፡23–24)። በመንፈሳዊ አነጋገር፤ እግዚአብሔር ሰዎችን “በሚያስደንቅ ብርሃን” ውስጥ እንዲኖሩ ከጨለማ እንዲወጡ ይጠራቸዋል። ኢሳይያስ 43፡1–7፣ 16–21፣ እና 1 ጴጥሮስ 2፡9–10 ይመልከቱ።

[12] መልካሙንና ክፉውን የሚለየው እግዚአብሔር ነው። ስለ አንድ ነገር “መልካም” የሚል አስተያየት በዘፍጥረት 1 ላይ ሰባት የተለያዩ ጊዜያት መደጋገሙ ደግሞ ጠቃሚ ነው። ሰባት ቁጥር በዘፍጥረት ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ደግሞም ቀደም ሲል እንደተገለፀው በቁጥር 1 (በዕብራይስጥ) ሰባት ቃላት አሉ። ደግሞም ሰባት ጊዜ ያህል “ያ መልካም እንደሆነ” የሚሉ ሐረጎች አሉ። በተጨማሪም ፍጥረት የተፈጥረባቸው ሰባት ቀኖች አሉ። የሰባት ቁጥር መደጋገም ምንባቡን በቀላሉ ማስታወስ እንዲቻል አድርጎታል። እንደዚሁም የሰባት ቁጥር መደጋገም አንባቢው እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን እንዳረፈ እንዲያስታውስ ይረዳዋል። ይህም በሰዎች ውስጥ ለራሳቸው እረፍትን ለማግኘት ፍላጎትን መፍጠር ይኖርበታል። ይህም እረፍት የሚመጣው በኢየሱስ በኩል ብቻ ነው ( ማቴዎስ 11፡28 እና ዕብራውያን 3–4 ይመልከቱ)።

[13] የእግሊዝኛው ESV መጽሕፍ ቅዱስ “አንድ ቀን” ወይም በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ደግሞ “የመጀመሪያው ቀን” የሚለው ሲተረጎም “ዘ” የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል በመጨመር ለየት በማድረግ የታወቀ ቀን እንደሆነ በማስገንዘብ ተርጉሞታል (በተጨማሪ NIV 2011 እኤአ ዕትም፣ NLT፣ NET፣ HCSB ይመልከቱ) ነገር ግን የዕብራይስጡ ደግሞ ይህ ልዩነት ግልጽ ሳያደርግ “ “የመጀመሪያ ቀን” ይላል።ይህ በዕብራይስጥና በእነዚህ እንግሊዝኛ ትርጉሞች መካከል ያለው ልዩነት በቀን 2፣ 3፣ 4፣ እና 5 ውስጥም ሊስተዋል ይችላል። **ነገር ግን በእብራይስጡ እስከ ስድስተኛው ቀን ይህን ልዩነት ግልጽ ተደርጎ አልተጻፈም** (ዘፍጥረት 1፡31 ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ በዕብራይስጡ ስድስተኛው ቀን ግን ለብቻው የታወቀ ቀን እንደሆነ በማስረገጥ “ስድስተኛውን ቀን”ብሎ ገልጾታል። ከ 1–5 ያሉትን ቀናት እንደ ተራ ቀናት ሲገለጽ ስድስተኛው ቀን ግን ለየት ያለ ቀን እንድሆነ ተመልክቷል ይህም ሆነ ተብሎ የተደረገ ይመስላል። ጸሐፊው በስድስተኛው ቀን ያተኮረበት ዋናው ምክንያት ሊሆን የሚችለው – እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን በመልኩና እንደ ምሳሌው ሰዎችን በመፍጠር የርሱን መልክና ምሳሌ ወደ ምድር ሁሉ ለመውሰድ ስለፈለገ ይሆናል። ሌላው ደግሞ ስድስተኛው ቀን የታወቀ ቀን እንዲሆን አድርጎ የጻፈበት ምክንያት ሰዎች በሁሉም ቦታ ለእግዚአብሔር ክብርን የማምጣት ኃላፊነት የተጣለባቸው በመሆናቸው የፍጥረት ከፍተኛ ቦታ መሆናቸውን እንዲያመለክት ተፈልጎም ይሆናል። ሰዎች እንዴት አስፈላጊ እንደሆኑ የበለጠ ለመርዳት መዝሙር 8ን ይመልከቱ።

[14] “ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ” ይህ ስለ 24 ሰዓት ጊዜ ለመናገር ያልተለመደ መንገድ ነው። በተለምዶ ሰዎች አንድ ቀን ለመግለጽ ሲፈልጉ ከጠዋት ጀምሮ እስከ ምሽት ድርስ ያለውን ብቻ ነው ሚቆጥሩት። በዚህ በተለመደ አገላለጽ ጨለማ የቀኑ መደምደሚያ ነው። እዚህ ጋ ጨለማው ብርሃንን ያሸነፈ ይመስላል። ነገር ግን ዘፍጥረት 1፡1–2:3 መሠረት ደግሞ

6 እግዚአብሔርም: – በውኆች መካከል ጠፈር ይሁን፤ በውኃና በውኃ መካከልም ይከፈል አለ።

7 እግዚአሔርም ጠፈርን አድረገ፤ ከጠፈር በታችና ከጠፈር በላይ ያሉትንም ውኆች ለየ፤ እንዲሁም ሆነ።

8 እግዚአብሔር ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፤ ሁለተኛ ቀን።

9 እግዚአብሔርም: – ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰበሰብ የብሱም ይገለጥ አለ፤[15]

እንዲሁም ሆነ።

10 እግዚአብሔርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው፤ የውኃ መከማቻውንም ባሕር አለው፤ እግዚአብሔርም ያ

መልካም እንደ ሆነ አየ።[16]

11 እግዚአብሔርም: – ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን

የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ፤ እንዲሁም ሆነ።

12 ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ

አበቀለች። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ።

13 ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፤ ሦስተኛ ቀን።[17]

---

ፍጹም ተቃራኒ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ግን በምሽት ይጀምርና በጠዋት ይጨርሳል ይህም ደግሞ የጠዋቱን ኀላ አድርጎ የሚገልጽ ይመስላል። እግዚአብሔር ደግሞ ባለማቋረጥ በጨለማ ላይ ያለውን ድል አጉልቶ ያሳያል። ፀሐይ በወጣች ጊዜ ሁሉ በጨለማ ውስጥ ብርሃኑን የሚያበራ እግዚአብሔር መሆኑን እንረዳለን። እንደዚሁም ደግሞ ከፀሐይ መውጣት ጋር በተያያዘ የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔር በኃጢአትና በዝብርቅርቅ ላይ አሸናፊ መሆኑን እንዲያስታውሱ ያደርጋል።

ከዚህ ከዘፍጥረት ክፍል ጋር በማያያዝ ትንቢተ ኤርሚያስ 33፡19–22 ማጥናት አስደሳች ነገር ነው። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ እግዚአብሔር በቀንና በሌሊት ስላደርገው ቃል ኪዳን ይናግራል። ይህም ማለት ቀንና ሌሊትን መፍጠር ብቻ ሳይሆን ከእነሱ ጋር ጠንካራ ስምምነትም አድርጓል። የዚህ ስምምነት ውሎች በዘፍጥረት 1 ላይ አልተጠቀሱም። ይሁን እንጂ፣ በሰማይና በምድር ዘመን ሁሉ ቀንና ሌሊት በተወሰነላቸው ጊዜ እንዲመጡና እንዲሄዱ ያደረገው ስምምነት ይመስላል። የክርስቶስ መምጣት አስመልክቶ ለሕዝቡ የሰጣቸው ተስፋዎች ምን ያህል እርግጠኞች እንደሆኑ ለማሳየት ይህን ቃል ኪዳን ከቀንና ከሌሊት ጋር አድርጓል። ስለዚህ የቀንና የሌሊት ያለማቋረጥ በመፈራረቅ መቆየታቸው እግዚአብሔር የገባቸውን ተስፋዎች ሁሉ እንደሚፈጽም፤ በተለይም በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚገዛ ዘላለማዊ ንጉሥ በእርግጥ እንደሚመጣ የገባውን ቃል ለሰዎች ለማስታወስ ያገለግላል።

[15] እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ለመኖር ምቹ ቦታን ፈጥሯል። ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ዋና ክፍል ነው። ክርስቶስ በወንጌል ውስጥ ሐዋሪያትን ከባሕር ማዕበል ወደ ደረቅ ምድር ማምጣቱ ትልቅ ትርጉም አለው።

[16] በሰዋዊ አስተሳሰብ ሰዎች መልካም የሆነውን ይወስናሉ። ነገር ግን እነዚህ የመልካም ነገር ትርጓሜዎች በጊዜ ሂድት ሊለወጡ እና በተለያዩ ባህሎችም የተለያየ ስያሜ ሊኖራችው ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን መልካም የሆነውን የሚወስነው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ያስተምራል። እግዚአብሔር ደግሞም ክፉ የሆነውንም ይወስናል። ከእግዚአብሔር የሆኑ ትርጉሞች (ፍቺዎች) ምን ጊዜም እውነት ናቸው ደግሞም በጊዜ ሂደት አይለወጡም። አሁንም “ያ መልካም እንደ ሆነ አየ” የሚለው ሐረግ በዘፍጥረት 1:1–2:3 ሰባት ጊዜ ተደጋግሟል።

[17] በሶስተኛው ቀን ዘሮች ሙብቀላቸው ደግሞ አስፈላጊ ነገር ነው። ይህም በሦስተኛው ቀን አዲስ ሕይወት እንደሚመጣ እንድናይ የሚረዳ የመጀመሪያው ፍንጭ ነው። በመሆኑም ከመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ጀምሮ፣ በሦስተኛው ቀን የክርስቶስ መሞትና መነሣት በተመለከተ ለወንጌል መልዕክት እውቅና እንድንሰጥ ያዘጋጀናል። በብሉይ ኪዳን በመላው፣ በሦስተኛው ቀን ጉልህ ክንውኖች ሲከናወኑ ይስተዋላል። ይህም ለመጨረሻው ሦስተኛ ቀን አንባቢዎችን ያዘጋጃል።

14 እግዚአብሔርም አለ: – ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ፤ ለምልክቶች፣
ለዘመኖች፣ ለዕለታት፣ ለዓመታትም ይሁኑ፤
15 በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር ብርሃናት ይሁኑ፤[18] እንዲሁም ሆነ።
16 እግዚአብሔርም ሁለት ታላላቆች ብርሃናትን አደረገ፤ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሠለጥን[19] ትንሹም
ብርሃን በሌሊት እንዲሠለጥን ከዋክብትንም ደግሞ አደረገ።[20]
17 እግዚአብሔርም በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር አኖራቸው፤
18 በቀንም በሌሊትም እንዲሰለጥኑ ብርሃንና ጨለማንም እንዲለዩ፤ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ
አየ።
19 ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ፤ አራተኛ ቀን።
20 እግዚአብሔርም አለ: – ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ
ጠፈር በታች ይብረሩ።
21 እግዚአብሔርም ታላላቆች አንበሪዎችን፤ ውኃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኘቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹን ሕያዋን
ፍጥረታት ሁሉ፤ እንደ ወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ሁሉ ፈጠረ፤ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ
አየ።
22 እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው።[21] ብዙ ተባዙም የባሕርንም ውኃ ሙሉአት፤ ወፎችም
በምድር ላይ ይብዙ።
23 ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አምስተኛ ቀን።

---

[18] ከጥንት ጀምሮ ሰዎች ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ያመልኩ ነበር። እዚህ ላይ እንደ ምልክት ሆነው እንዲያገለግሉ እና "በምድር ላይ ብርሃን እንዲሰጡ" እንደተፈጠሩ እናያለን። መዝሙረኛውም በመዝሙር 8 ሲጽፍ ስለ ፀሐይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብት እያሰበ ነበር።

[19] በዚህ ክፍል ስንመለከት "ፀሐይ" የሚለው ስም ጥቅም ላይ አልዋለም። ነገር ግን ፀሐይን "ትልቁ ብርሃን" ብሎ ይገልጸዋል። የዚህ መጽሐፍ የመጀምሪያ አንባቢዎች፤ ሰዎች ፀሐይን ከሚያመልኩበት ከግብፅ መውጣታቸው በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡ ፀሐይ በራሱ አምላክ እንደ ሆነ እንዳያስቡ የፈለገ ይመስላል። ምክንያቱም የተፈጠረ ነገር ነውና። ለዚህም ሊሆን ይችላል እዚህ ጋ በመደበኛ ስሙ ያልተጠራው።

[20] ፀሐይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብት መመለክ የለባቸውም። የተፈጠሩት በምድር ላይ ለሚኖሩት ጥቅም ነው። ይህ ማለት ለሰዎች ብርሃን ለመስጠት ብቻ አይደለም። ነገር ግን ፀሐይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብት አንዱ ምክንያት የእግዚአብሔርን ኃይል ባለማቋረጥ እንድናስብ ታቅዶም ነው። ዘዳግም 4:19፤ ኢዮብ 9:7፣ 22:12፣ 25:5፣ 38:31–33፤ መዝሙር 8:3፣ 147:4፤ ኢሳይያስ 40:26፣ 45:12 እና ኤርሚያስ 31:35 ይመልከቱ። ደግሞም ከዋክብቶች ለሰዎች የአብርሃምን ዘሮች ቁጥር ለማስታውስ ያገለግላሉ፤ ዘፍጥረት 15:5–6 ይመልከቱ።

[21] የእግዚአብሔር ቃል በእነርሱ ላይ በረከትን አመጣ። ስለዚህ የእግዚአብሔር ንግግር ፍጥረቱ ያዘዘውን እንዲፈጽም ነገሮች ደግሞ እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል። ይህ በዘፍጥረት 1:28 ላይ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተናገረውን ቃል ስንመለከት ምን ያህል ተጽእኖ ሊፈጥር እንደሚችል መገመት አያዳግትም። ከበረከቱ የተነሣም ፍሬያማ መሆንና መባዛት እንችላለን።

24 እግዚአብሔርም አለ: – ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ፤ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር
አራዊትንም እንደ ወገኑ ታውጣ፤ እንዲሁም ሆነ።
25 እግዚአብሔርም የምድር አራዊትን እንደ ወገኑ አደርገ፤ እንስሳውንም እንደ ወገኑ፤ የመሬት
ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ፤ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።[22]

[22] እነዚህ ፍጥረታት ምድርን እንዲሞሉ ወይም ደስታን በማምጣት ሰዎችን እንዲያዝናኑ ብቻ አልተፈጠሩም (ምንም እንኳን ሁለቱንም እንዲያደርጉ የታሰበ ቢሆንም ማለት ነው)። ነገር ግን እነዚህ ፍጥረታት የተፈጠሩት ከራሳቸው በላይ የሆነን ነገር ለመጠቆም ነው። ይህም በአጽናፈ አለሙ ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ እንደሚያደርገው፤ እነዚህም ፍጥረታትም የተፈጠሩት የእግዚአብሔርን ውዳሴ ለመምጣት ነው (መዝሙር 148 ይመልከቱ)። የእነዚህ ፍጥራታት መኖር እግዚአብሔር ምን ያህል ታላቅና ከሁሉ በላይ እንደሆነ ምስክር ነው። መላዕክቱ ለእግዚአብሔር ፍጥረት የሰጡት ምላሽ ለዚህ እንደ ምሳሌ ሊታይ ይችላል። እንደዚሁም የእነሱ ምላሽ ደግሞ የኛም ምላሽ ሊሆን ይገባል! ኢዮብ 38፡7 እንደ ሚያስረዳን እግዚአብሔር ምድርን ሲፈጥር ሲያዩ “የእግዚአብሔር ልጆች በደስታ ዕልል አሉ” ይላል። እንደገና እዚህም ጋ ሰማይና ምድር ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚያቀርቡበት ቤተ መቅደስ እንደሆኑ እንመለከታለን።

26 እግዚአብሔርም አለ: – ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን[23] እንፍጠር፤[24] የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።[25]

---

[23] በቁጥር 26 ላይ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ሁሉንም ነገር ሲፈጠር ከሚጠቀምባቸው ቃላት የተለየ ነው። ይህም ቢያንስ በሁለት መንገድ ይለያል። **በመጀመሪያ**፤ እግዚአብሔር ስለ ሰዎች አፍጣጠር የተናገረው ቃል የተለየ ነው፤ ምክንያቱም ግለሰባዊ ስለሆነ። ነገር ግን ሌላውን ፍጥረት ለመፍጠር የተጠቀመበት ቃል ፍጹም ግላዊ ያልሆኑ ቃላቶች ናቸው። ሌሎቹ ሲፈጥር "ብርሃን ይሁን" ወይም "ጠፈር ይሁን" ይላል። "ይሁን" የሚለው ቃል ሆን ተብሎ የተፈጠሩት ነገሮች ከእግዚአብሔር ለማራቅ ይመስላል። ፍጥረት የሆነው በሥላሴ አማካይነት ነው፤ ነገረ ግን በተመሳሳይ ሁኔታ የፍጥረት ሂደት የሚገለጸው ሥላሴ በሆነ እግዚአብሔር እንዳልተሠራ ነው። ይሁን እንጂ "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" የሚለውን ቃል በመጠቀም እግዚአብሔር የሰዎችን አፈጣጠር ከራሱ ጋር አቆራኝቶታል። ስለዚህ ምርጫ የሚለውን ቃል አንባቢውን በፍጥረት ሂደት ውስጥ ሥላሴ ሰዎችን በመፍጠረ ሥራ ብቻ "እጆቹን አቆሽሿል"(እዚህ ጋ ሰውን ከምድር አፈር በግዚአብሔር እጆች እንደተበጀ ለመግለጽ ነው) ወደሚለው መደምደሚያ ይመራቸዋል። ይህ ደግሞ በእርግጥም ሰው በእግዚአብሔር እጆች ስለተሠራ ዋጋ ያለው መሆኑን ያሳያል! **በሁለተኛ ደረጃ** ደግሞ እግዚአብሔር እንደ ሥላሴ ስለ ሰዎች የተናገው ቃል ለሌሎች ፍጥረታት ከተናገረው ቃሉ ይለያል፤ ምክንያቱም ሰዎች ብቻ ናቸው በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠሩት! በሥላሴ መልክና አምሳል መፈጠር ማለት ግን ምን ማለት ነው? ይህ ማለት ሥላሴ የሆነው እግዚአብሔር በሆነ መንገድ በሰዎች ውስጥ ይገለጣል ማለት ነው። በሌላ መልኩ ይህ ማለት ሰዎች በአካል እግዚአብሔርን ይመስላሉ ማለት ደግሞ አይደለም፤ እግዚአብሔር መንፈስ ነውና። ነገር ግን ሰዎች በግልም ይሁን በኅብረት ሥላሴ የሆነ እግዚአብሔር ሕያው መገለጫዎች ሆነው ያገለግላሉ ማለት ነው። ልክ እንደ መስታወት በሆነ መንገድ የሥላሴን ባሕሪይ፣ መገኘቱ፣ ኃይሉን፣ ክብሩን እና ለተቀረው ማሕበረሰብ ውስጥ ላለው ለሰው ልጅና ለተቀረው አጽናፈ አለም የእርሱን ፍቅር ያንጸባርቃሉ (ኤፌሶን 3፡10 ይመልከቱ)!

[24] በቁጥር 26 ላይ "እንፍጠር" የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር እንደ ተገለጸ በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልጋል። በቁጥር አንድ (ኤሎሂም የሚለውን የዕብራይስጥ ስም በተመለከተ የግርጌ ማስታወሻውን ይመልከቱ)፣ በጣም ተፈጥሯዊ የሆነው የጽሑፉ ንባብ ሰዎች እግዚአብሔር ከአንድ በላይ ነው ወደሚል ድምዳሜ ይስባቸዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ብዙ (ሦስት) ነው እንደገና ደግሞ እሱ በተመሳሳይ ሁኔታም ነጠላ (አንድ) ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ነው። የሥላሴ ትምሕርት ከሐዋሪያት በኋላ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ያመጡት ፈጠራ አይደለም። ሥላሴ የሚለው ቃል እስከ ዘመነ ሐዋሪያት ድረስ ጥቅም ላይ ውሎ ላይሆን ቢችልም ቅሉ የሥላሴ እውነታ ግን ሁልጊዜ ነበር። የዚህ እውነታ ፍንጭ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ገና ከመጀመሪያ ምዕራፍ ጀምሮ ሊታይ ይችላል። በእርግጥ፣ ይህ እውነት በብሉይ ኪዳን ገፆች ውስጥ ቢያንስ በሆነ መልኩ ባይገለጥ በጣም የሚያስደንቅ ይሆናል፣ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ አስፈላጊው ገፀ ባሕሪ እግዚአብሔር ነውና። በብሉይ ኪዳን ከሥላሴ ጋር የተያያዙ ሌሎች ጠቃሚ ክፍሎች መዝሙር 45፡7 (ይህ በዕብራውያን 1፡9 ላይ ተጠቅሷል) እና ኢሳይያስ 9፡6 የመሳሰሉትን ደግሞ ያካትታል።

እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው በሥላሴ ውስጥ ባለው ጉድለት ምክንያት እንዳልሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው መወደድ ስለሚያስፈልገው ወይም ፍቅሩን የሚገልጽበት ቦታ ስለሚያስፈልገውም አይደለም። ጉዳዩ እንደዚህ ከሆነ፤ ይህ ማለት ደግሞ እግዚአብሔር ፍጹም አይደለም ማለት ነው፤ ምክንያቱም እሱን ወደ ፍጹምነት የሚያመጣው ሌላ ነገር ያስፈልገዋልና። ነገር ግን እግዚአብሔር ምንም ጉድለት የሌለበት ፍጹም አምላክ ነው። ምንም ከሌላ የሚፈልገው ነገር የለም። ፍቅር አያስፈገውም ምክንያቱም **እግዚአብሔር ፍቅር ነውና ፤ ደግሞም ፍቅር ገና ዓለም ሳይፈጠር ጀምሮ በሥላሴ አካላት መካከል ባለማቋረጥ ይገለጽ ነበር** (1 ዮሐንስ 4፡8 እና ዮሐንስ 17፡24 ይመልከቱ)። እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው ኅብረት ማድረግ ስለጎደለውም አይደለም። በሥላሴ ውስጥ ጥብቅ ኅብረት አለና።

[25] በግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ሰዎች ሁሉ ሰው መሆን ምን ማለት እንደሆነ መረዳት ዋና ነገር መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ሰው መሆን እግዚአብሔርን መምሰል ነው። እኛ ሥላሴ የሆነው እግዚአብሔር ነጸብራቅ ነንና። ነገር ግን እኛ የእግዚአብሔር አምሳል እንደ መሆናችን መጠን ምን ማድረግ አለብን? እንግዲህ የኛ ተግባር ምንድር ነው? የእግዚአብሔርን መልክ በትትክክል ለማንጸባረቅ ከፈለግን ምን ማድረግ አለብን? መልሱ የሚገኘው በቀጥር 26 ሁለተኛው አጋማሽ ላይ ነው። ይህ ጥቅስ ሰዎች እግዚአብሔር በፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ ላይ "የመግዛት" ሥልጣን እንደተሰጣቸው ይናገራል። ስለዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራቸው እግዚአብሔር እንደ ሚያስተዳድረውና እንደ ሚገዛውም እነርሱም እንዲሁ የማስተዳደርና የመግዛት ኃላፊነት እንዲቀበሉ ነው። ይሁን እንጂ ሰዎች (የእግዚአብሔርን ፍጥረት በምድር ላይ) ሊያስተዳድሩና ሊገዙ የሚችሉት ውስን በሆነ ሁኔታ ነው። እግዚአብሔር ግን የሚገዛውና የሚያስተዳድረው ወሰን በሌለው ሁኔታ (በሁሉም ሥፍራ) ነው። እንግዲህ ሰዎች የእግዚአብሔር ተባብሪዎች ናቸው። ከእርሱ ጋር እናስተዳድራልን

27

እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤

በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤

ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።[26]

---

እንገዛለን፤ ይህም በእርሱና ሁሌም ከእርሱ በታች ሆነን ነው። ለምሳሌ አዳምና ሔዋን “በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ መግዛት ነበረባቸው።” ይህ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው ምክንያቱም በዘፍጥረት 3፡1 ላይ ሰይጣን ተሳቢ ነገር ሆኖ ይታይ ነበር። ስለዚህ በዘፍጥረት 1:26 በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት አዳም በእባቡ ላይ መግዛት ነበረበት። በሌላ አባባል ደግሞ እግዚአብሔር በእባቡ ላይ ይገዛ የነበረው አዳም መለማመድ በነበረበት ሥልጣን በኩል ነበር። ይህ ግን አልሆነም። ይልቁንም እባቡ በአዳም ላይ ገዝቷል! ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ በእባቡ ላይ ሊሆን የተገባው አገዛዝ እንደፈለገው ተግባራዊ ሳይሆን ቀረ። ስለዚህም በአዳም የከሸፈ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ የመግዛት አስከፊ መዘዝ ምክንያት የሰው ልጅችና ፍጥረት ሁሉ ለጉዳት ተዳርገዋል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን የመጀመሪያው አዳም ከእባቡ ጋር በተገናኘ ጊዜ የእግዚአብሔርን የመግዛት ሥልጣን መግለጽ ቢያዳግተውም የኋለኛው አዳም (ኢየሱስ) ግን ይህን አድርጓል። ስለዚህ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል መፈጠር ማለት ምን እንደ ሚመስል ኢየሱስ አሳይቶናል። ኢየሱስ የተናገረውና ያደረገው ሁሉ የእግዚአብሔር አብ ልብ ነጸብራቅ ነበር (ዮሐንስ 5፡19 ይመልከቱ)! ኢየሱስ የእግዚአብሔር አስተዳደርና አገዛዝ በመግለጥ በምድር ላይ ነግሷል! ኢየሱስ ለሰይጣን ሆነ ከሰይጣንም ሥር ለሚሰሩ ሰዎች አልተገዛም። ይልቁንም እርሱ በእግዚአብሔር ቃል ገዛቸው (ማቴዎስ 4፡1–11 ይመልከቱ)። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መልክ ፈጽሞ በማንጸባረቁ “እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው” ተብሏል (ቆላስያስ 1:15 ይመልከቱ)። ኢየሱስ በእርሱ የሆኑትን ሁሉ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንዲገዙ ጠራቸው (ሉቃስ 10፡19፣ ማቴዎስ 28፡18–20፣ እና ራዕይ 12 ይመልከቱ)። በዘፍጥረት 1:26 ላይ ያለውን የግጥም ይዘት ለመረዳት መዝሙር 8 ን ይመልከቱ። ይህ መዝሙር በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ከኢየሱስና የኢየሱስ ከሆኑት ጋር የተያያዘ ነውና።

[26] ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያው ግጥም ነው። ግጥም ከፍ ያለ ንግግር ነው። ከሚጠቀምባቸው ልዩ ቃላቶች የተነሳ እና እነዚህንም ቃላት የተጠቀመበት መንገድ ከትረካ ለየት እንዲል አድርጎታል። እነዚህ ቃላቶች በተወሰነ መልኩ ለየት ባለ ሁኔታ የተደረደሩ ናቸው። የዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩ የሚባለውን ንድፍ ይከተላል። በዚህ መንገድ ብዙውን ጊዜ በተለይ እርስ በርስ የተያያዙ ሁለት መገላጫዎች አሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ልክ በዚህ ግጥም ውስጥ እንደሚታየው በተለይ ተያያዥነት ያላቸው ሦስት መገለጫዎች አሉ። በትይዩ የግጥም ንድፍ ሁለተኛው መገለጫ የመጀመሪያውን መገለጫ ሃሳብ ይደግማል። ይህ ሲሆን ዝም ብሎ አይደግመውም።ነገር ግን ብዙውን ጊዜ በሆነ መንገድ ይስለዋል ወይም ያጠነክረዋል።

ሰዎች ሲፈጠሩ በግጥም መታጀቡ ሌላው የሰው ልጅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ማሳያ ነው። ሌላው ፍጡር ወይም የፍጥረት ክፍል በተደረገበት ወቅት በግጥም አልተነገረም – ይህ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው! ይህ ልዩ ግጥም ሰዎችን የፈጠረው እግዚአብሔር መሆኑን ያጎላል። ይህ ግጥም ደግሞ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት ሦስት ጊዜ ተደጋግሟል። **አንድን ሰው ስናስብ በመጀመሪያ ደረጃ መሆን ያለበት እግዚአብሔር ያንን ሰው እንደፈጠረው ማስታውስ ነው።** ይህ ለእያንዳንዱ ከየዘሩ ለመጣ ሰው ሁሉ እውነት ነው። ይህ ግጥም እግዚአብሔር ሰዎችን በመልኩ እንደ ምሳሌው እንደ ፈጠረ አንጽዖት ይሰጣል። ይህ ግጥም መጀመሪያ ከተነገረ በኋላ እንደገና ቀጥሎ በሚገኘው ቁጥር መደጋገሙ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል። ሌላው ፍጥረት የእግዚአብሔርን ማንነት እንዲያንጸባርቅ ተደርጎ አልተሠራም። ሰዎችን ከሌላው በተለየ ሁኔታ ውድ ያደረጋቸው የእግዚአብሔርን መልክ እንዲያንጸባርቁ ተደርገው በመፈጠራቸው ነው። ሕይወት ከመፀነስ እስከ ዕለተ ሞት– ውድ የሚያደርገው ይህንን እውነት ነው። ለሕይወት ዋጋ እንሰጣለን ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ዋጋ እንሰጣለንና! ሰውን መግደል ወይም መጉዳት ማለት በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን መግደል ወይም ማበላሸት ማለት ነው። ስለ “ወንድና ሴት” የሚናገረው የግጥሙ ሦስተኛ አረፍተ ነገር አንፆት የሚሰጠው ሁሉም ሰዎች ማለትም ወንድም ሆነ ሴት የሚመለከት ነው። ከሁሉም ዘርና ጾታዎች (ወንድና ሴት) የተወጣጡ ሰዎች ሁሉ ትልቅ ዋጋ አላቸው ምክንያቱም ሁሉም ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ናቸውና። ሌላውን ሰው ስንጎዳ፤ የእግዚአብሔር መልክና አምሳል የያዘውን ነገር እየመታን ነው ማለት ነው! ሁሉም ሰዎች (የተወለዱም ሆኑ ያልተወለዱ፣ አካል ጉዳተኞችም ሆኑ ጤናማ፣ ወጣትም ሆኑ ሽማግሌዎች) በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ናቸው ስለዚህም ውድ ናቸው። ዘፍጥረት 9፡5–6 እግዚአብሔር የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ “በደም አፍሳሹ ሕይወት ላይ እንዲቆጠር የሚፈልገው” ለምን እንደሆነ ያብራራል።

28 እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው፡—[27] ብዙ ተባዙ፣ ምድርንም ሙሉአት፣ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።[28]

29 እግዚአብሔርም አለ፡— እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በምድር ፊት ሁሉ ላይ ዘሩን በእርሱ ያለውን ሐመልማል ሁሉ፣ የዛፍን ፍሬ የሚያፈራውንና ዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ።

30 ለምድርም አራዊት ሁሉ፣ ለሰማይ ወፎች ሁሉ፣ ሕያው ነፍስ ላላቸው ለምድር ተንቀሳቃሾችም ሁሉ የሚበቅለው ሐመልማል ሁሉ መብል ይሁንላቸው፤ እንዲሁም ሆነ።

31 እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ።[29] ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ፤ ስድስተኛ ቀን።

---

[27] በቁጥር 22 እንደተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል እዚህም ጋ የበረከት ቃል ይናገራል። በመሆኑም አዳምና ሔዋን ደግሞ ያዘዛቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ እግዚአብሔር በበረከት ንግግሩ ነገሮችን እንዲሠሩ አድርጓል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን የእግዚአብሒር በረከት እየረዳቸው ቢሆንም በዚህ ተግባር አልተሳካላቸውም! ሆኖም አዳምና ሔዋን ወድቀዋል ማለት እግዚአብሔር ዓላማውን ቀይሯል ማለት ደግሞ አይደለም። አሁንም ቢሆን ሰዎች የእሱን መልክና አምሳል ወደ ምድር ዳርቻ ሁሉ እንዲወስዱ ይፈልጋል። ይህ ደግሞ የሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። መዝሙር 8 እና ማቴዎስ 28፡18–20 ይመልከቱ።

[28] ሰዎች በምድር ላይ እንዲበዙ እንዲባዙና ምድርንም እንዲገዙአት ዘንድ የታዘዘበት ምክንያት ምናልባት የግዚአብሔርን መልክና አምሳል ምድርን ሁሉ ይሞላ ዘንድ ታቅዶ ሊሆን ይችላል። ይህ ማለት ደግሞ ይህን ማደርግ ቀላል ሥራ ነው ለማለት አይደለም። ይልቅስ ይህ ጥቅስ ጠንክሮ መሥራትን የሚያካትት ረጅም ሂደትን ይገልጻል። ነገር ግን እርግጥ ነው አዳምና ሔዋን ይህን ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ኃጢአት ሠርተዋል። እንዲያውም ከፍጡራን አንዱ የሆነው እባብ በላያቸው ላይ ገዛ (ዘፍጥረት 3 ይመልከቱ)! ይሁን እንጂ ኋለኛው አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአት ባለመሥራቱ እባቡ (ሰይጣን) በኢየሱስ ላይ ሊገዛ አልተቻለውም (ማርቆስ 1፡12–13 ይመልከቱ)! በሞቱና በትንሣኤው ምክንያት ኢየሱስ ይህን ተግባር መወጣት ጀምሯል። በቤተክርስቲያንም በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን አላማ መፈጸምን ቀጥሏል። ይህም አንድ ቀን ሙሉ በሙሉ ይጠናቀቃል። ኢየሱስ ፍሬያማ ነው ስለዚህ በእርሱ ያሉትን ሁሉ መልካም ፍሬ ያፈራሉና። የእግዚአብሔርን መልክና አምሳል በክርስቶስ በኩል በምድር ሁሉ ላይ እየተንሰራፋ ነውና። የክርስቶስ እና በእርሱ የሆኑትን ፍሬያማነት ለምሳሌ ዮሐንስ 15፡1–17 እና ገላትያ 5፡22–23 ይመልከቱ።

የሐዋሪያት ሥራ ጸሐፊ (የጳውሎስ ተጓዥ ጓደኛው ሉቃስ) በዘፍጥረት 1፡28 በግሪክኛ ትርጉም ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉትን የግሪክኛ ቃላት በመጠቀም ቤተ ክርስቲያን እንዴት እየበዛች እንዳለች የገለጸው በአጋጣሚ አልነበረም፤ (ይህ የብሉይ ኪዳን የግሪክ ትርጉም አንዳንዴ LXX–ሴፕቱጀንት ይባላል)። ሉቃስ አንባቢዎቹን በዘፍጥረት 1፡28 ላይ ባለው የእግዚአብሔር ትዕዛዝና በቤተ ክርስቲያን እድገት መካከል ያለውን ግኙኝነት እንዲረዱ የሚፈልግ ይመስላል! ለምሳሌ ያህል በሐዋሪያት ሥራ 6፡7 ላይ ሉቃስ እንዲህ ይላል፡- "የእግዚአብሔርም ቃል **እየሰፋ** ሄደ፤ በኢየሩሳሌምም የደቀመዛሙርት ቁጥር እጅግ **እየበዛ** ሄደ፤ ከካህናትም ብዙዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ።" እንደዚሁም በሐዋሪያት ሥራ 12፡24 ላይም ደግሞ ሉቃስ "የእግዚአብሔር ቃል ግን **ያድግና ይበዛ** ነበር" ይላል። ልክ እንደነዚህ ተመሳሳይ ቃላት በዘፍጥረት 1፡28 ላይም ተጠቅሰዋል! ሉቃስ የቤተ ክርስቲያንን እድገት በዘፍጥረት 1፡28 ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ፍጻሜ እንደሆነ አድርጎ በመመልከት፤ አንባቢዎቹም ደግሞ በሁለቱ መካከል ያለውን መዛመድ እንዲያስተውሉ ይፈልጋል (ለምሳሌ የሐዋሪያት ሥራ 1፡15፤ 2፡41፣ 4፡4፣ 6፡1፣ 6፡7፤ 8፡1–8፣ 8፡26–40፤ 9፡31 እና 10፡44–48 ይመልከቱ)። ስለዚህ ዛሬም ቢሆን አብያተ ክርስቲያናት ልክ እንደ እነዚህ የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ፍሬያማ እንዲሆኑና እንዲበዙ የታዘዙ መሆናቸውን ሊያስቡበት ይገባል። በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በመፍሰሱ የተነሳ ይህ እስከ ዛሬ ድረስ በምድር ላይ እየሆነ ነውና።

[29] በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሙሴ እግዚአብሔር ያደርገውን ነገር **ሁሉ** እንዳየና "እጅግም መልካም" መሆኑን እንደ ተረዳ ይናገራል። ከዚህ ጥቅስም በፊት ስድስት ጊዜ ያህል ሙሴ **አንድ የተለየ ነገር መልካም** እንደሆነ እግዚአብሔርም እንዳየ ለአንባቢዎቹ ገልጿል። አሁንም ለሰባተኛ ጊዜ ሙሴ እግዚአብሔር **ሁሉም** ነገር **በጣም ጥሩ** እንደሆነ እንዳየ ለአንባቢዎቹ ይናገራል። በእነዚህ ሁሉ ማጣቀሻዎች ውስጥ ስለ እግዚአብሔር የሠራው መልካምነት አንጽዖት የተሰጠው አንድ በጣም

## ዘፍጥረት 2

1 ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ።

2 እግዚአብሔርም የሠራው ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤[30] በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ
ዐረፈ።[31]

3 እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም፤ እግዚአብሔርም ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ
ሁሉ በእርሱ ዐርፎአልና።[32]

---

አስፈላጊ ነገር እንዳለ ግልጽ ነው። ይህን ደጋግመን እንድንሰማው የተፈለገው ለምንድር ነው? ይህም እግዚአብሔርን እና ቸርነት አብርው የሚሄዱ መሆናቸውን ለማሳየት ነው። ሊለያዩ አይችሉም (ያዕቆብ 1:17 ይመልከቱ)። ይህ እውነታ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግኑኝነት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይገባል። እግዚአብሔር በሕይወታችን የሚያከናውነውም ሥራ በመልካምነት እንደ ሚያጠናቅቀው እንድንተማመን ያስችለናልና (ሮሜ 8:28 ይመልከቱ)።

[30] የሚገርመው በግሪኩ (LXX– ሴፕቱጀንት ተብሎም ይታወቃል) እና ሌሎች ጥቂት ጥንታዊ ትርጉሞች እግዚአብሔር ሥራውን "በስድስተኛው ቀን" እንዳጠናቀቀ ይናገራሉ። ይህ ምናልባት ተርጓሚዎቹ በዕብራይስጡ እንደ ስህተት ያዩትን ነገር "ለማረም" ያድረጉት ሙከራ ሊሆን ይችላል።

[31] በቁጥር 2 እና 3 ላይ ሙሴ እግዚአብሔር "ያደረገውን ሥራ" እንዳጠናቀቀ ሦስት ጊዜ ያህል ተናግሯል! የሙሴ አጽናዖት መስጠት በዚህ እውነታ ላይ ነገሩ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲያውቁት በጣም አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል። በተጨማሪም ነገሩ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር ብቻውን ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ አንጻዖት ለመስጠት ታስቦም ነው።

[32] ሰባተኛው ቀን የተገለጸበት መንገድ ከሌሎቹ ቀናት ገለጻ በጣም የተለየ ነው። **በመጀመሪያ** ምንም ሥራ መሠራቱን አልተነገረም። **በሁለተኛ ደረጃ** "ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ" በሚል መደምደሚያ አልተቋጨም። ሁሉም ቀናት መጠናቀቃቸውን አንጽዖት በሚሰጥ መልኩ ነው የተገለጹት። ሰባተኛው ቀን ግን ቢያንስ ከጸሐፊው አንጻር መጨረሻ ያለው አይመስልም። የኋለኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ስለዚህ ቀን አስፈላጊነት አንስተው ሲናገሩ ይስተዋላል (መዝሙር 95፡ 7–11፤ ዕብራውያን 3 እና 4 ይመልከቱ)። **ሦስተኛ** ይህ ቀን ሌሎች ቀናት አያስከትልም። ከዚህ ከሰባተኛው ቀን በኋላ ሌላ ቀናት መኖራቸውን አልተገለጸምና። ነገር ግን ሁሉም ሌሎች ቀናት ተጨማሪ ቀን ያስከትላሉ። ሙሴ ሰባተኛውን ቀን ሌሎች ቀናትን በገለጸበት መንገድ ሳይሆን በዚህ መልኩ መግለጹን እንደመረጠ አንባቢው መረዳት አለበት። ግን ለምን ይህን አደረገ? ሙሴ አንባቢዎቹ (ማለትም የመጀመሪያዎቹን አንባቢዎች በእርግጠኛነት እነዚህን ቃላት ሲያነብላቸው በምድረ በዳ አላረፉም ነበር) ወደ እግዚአብሔር እረፍት እንዲገቡ ይፈልግ ይሆን? ይህን መሰሉ እረፍት ለእነሱም ይሁን ለእኛም በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው የሚገኘው። ማቴዎስ 11:28 እና ዘፀአት 33:14 ይመልከቱ።

የሚገርመው፤ በዚህ ምዕራፍ በተቀረው ክፍሉ አጽንዖት የሚሰጠው በሰው ልጅ ላይ ነው። በዘፍጥረት 3 ላይ የሰው ልጅ በሚሰራው ላይ አጽንዖት ተሰጥቶበታል። የሰው ልጅ ልክ እንደ እግዚአብሔር እንዲያርፍ የእርሱም ሥራ መጠናቀቅ ነበረበት። ታዲያ የሰንበት እረፍት አስፈላጊነት ምን ነበር? የተጠናቀቀውን የእግዚአብሔር ሥራ ሳምንታዊ ማሳሰቢያ ነበር። የሰው ልጅ አሁንም የሚሠራው ሥራ እንዳለበት እንደዚሁም ደግሞ እንደ እግዚአብሔርም ሥራውን መጨረስ እንዳለበት ሳምንታዊ ማሳሰቢያ ነበር። ደግሞም የሰው ልጅም ወደ እግዚአብሔር እረፍት መግባት እንዳለበት ማሳሰቢያ ነበር። የሳምንት የእረፍት ቀን እግዚአብሔር ሥራውን እንደጨረሰ እና የሰው ልጅም ሥራውን መጨረስ እንዳለበት ማሳሰቢያ ነበር። በመሆኑም ሰዎች ወደ እግዚአብሔር እረፍት እንዲገቡና ቢያንስ ለአንድ ቀን እንኳን የእግዚአብሔርን እረፍት "እንዲያጣጥሙ" ሳምንታዊ ግብዣ ነበር።

ሰዎች ከተፈጠሩ ከሳምንት በኋላ ፍጥረታት ተፈጥረው ቢሆን ምንም ዋጋ የለውም ነበር። በጣም መሠረታዊ የሕይወት ዘይቤ ማለትም በእግዚአብሔር የተፈጠረው – የሥራ ሳምንት– እርሱን እንድናስታውስ እና የእግዚአብሔር እርፍት ደግሞ

## ዘፍጥረት 2፡4–25

ዘፍጥረት 1፡1–2:3 እና ዘፍጥረት 2፡4–25 ተመሳሳይ ናቸው። ሁለቱም ፍጥረት የተፈጠረበትን ሂደት ያካትታሉ። በሌላ መልኩ ደግሞ የተለያዩም ናቸው። በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች ማካከል ያሉትን ጥቂት ልዩነቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

1. **ዘፍጥረት 1፡1–2:3 እግዚአብሔር ሰምይንና ምድርን እነደፈጠረ ትልቅ ስዕል ለአንባቢው ይሰጣል።** እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከሩቅ ሲፈጥር አንባቤው ከሩቅ ሆኖ የሚያይ ይመስላል። እግዚአብሔር ሥራውን እንዴት እንደሚሠራ የሚያሳዩ የቅርብ ዝርዝሮች ሊታዩ አይችሉም። ምክንያቱም በቃሉ እንደሚፈጥር ግልጽ ነውና። ነገር ግን ለምሳሌ በፍጥረት ሥራ ሂድት ውስጥ “እጆቹ” ቆሸሸው እና “አፉም” በአዳም ላይ እፍ ሲልበት እያየን አይደለም። እደዚህ ዓይነት ዝርዝር ሁኔታ በዘፍጥረት 2፡4–25 ላይ እናገኛለን። በምድር ላይ ያሉ የተወሰኑ ቦታዎች በዘፍጥረት 1፡1–2:3 ውስጥ አልተጠቀሱም። ሁሉም ነገር ከሩቅ እና ከትልቅ ስዕል እይታ ነው ምንመለከተው። ሰዎች እንኳን በትልቁ ስዕል ተገልጸዋል። ስማቸው አልተጠቀሰም ፍላጎታቸውም አልተነገረም። **ይሁን እንጂ ዘፍጥረት 2፡4–25 ግን የቅርብ እይታ ነው።** አንባቢው በምድር ላይ ቆሞ እግዚአብሔር ከሰዎች እና ከሠራቸው ነገሮች ጋር በቅርበት ሲገናኝ የሚያይ ይመስላል።

2. **ዘፍጥረት 1፡1–2:3 በጣም የተዋቀረ ነው።** በአንድ ቀን የተገለጹት ሰባት የተለያዩ ቀናት ለሙሴ መቅደም ድግግሞሽ እንዲኖረው እና ሥርዓት ያለው እንዲሆን አድርጎለታል። ደግሞም የተለያዩ ሐረጎች ተደጋግመዋል (ማለትም፣ “እንዲህም ሆነ”፣ “እግዚአብሔርም አለ”፣ “እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ”)። ቁጥሮች እንደሚጨምሩ እንጠብቃለን፡– የመጀመሪያ ቀን፣ ሁለተኛ ቀን፣ሦስተኛ ቀን፣ ወዘተ። **ዘፍጥረት 2፡4–25 በጣም የተዋቀረ አይደለም።** በአንድ መልኩ የሚመስለው የበለጠ ምድራዊ መሆኑን ነው። ንድፉና አወቃቀሩን ለማየት አንባቢው በጣም ጠጋ በሎ እንደተመለከተ ይመስላል። በቅርበት የመመልከቱ ሂደት አንባቢው እግዚአብሔርን በአዲስ መንገድ እንዲያውቀው ያስችለዋል። ለምሳሌ እንዲህ በቅርበት የመመልከቱ ሂደት አንባቢው የእግዚአብሔር እጆች በሥራው ምክንያት ሲቆሸሹ “ማየት” እና ትንፋሹን ደግሞ “ሊሰማው” እንደሚችል ያህል ነው።

---

እንደሚያስፈልገን ለማሳሰብ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ አዲስ ሳምንት እግዚአብሔርን እንድናስብ ከማድረጉም በላይ እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን ዕቅድ አዲስ ማሳሰቢያም ነው።

3. ዘፍጥረት 1፡1–2:3 “የተለመደ” የእግዚአብሔር ስም ይጠቀማል– ኤሎሂም። በዘፍጥረት 1፡1–2:3 ላይ የእግዚአብሔር “የተለመደ” ስም መጠቀሙ ተገቢ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ጥቅሶች በዋነኝነት የሚናገሩት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ማካከል ስላላው ልዩ ግንኙነት አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደዚሁም ሰዎችን ሁሉ መፍጠሩን ያካትታሉ – እንደገና እነዚህ ነገሮች ከሩቅ እናያቸዋለን። በዘፍጥረት 1፡1–2:3 ላይ ኤሎሂም የሚለው ስም በሚያስደንቅ ሁኔታ 35 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። በእነዚህ የመጀመሪያ ጥቅሶች ላይ የተገለጸውን ሥራ በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ብቻ እንደተሠሩ ለማጉላት ሙሴ የእግዚአብሔርን ስም ደጋግሞ ይጠቅሳል። **ዘፍጥረት 2፡4–25 የእግዚአብብሔርን (የያህዌ) የቃል ኪዳን ስም ኤሎሂም ከሚለው ስም ጋር ያጣምራል። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ 11 ጊዜ ያህል ኤሎሂም የሚለው ስም ያህዌ ኤሎሂም በሚለው ስም ተተክቷል፤** (ይህ በእንግሊዝኛ ESV ተብሎ በሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ “ጌታ አምላክ” ተብሎ ተተርጉሟል በአዲሱ መደበኛ አማርኛ ትርጉም ደግሞ “እግዚአብሔር አምላክ” ተብሎ ተጽፏል)። በዘፍጥረት 2፡4–25 ላይ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ስም መጠቀሙ ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ወደ ሕዝቡ (አዳምና ሔዋን) ቀርቦ ከእነርሱ ጋር የጠበቀ ዝምድና መሥርቷልና። ስለዚህ የእግዚአብሔር ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጠራበት መንገድ እንኳን ስንመለከት ስለ እሱና እሱ ደግሞ ከሕዝቡ ጋር ያለውን ግኑኝነት እየተገነባ መሆኑን እንረዳለን። “ኤሎሂም” እና “ያህዌ” አንድ ላይ መሆናቸው ሙሴ የሚናገረውን የአማልክት ብዛት በተመለከት ግራ መጋባትን ያስወግዳል ማለት ነው። ማለትም ሙሴ የሚናገረው ስለ አንድ አምላክ ብቻ ነውና።

4. ዘፍጥረት 1፡1–2:3 የሚያተኩረው በመላው አጽናፈ ሰማይ ላይ ነው። **ዘፍጥረት 2፡4–25 ደግሞ የሚያተኩረው በአጽናፈ ዓለም ውስጥ በአንድ የተወሰነ ቦታ ማለትም በኤደን የአትክልት ስፍራ ላይ ነው።** ልክ ካሜራ በጣም አስፈላጊ በሆነ ነገር ላይ እንደሚያተኩር በተመሳሳይ መልኩ ዘፍጥረት 2፡4–25 የአንባቢውን ትኩረት በአጽናፈ ዓለም ውስጥ እጅግ አስፈላጊ በሆነው ስፍራ ማለትም እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር በሚኖርበት እና በሰዎች የሚመለክበት ቦታ ላይ ያተኩራል። በሚያሳዝን ሁኔታ በኃጢአታቸው ምክንያት አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ከዚህ ቦታ ተባረሩ። የመጽሐፍ ቅዱስ አጋማሹ ያህል እግዚአብሔር ሕዝቡ እንደገና ከእርሱ ጋር የሚኖርበትንና እርሱን የሚያመልክበትን ቦታ መልሶ የማቋቋም ታሪክ ላይ የሚያተኩር ነው። አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ በኋላ እግዚአብሔርና ሰዎች አብረው የሚሆኑበት አዲሱ ቦታ የማደሪያው ድንኳን ነበር። የማደሪያው ድንኳን በኤደን የሚገኘውን የአትክልት ቦታ ላይ የነበረውን አምልኮ ለማስታውስ የተነደፈ ይመስላል። ለምሳሌ ፍራፍሬዎች፣ ዛፎች፣ የከበሩ ድንጋዮች በማደሪያው  ውስጥ አልፎም ተርፎ በተጠለፉ ጨርቆችና በካህናት ልብስ ላይ ተደርገው ነበር። አምላኪው የማደሪያው ድንኳን ሲመለከት እሱ ወይም እሷ ስለ ኤደን የአትክልት ስፍራ

ያስታውሷቸው ነበር። በማደሪያው ድንኳን ውስጥ የነበሩ “ዕቃዎች” እንኳን በዘፍጥረት ውስጥ የሚገኙትን የመጀመሪያዎቹን ምዕራፎች ለሰዎች ለማስታውስ የታሰቡ ይመስላል። ለምሳሌ፡- ሰባት መብራቶች የነበሩት መቅረዙ የሕይወት ዛፍ ምልክት እንዲሆን የታሰበ ይመስላል፤(ያስታውሱ፤ ሰባት በተለይ ከፍጥረት ጋር የተቆራኘ ቁጥር መሆኑን መገንዘብ ያሻል) ። በመጨረሻም የማደሪያው ድንኳን በቤተ መቅደሱ ተተካ። እንደዚሁም ደግሞ ልክ እንደ ማድሪያውም ድንኳን መቅደሱም በኤደን ውስጥ የነበርውን አምልኮ ለማስታውስ እንዲረዱ በተዘጋጁ ነገሮች የተሞላ ነበር። ቤተ መቅድሱ ቋሚ የሆነ ይመስል ነበር። ሆኖም በኃጢአት ምክንያት ይህም ቤተ መቅደስ ፈርሷል። ይህ አሳዛኝ ነገር ነበር። እንግዲህ እግዚአብሔርና ሰዎች ዳግመኛ አብረው አይኖሩምን? ይሁን እንጂ እንደገና በኋላ አዲስ ቤተ መቅደስ ተሠራ። እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ የተሠራውም ቤተ መቅደስ ቢሆን ፍርሷል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ለመኖር ፈቃደኛ አልነበረም ማለት ደግሞ አይደለም። ምክንያቱም ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ በሰዎች “መካከል” መኖሪያውን አድርጓልና። ኢየሱስ ደግሞ እግዚአብሔርና ሰዎች የሚገናኙበት አዲሱ “ቦታ” ነውና (ዮሐንስ 1፡14 እና 2፡18–22 ይመልከቱ)። አሁን እግዚአብሔር ማደሪያ የሚሆነው ኢየሱስ የማዕዘን ራስ ድንጋይ በሆነበት መቅደስ ውስጥ ሁሉ ነው (ኤፌሶን 2፡19–22 ይመልከቱ)። በተመሳሳይ መልኩ በማደሪያው ድንኳንና በመቅድሱ ሰዎችን የአትክልት ስፍራውን እንዲያስታውሱ (በፍራፍሬ፣ በከበሩ ድንጋዮች፣ ወዘተ) ምስሎች ተሞልቶ እንደነበረ ሁሉ፤ ቤተክርስቲያንንም ለመግለጽም ጥቅም ላይ የዋለው ቋንቋ ስንመለከት በኤደን የነበረውን የአትክልት ስፍራ ሰዎች እንዲያስታውሱ የታሰበ በሚመስል መልኩ ነው (ማለትም በዮሐንስ 15 ላይ የአማኞች ፍሬያማነት፣ በገላትያ 5፡ 22–23 የተጠቀሱት የመንፈስ ፍሬ እና በራዕይ 2 እና 3 አብያተ ክርስቲያናት በመቅረዝ ተመስለው መገለጻቸው ልብ ይሏል)። በተመሳሳይ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢው በአትክልት ስፍራ ላይ እንዲያተኩር በማድረግ ይጀምርና እንደዚሁም ደግሞ በአትክልት ስፍራ ላይ እንዲያትኩር በማድረግ ደግሞ ያበቃል። በዘፍጥረት ውስጥ የነበረው የአትክልት ቦታ ትንሽ ነበር። በራዕይ ውስጥ ግን ግዙፍ ነው። በዘፍጥረት ውስጥ ሰዎች በአትክልቱ ስፍራ እንዲቆዩ አይፈቀድላቸውም ነበር። በራዕይ ውስጥ ግን ሰዎች ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚኖሩ ተገልጿል።

*****

(ከዚህ በታች የተገለጽው በዘፍጥረት 2፡4 ላይ ካለው ግጥም ጋር የተያያዘ ማስታወሻ ነው)

እግዚአብሔር አምላክ

ሰማይንና ምድርን ባደርገ ቀን፤
በተፈጠሩም ጊዜ የሰማይና የምድር ልደት ይህ ነው።

ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለተኛው ግጥም ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥሞች፤ የዚህ ግጥም ሁለት ክፍሎች (አንዳንድ ጊዜ "አጫጭር ጥቅሶች" ይባላሉ) ደግሞም እርስ በርሳቸው ትይዩ ናቸው። ሁለተኛው አጭር ጥቅስ እንደ መጀመሪያው ነው። ነገር ግን ትይዩነት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅኔዎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለው ዘይቤ ብቻ አይደለም። ምክንያቱም አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥሞች ሌሎች ቅጦችንም ያካትታሉ። በዚህም ግጥም ላይ የምናየው ይኸው ነው። በዚህ ግጥም ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ቃላቶች ሆን ተብሎ ቺዝም የሚባል ንድፍ ለማዘጋጀት የተዘጋጁ ይመስላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ትኩረትን በጣም አስፈላጊ ወደ ሆነ ነጥብ ለመሳብ ሲፈልጉ ቺዝሞችን ይጠቀማሉ። ቺዝም የሚለው ከግሪኩ ፊደላት ቺ ጋር የተገናኘ ነው (ለዚህም ነው ቺ-አዝም ተብሎ የሚታወቀው)። የግሪክ ፊደል ቺ የእንግሊዝኛው ፊደል X (ኤክስ) ይመስላል። በተመሳሳይ መልኩ የ X (ኤክስ) ግርጌ ትክክለኛ ቅጂ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ የ X (ኤክስ) የላይኛው ግማሽ ቅጂ ነው፤ በቺዝም ውስጥ ፀሐፊው ሆን ብሎ ንድፍ አዘጋጅቷል ስለዚህ የሥራው የመጀምሪያ አጋምሽ  ይገለበጣል በተቃራኒው ደግሞም በሥራው ሁለተኛም አጋማሽ ይገለበጣል።
በዘፍጥረት 2፡4 ላይ ያለውን ግጥም በድጋሚ ይመልከቱ፡

እግዚአብሔር አምላክ
ሰማይንና ምድርን ባደርገ ቀን፤
በተፈጠሩም ጊዜ የሰማይና የምድር ልደት ይህ ነው።

በዘፍጥረት 2፡4 ላይ ያለው የግጥም የመጀመሪያ አጋማሽ ሶስት ዋና ቃላትን በመጠቀም "የተገነባ" ነው።

ሀ. ሰማይንና

ለ. ምድር

ሐ. ተፈጠሩ

የግጥሙ ሁለተኛ ኢጋምሽ ተመሳሳይ ቃላትን (ወይም “ተፈጠሩ” በሚለው ሁኔታ ውስጥ በጣም ተመሳሳይ ቃል ይህም “አደረገ”) የሚለው ሲጠቀም ግን በተቃራኒ ቅደም ተከተል ይገልጸዋል።

ሐ. አደረገ

ለ. ምድር

ሀ. ሰማይንና

**“እግዚአብሔር አምላክ” የሚለው ስም በቺዝሙ ሁለት ግማሾች መካከል እንደሚገኝ ልብ ማለት ያስፈልጋል።** ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ የሚለው ስም ወደ ቺዝም ሲጨመር ንድፉ ይህን ይመስላል።

ሀ. ሰማይንና

ለ. ምድር

ሐ. ተፈጠሩ

መ. እግዚአብሔር አምላክ

ሐ. አደረገ

ለ. ምድር

ሀ. ሰማይንና

የቻይስቲክ ንድፍ ዋናው ነጥብ በቺዝሙ መካከል ይገኛል። ዋናው ነገር እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የፈጠረ መሆኑን መረዳት ነው። ነገር ግን ልብ ማለት ያለብን እዚህ ጋ የእግዚአብሔር የግል ስሙ እሱም – ያሕዌ ኤሎሂም የሚለውን ጥቅም ላይ መዋሉን ነው (ይህ በአብዛኛው አማርኛ ትርጉሞች እግዚአብሔር አምላክ ተብሎ ተጽፏል)። ይህም የሌሎች አማልክት አምላኪዎች ይህ ጥቅስ የሚናገረው ስለ አምላካችን ነው ብለው እንዳይናገሩ ይከለክላል። ሙሴ እየተናገረ ያለው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አምላክ ብቻ ነው። ሙሴ ያህዌ ኤሎሂም እና ያህዌ ኤሎሂም ብቻ ሁሉንም ነገር እደፈጠረ አስደናቂ አዋጅ ተናገረ። ለዚህም ነው የእግዚአብሔርን የግል ስሙ የተጠቀመው። ይህ ሰዎችን ወደ አምልኮ ሊመራ ይገባል። እንደዚሁም ደግሞ ሰዎችን አማልክት ያልሆኑትን እና ለመፍጠር (ወይም ለማዳን) ኃይል የሌላቸውን አማልክቶችን

እንዲተው ሊመራቸው ይገባል። የሚገርመው መዝሙረ ዳዊት 148፡13 ልክ የዚህ ቺዝም ሁለተኛ ኢጋምሽ የሰማይና የመድርን መደበኛ ስርአት መቀልበሱ አስገራሚ ነው። “የእግዚአብሔርን ስም ያመስግኑ፤ ስሙ ብቻውን ከፍ ከፍ ብሎአልና ምስጋናውም ከምድርና ከሰማይ በላይ ነውና የሕስቡንም ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል” (እዚህ ጋ አዲሱ መደበኛ ትርጉምና የድሮ ዕትም ያነጻጽሩ)። መዝሙረኛው የዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች እያሰበ ሊሆን ይችላል፤ በዚህ ግጥሙም ላይ “ ምድርና ሰማይ” የሚሉትን ቃላት ባልተለመደ ቅደም ተከተል ተጥቅሞም ሊሆንም ይችላል። መዝሙር 148 ፍጥረት ሁሉ ያህዌን እያመሰገነ ይናግራል። በመዝሙሩ ውስጥ ያለውን የመጨረሻው ቁጥር (ቁጥር 14) ያህዌ “የሕዝቡንም ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል” የሚለውን እውነታ ያስረግጣል። “ቀንዱ” የክርስቶስ ማጣቀሻ ነው –ምክንያቱም ክርስቶስ በመጨርሻው የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣልና (ዘፍጥረት 3፡15 ይመልከቱ)።

## ዘፍጥረት 2፡4–25[33]

4 እግዚአብሔር አምላክ[34] ሰማይንና ምድርን ባደረገ ቀን፤[35] በተፈጠሩም ጊዜ የሰማይና የምድር ልደት ይህ ነው።[36]

[33] ሙሴ ኦሪት ዘፍጥረትን በጻፈበት ወቅት በምዕራፍ አልከፋፈለውም ነበር። በምዕራፍ የመከፋፈሉ ሂደት እስከ ሐዋሪያት ዘመን ድረስ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ አልተጨመረም ነበር። ስለዚህም ነው አንዳንድ ጊዜ በዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ ከሚታተሙት የምዕራፎች ክፍሎች ለየት ያለ የቅዱሳን ማጻሕፍት ክፍል መከፋፈል ተገቢ ሊሆን የሚቻለው። እግዲህ በዚህም ክፍል ውስጥ ያለው ሁኔታ ይህንኑ ይመስላል። በዘፍጥረት 2 ውስጥ ያሉትን የመጀምሪያዎቹ ሦስት ቁጥሮች የዘፍጥረት 1 መደምደሚያ ሆነው ያገለግላሉ። በመጀመሪያዎቹ ቁጥሮች (ሰባተኛ ቀን) ያለው ርዕስ ከዘፍጥረት 1 (የመጀመሪያዎቹ ስድስት ቀናት) ርዕስ ጋር ስለሚሄድ ግልጽ ነው። እንደዚሁም የእግዚአብሔር ስም በ 2፡1–3 (ኤሎሂም) በዘፍትረት 1 ውስጥ ለእግዚአብሔር ስም ጥቅም ላይ የዋለው ስም ነው። ሆኖም ደግሞ በ 2፡4–24 ላይ ሌላ ስም (ያህዌ ኤሎሂም) የሚለው ጥቅም ላይ ውሏል። በቁጥር 4 ላይ የተገለጸው የስም ለውጥ አዲስ ክፍል መጀመሩን ከሚጠቁሙት ምልክቶች አንዱ ነው።

[34] በዚህ ጥቅስ ውስጥ ለእግዚአብሔር ጥቅም ላይ የዋለው ስም መለወጡን መመልከት ያስፈልጋል። እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የሚለው ስም በዘፍጥረት 1:1–2:3 ላይ ጥቅም ላይ መዋሉን ተጠቅሷል። ነገር ግን በ2፡4–3:24 ባለው ክፍል ሙሴ "እግዚአብሔር አምላክ" (ያህዌ ኤሎሂም) የሚለውን ስም መጠቀም ጀመረ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በአብዛኛው ያህዌ የሚለው ስም ኤሎሂም ከሚለው ስም ጋር ሳይጣመር ጥቅም ላይ ውሏል። እዚህ ጋ ግን ያህዌ እና ኤሎሂም የሚሉት ስሞች አያይዞ መግለጹ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ተያይዘው ባይገለጹ ኖሮ ምናልባት አንባቢው በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ሙሴ እየተናገረ ያለው ስለ አዲስና የተለየ አምላክ ነው ብሎ ሊያስብ ይችል ነበር። በመሆኑም ያህዌ ከኤሎሂም ጋር በማያያዙ ሙሴ በዘፍጥረት 1:1–2:3 ከገለፀው አምላክ ወይም እግዚአብሔር አዲስ እና የተለየ አምላክ አለመሆኑን አሳይቷል። ስለዚህ እዚህ ጋ የተገለጸው አምላክ በዘፍጥረት 1:1–2:3 ከተገለጸው ጋር አንድ አይነት አምላክ ነው ማለት ነው። በተጨማሪም አዲሱ የስም አገላለጽ እግዚአብሔር በአንድ ስም ብቻ ሊግለጽ ከሚችለው በላይ የባሕሪ ገፅታ እንዳለው ያሳያል። ይህ አዲስ ስም እግዚአብሔር ከሌሎች አማልክት የተለየ መሆኑንም ያስረዳል።

[35] ****** ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለተኛው ግጥም ነው። በመሆኑም በጣም ጠቃሚ ነውና የቅርበት ጥናት ይጥይቃል። ደግሞም የዚህ ግጥም ማብራሪያ በዚህ ቦታ ላይ ላማካተት በጣም ረጅም ነው። የዚህን ግጥም ዝርዝር ማብራሪያ ለማግኘት የዚህን ክፍል መግቢያ ተመልከት። ከዚህ ግጥም ጋር የተገናኙት ማስታወሻዎች በቀይ ኀልተው ተጽፈዋል።

[36] "ትውልድ ይህ ነው" (ወይም ይህን የመሰለ ሐረግ–በአንዳንድ እንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች "ልደት" የሚለው ቃል "ትውልድ" ተብሎ ተጽፏል) ፤ በዘፍጥረት ውስጥ በሙሉ ጥቅም ላይ ውሏል (በተጨማሪ 5፡1፣ 6፡9፣ 10፡1፣ 11፡10፣ 11፡ 27፣ 25፡12፣ 25፡19፣ 36፡1፣ 36፡9 እና 37፡ 2 ይመልከቱ) ። ይህ የመግቢያ ሀሳብ ነው። ማለትም ከእነዚህ ቃላት ተከታትለው ከሚመጡ ቃላት ጋር የሚሄዱ ናቸው ማለት ነው። በቁጥር 4 እና ቀጥሎ በሚመጣው መካከል ያለው ግኑኝነት ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም በሁለቱም በዕብራይስጥ (MT ወይም ማሶሬቲክ ጽሑፍ) እና የግሪኩ (LXX ወይም ሰፕቱጀንት) ጽሑፎች በቁጥር 5 የሚጀምረው "እና" በሚለው ቃል ነው። በአንዳንድ ዘይቤዎች ምክንያት በተለይም ESV የሚባለው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር 5 "እና" በሚለው ቃል አይጀምርም።

በዘፍጥረት 2፡4 ላይ "የምድር ልደት ይህ ነው" የሚሉት ቃላት ምናልባት የዘፍጥረት እውነተኛ መጀምሪያ ተደርጎ መታየት እንዳለበት ያመለክታል። ዘፍጥረት 1:1–2:3 መጽሐፉን በዐውደ-ጽሑፍ ያስቀመጠው መቅደም ነው።

በዘፍጥረት ውስጥ በሁሉም ምሳሌ፤ "እነዚህ የ . . ." የሚሉት ቃላት **ከሰዎች** ጋር የተገናኙ ናቸው (ማለትም "እነዚህ የያዕቆብ ትውልድ ናቸው")። ግን እነዚህ ቃላቶቹ ከአንድ **ቦታ** ጋር የተገናኙ ናቸው። እነዚህ ቃላቶች በዘፍጥረት ውስጥ በሌላ ቦታ ጥቅም ላይ የዋሉት የአንባቢውን ትኩረት ልዩ ትርጉም ያላቸውን **ሰዎች** ለመሳብ ስለሆነ እዚህ ጋር ተመሳሳይ መርህ መከተል አለበት፤ እነዚህ ቃላት የአንባቢውን ትኩረት ወደ ልዩ **ቦታ** ይስቡታልና። "ሰማያትና ምድር" የሚለውስ ትርጉም ምንድን

5 የሜዳ ቁጥቋጦ ሁሉ በምድር ላይ ገና አልነበረም፤ የሜዳውም ቡቃያ ሁሉ ገና አልበቀለም ነበር፤
እግዚአብሔር አምላክ በምድር ላይ ገና አላዘነበም ነበርና፤ ምድርንም የሚሰራባት ሰው አልነበረም።[37]
6 ነገር ግን ጉም ከምድር ትወጣ ነበር፤ የምድርንም ፊት ሁሉ ታጠጣ ነበር።
7 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወትን እስትንፋስን እፍ
አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።[38]

---

ነው? ትርጉሙ የሚመስለው እግዚአብሔር የሚመለክበትን ቦታ መፍጠሩን ለማምልከት ይመስላል። ሙሴ ስለ ዓለም አቀፍዊ ቤተ መቅደስ ታሪክ እየተናገረ ነው! ይህ በብዙ ቦታዎች ተረጋግጧል። ለምሳሌ ቆላስያስ 1፡15–20 እና ራእይ 21–22 ይመልከቱ።

*ተመሳሳይ ሐረግ* **ለሰዎችም** *ሆነ* **ለቦታ** *መጠቀማቸው እነዚህ ሁለቱ ነግሮች በተወሰነ መልኩ የተገናኙ መሆናቸውን ያመለክታል። ሁለቱም የታሪክ መስመሮች አሏቸው እና እነዚህ ታሪኮች ከአንድ ነገር ጋር ይዛመዳሉ። ሁለቱም ከአምልኮና ከአምልኮ ስፍራው ማለትም ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ጋር የተያያዙ ናቸው።*

*አንዳንድ ጊዜ በተለየ ሁኔታ "ትውልድ ይህ ነው" የሚለው ከመግቢያው ሐርግ ቅጥሎ ዝርዝር ይከተላል። በሌላ ጊዜ ደግሞ የመግቢያ ሐረጉ በታሪክ ይከተላል። እዚህ ያለው ሁኔታ ይህ ሲሆን ክፍሉም በ4፡26 ላይ ይጠናቀቃል። በዚህ ጥቅስ ላይ ሰዎች እግዚአብሔርን ሲያመልኩ እናያለን "በዚያን ጊዜም በእግዚአብሔር ስም መጠራት ተጀመረ" ይላልና። ስለዚህ የዚህ ክፍል ማጠቃለያ ዋና ነጥብ ስለ አምልኮ እንደሆነ ተጨማሪ ማረጋገጫ ሆኖ ያገላግላል ማለት ነው።*

*ሰፕቱጀንት (የጥንታዊ የግሪክ ትርጉም) "ይህ የሰማይና የምድር የትውልድ ሐረግ መጽሐፍ ነው" ይላል። ይህ የጥንታዊ የግሪክ ትርጉም (LXX ተብሎም ይጠራል) እንዴት እንደተጻፈ ልብ ማለት ያስፈልጋል ምክንያቱም ማቴዎስ 1፡1 የሚጀምረው በተመሳሳይ መንገድ ነውና። ማቴዎስ አንባቢዎቹ ስለ ኢየሱስ መምጣት ሲያነቡ ስለዚህ ጥቅስ እንዲያስቡ የሚፈልግ ይመስላል። በተጨማሪም ማቴዎስ አንባቢዎቹ የኢየሱስ መምጣት እንደ አዲስ ፍጥረት መጀመሪያ እንደሚያዩት ተስፋ እያደረገም ሳይሆን አይቀርም።*

[37] *እግዚአብሔር ምድርን በራሷ ፍሬያማ እንድትሆን አልፈጠረም። የእግዚአብሔር መልካም ምድር የእግዚአብሔርን ሥራ ይጠይቃል እግዚአብሔር (ዝናብ ይሰጣል) እና ሰው ደግሞ (በምድሩ ላይ ይሠራል)። እግዚአብሔር በሚፈጥራቸው ሰዎችና በሚፈጥረው ቦታ መካካለ ያለውን ግኑኝነት አስተውል። እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው መዝሙር 8 ይመልከቱ።*

[38] *ኢየሱስ ከሙታን ከተነሳ በኋላ ደቀመዛሙርቱ "መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ" "እፍ አላባቸው" ከሚለው ቃል ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ቋንቋ ጥቅም ላይ ውሏል (ዮሐንስ 20፡22 ይመልከቱ)። ሐዋሪያው ዮሐንስ ይህን ቋንቋ ሆን ብሎ የተጠቀመው በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ምክንያት አዲስ ዓይነት ሰዎች እየተፈጠሩ መሆኑን አንባቢዎቹ እንዲገነዘቡት ስለፈለገ ነው! ክርስቲያኖች የአዲሱ ፍጥረት አካል ናቸው (2 ቆሮንቶስ 5፡17 እንደዚሁም ደግሞ 1 ቆሮንቶስ 15፡42–49 ይመልከቱ)። ሐዋሪያው ጳውሎስ ደግሞ ይህንን የዘፍጥረት ጥቅስ ተጠቅሞ አዳምን ከኢየሱስ ጋር በማነጻጸር አማኞች ስለሚቀበሉት የትንሣኤ አካል ተናግሯል። ጳውሎስ ኢየሱስን "የኋለኛው አዳም" ሲል ጠርቶታል። እንደዚሁም በተመሳሳይ መንገድ "የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን፤ የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን።" ሲል ተናግሯል። በዚህ መንገድ አማኞች የትንሣኤ አካል እንደሚቀበሉ አስረግጧል።*

8 እግዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ[39] በዔደን ገነትን[40] ተከለ[41] የፈጠረውንም ሰው ከዚያው አኖረው።
9 እግዚአብሔር አምላክም ለማየት ደስ የሚያሰኘውን ለመብላትም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ ከምድር
አበቀለ፤[42] በገነትም መካከል የሕይወትን ዛፍ፣[43] መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውንም ዛፍ አበቀለ።[44]
10[45] ወንዝም ገነትን ያጠጣ ዘንድ ከኤደን ይወጣ ነበር፤ ከዚያም ለአራት ክፍል ይከፈል ነበር።

---

[39] ኤደን ከምስራቅ ጋር የተገናኘ መሆኑን አንባቢን የማደሪያው ድንኳን (የእግዚአብሔርን ቤት) ሊያስታውስ ይገባል። ምስራቅ በተለይም ከመገናኛው ድንኳንና ከመቅደሱ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ የማደሪያው ድንኳን እና ቤተ መቅደሱ የኤደን ትናንሽ ምስሎች መሆናቸውን የሚያሳይ አንዱ ማሳያ ነው።

[40] የአትክልት ስፍራው ኤደን አልነበረም። ይልቁንስ አትክልት ቦታው በኤደን ውስጥ ልዩ ቦታ ነው። ስለዚህ የአትክልት ቦታው በአንፃራዊነት ሲታይ በዚህ ጊዜ በተለይ ትልቅ አልነበረም። ነገር ግን አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሲጠብቁ ፍሬያማ ሲሆኑና ሲባዙ የአትክልት ቦታውም አብሯቸው እንዲያድግ የታቀደ ነበር። የአዳምና የሔዋን ዘሮች ምድርን እንደሞሉ የአትክልት ስፍራውም ምድርን መሙላት ነበረበት። ነገር ግን እንደ አለመታደል ሆኖ የመጀመሪያው አዳም የተሰጠውን ሥራ መፈጸም አልቻለም። በአለ መታዘዛቸውም ምክንያት አዳምና ሔዋን ከገነት ተባረሩ። የኋለኛው አዳም ኢየሱስ ግን ይህንን ተግባር እየፈጸመ ይገኛል። በኢየሱስም መታዘዝ የተነሳ የእግዚአብሔር ፍሬያማ የሆነው “አትክልት” ምድርን ለመሸፈን እየሰፋ ነው! አንድ ቀን ደግሞ የአትክልት ቦታው ሁሉንም ነገር ያጠቃልላል ራዕይ 21–22 ይመልከቱ።

[41] ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዘፍጥረት 2፡4–25 አንባቢው እዲረዳ የተደረገ ሲሆን አሁን ደግሞ እስቲ እግዚአብሔር በሚሰራበት ጊዜ “እንመልከተው” እዚህ ጋ በጭቃ ሲሰራ እና የአትክልት ቦታውንም ሲተክለው “እጆቹም እየቆሸሹ” ሲስሩ እንመለከታለን። ያህዌ ኤሎሂም ከዚህ የአትክልት ስፍራ ጋር በቅርበት እየተገናኘ ነበር ማለት ነው።

[42] ይህንን ከዘፍጥረት 3፡6 ጋር ማገናዘብ ይቻላል። በዘፍጥረት 3፡6 ላይ ሙሴ ሔዋን ዛፉ “ለመብላት ያማረ እንደሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ” እንዳየች ተናግሯል። ደግሞም “ለጥበብም መልካም እንደሆነ” አየች ይላል። እግዚአብሔር ዛፎቹን የፈጠረው ይህን ለማድረግ አልነበረም። ይህን ግን ከእባቡ የተማረችው ይመስላል። ለሰዎች ጥበብ ከዚህ ዛፍ አይደለም የመጣው። የሚገርመው ግን በምሳሌ 3፡18 ጥበብ ከሕይወት ዛፍ ጋር የተገናኘች እንጂ መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ ጋር አለመሆኑን ነው።

[43] የሕይወት ዛፍ በአትክልቱ መሃል ላይ ነው የነበረው። ይህ እውነታ የዚህን ዛፍ ትልቅ ጠቀሜታ ያሳያል። በዘፍጥረት 3፡3 መሰረት ይህ ደግሞ መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀው ዛፍ የሚገኝበት ቦታ ነው።

[44] እንግዲህ እነዚህ ሁለት ዛፎች የሁሉንም ሰዎች ሕይወት ለመወሰን በጣም ጠቃሚ ሚና ይጫወታሉ ማለት ነው። ነገር ግን በእነዚህ ዛፎች ላይ የተሰጠው አጭር ትኩረት ለአንባቢው (ይህ **ቅድመ ጥላ**) ይባላል፤ በዘፍጥረት 3 (እና በተቀረው የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍል) ስለሚሆነው ነገር ያዘጋጀዋልና። አዳማና ሔዋን መልካሙናን ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ በመብላታችው ምክንያት ከሕይወት ዛፍ እንድይበሉ ተከልክለዋል። የሕይወት ዛፍ ሕይወት ሰጪ ዛፍ ነው። ይህም በእርግጥ ጥሩ ዛፍ ነው። ነገር ግን መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውም ዛፍ ቢሆን መልካም ነው (ዘፍጥረት 1፡31 ይመልከቱ)። ዛፉን ግን አላግባብ መጠቀም ግን ክፉ ነው።

[45] በዚህ ጥቅስ ውስጥ ከወንዝ ጋር የተያያዙ አራት ጥቅሶች አሉ። ይህ ወንዝ በሙሴ ለተነገረው ታሪክ (እና በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ) ትልቅ ትርጉም እንዳለው የሚያሳይ ፍንጭ ነው። ወንዙ በአትክልቱ ውስጥ የት እነደ ነበረ ግልጽ ባይሆንም በመጽሐፉ ራሱ ከሕይወት ዛፍ እና መልካሙንና ክፉን ከሚያስታወቀው ዛፍ አጠገብ እንደሚገኝ ነው የተጻፈው። በአንድ ጥቅስ ብቻ የሚራራቁ ናቸው። ስለዚህም ወንዙና የሕይወት ዛፍ በተወሰነ መልኩ እርስ በርስ ተቀራርበው እንዲታዩ የታሰቡ ይመስላል። በሌላ አነጋገር **የሕይወት ዛፍና ወንዙ አብረው ይሄዳሉ ማለት ነው።** ሁለቱም በአትክልቱ ሥፍራ መሃል ይገኙ ነበር። በኋላ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ደራሲዎች በወንዝ (ወይም በጅረቶች) ውሃ ዳር ስለተተከለው ዛፍ መናገራቸው ጠቃሚ ነው (መዝሙር 1፡4፤ ሕዝቃኤል 47፡ 1–12 እና ራዕይ 22፡1–2 ይመልከቱ)። እነዚህ ምንባቦች ሁሉም እርስ በርስ የተያያዙ ከመሆናቸውም በላይ በዘፍጥረት 2 ውስጥ ካሉትም ጥቅሶች ጋር የተያያዙ ናቸው። ኢየሱስም ይህን ክፍል (እና ሕዝቅኤል 47፡9) በእርሱ ከሚያምን ሰው ውስጥ ስለሚፈልቀው የሕይወት ውኃ ወንዞች ሲናገር የሚያምለክት

11 የአንደኛው ወንዝ ስም ፊሶን ነው፤እርሱም ወርቅ የሚገኝበት የኤውላጥ ምድርን ይከብባል።

12 የዚያም ምድር ወርቅ ጥሩ ነው፤ ከዚያም ሉልና የከበረ ድንጋይ ይገኛል።[46]

13 የሁለተኛም ወንዝ ስም ግዮን ነው፤ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል።

14 የሦስተኛውም ወንዝ ስም ጤግሮስ ነው፤ እርሱም በአሦር ምሥራቅ የሚሄድ ነው። አራተኛውም ወንዝ ኤፍራጥስ ነው።

15 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔደን ገነት አኖረው።[47]

---

ይመስላል (ዮሐንስ 7፡38 ይመልከቱ)። ሐዋሪያው ዮሐንስ እንደተናገረው ኢየሱስ የተናገርው ስለ መንፍስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ በዘፍጥረት 2 ( እና መዝሙረ ዳዊት 1፣ ሕዝቅኤል 47፣ እና ራእይ 22) እንደተገለጸው ወንዝ ነው። ከአማኝ ውስጥ የሚፈልቀው መንፈስ ቅዱስ ለተጠማው አለም ሕይወትን ያመጣል።

ወንዙ በአትክልቱ ውስጥ ይጀምራል፤ ነገር ግን በአትክልቱ ውስጥ አይቆይም። ከአትክልቱ ስፍራ ወደ ሌላው አለም በተለያየ በአራት ማእዛናት ይፈሳልና። ይህም የአትክልቱ ቦታ መልካምነት ለአትክልቱ ስፍራ ብቻ የታሰበ እንዳልሆነ ያሳያል። ወደ ሌሎች ቦታዎችም መፍሰስ "ይፈለጋልና"። ይህ ለአዳምና ለሔዋን ትልቅ ማበረታቻ ሊሆን ይገባ ነበር። አትክልቱ በወቅቱ ከነበረው ዳርቻ በላይ እንዲስፋፋ ከተፈለገ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ነበረላቸው። ይህ ዛሬም በአማኞችም ላይ ያለ ነው። ማለትም በመንፍስ ቅዱስ አማካይነት ወደ ዓለም ሁሉ በድፍረት እንድንሄድ የሚያስፈልገንን ሁሉ አግኝተናል (የሐዋሪያት ሥራ 1፡8 ይመልከቱ)።

[46] ሙሴ በኤውላጥ ስላለው ወርቅና የከበሩ ድንጋዮች ለምን ማወቅ እንዳለባቸው ለአንባቢዎቹ በፍጹም አልተናገረም። በእርግጥ የሙሴ አናባቢዎች ወደ ኤውላጥ ሄደው ወርቅ ለማግኘት እንዲሞከሩ ማሳሰብ በእርግጠኝነት አይደለም። ይልቅስ ሙሴ አንባቢዎቹ እንዲያተኩሩ የሚፈልገው በኤደን ገነት እና እግዚአብሔርን በማምለክ ላይ እንጂ በባእድ አገርና በወርቅ አምልኮ ላይ አይደለም። ሆኖም በተመሳሳይ መልኩ አንባቢዎቹ በኤውላጥ ምድር ስላለው ወርቅ እና የከበሩ ድንጋዮች እንዲያውቁ ይፈልጋል! አስፈላጊነቱ ምናልባት ይህ በኤደን ገነትና በቤተ መቅደሱ ማካከል ያለው አንድ ተጨማሪ ግልጽ ግኑኝነት ነው (ወንዙን ማስታወስ ይገባል ማለት በሕዝቅኤል 47 ላይ ካለው ቤተመቅደስ ጋር የተገናኘ ነው)። ወርቅና የከበሩ ድንጋዮች የማደሪያው ድንኳን፣ የመቅድሱ የአገልግሎት እቃዎች እና የካህናቱ ልብስ ለማዘጋጀት ጉልህ ስፍራ ነበራቸው። በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ወርቅና የከበሩ ድንጋዮች በብዛት ይገኛሉ (ራዕይ 21 ይመልከቱ)። ምናልባት ወርቁና የከበሩ ድንጋዮች ከኤደን **ውጭ** መሆናቸውን ጠቃሚ ነው፤ ነገር ግን በራዕይ 21 ላይ ወርቁ እና የከበሩ ድንጋዮች በከተማው የአትክልት ስፍራ **ውስጥ** ናቸው። ይህ በኤደን የሚገኘው የአትክልት ቦታ ጥሩና ውድ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ለማካተት መስፋፋት ነበረበት ነገር ግን በራዕይ መጽሐፍ ላይ ያለውን የአትክልት ከተማ ሙሉ በሙሉ መስፋፋትዋን ለማመልከት ሊሆን ይችላል። በራዕይ መጽሐፍ የተነገረው የአትክልት ስፍራ ጥሩና ውድ የሆኑትን  ሁሉ ያካትታል። ይህንን የተፈጸመው ደግሞ በክርስቶስ ነው።

[47] የአትክልቱ ጤንነት ይመካ የነበረው በእግዚአብሔር ሥራ፣ መልካምነቱና ሞገስ ላይ ነበር። እደዚሁም ደግሞ በአዳም ታዛዥነት፣ ታማኝነት እና መበረታታት ላይ የተመሰረተ ነበር። በአትክልቱ ውስጥ እንዲያደርጋቸው በርካታ ስራዎችን ተሰጥተውት ነበር። የአትክልት ቦታው እንዲበለጽግ "ይሰራ" ዘንድ እናም ደግሞ የአትክልት ሥፍራው "እንድይረክስ" ይጠብቅ ዘንድ ተነግሮት ነበር። እግዲህ በዚህ መንገድ በአትክልቱ ወስጥ የሚኖሩትን ሁሉ ያበጅና **ይጠብቅ** ዘንድ ተነግሮት የነበረው። በዘፍጥረት 2፡15 ላይ "መጠበቅ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል በዘፍጥረት 3፡24 ላይ "ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ **ይጠብቅ** ዘንድ" በኤደን ገነት መግቢያ ላይ ያስቀመጠውንም ኪሩበኤል በተመለከተም ጥቅም ላይ ውሏል። በሌላ አነጋገር ኤደን ገነትን **መጠበቅ** የአዳም ሥራ ነበር። የኤደን ገነት ንጹሕ እንዲሆን መጠበቅ ነበረበት። እንደዚሁም ደግሞ በዘፍጥረት 2፡15 ላይ **"መጠበቅ"** ተብሎ የተትረጎመው ቃል በኋላ  በቤተመቅደስ ውስጥ ላሉ ካህናትም ጥቅም ላይ መዋሉን ልብ ማለት ያስፈልጋል (ለምሳሌ ዘኋልቁ 3፡10 እና 3፡38 ይመልከቱ)። ሙሴ፣ አሮንና ልጆቹ የእስራኤል ሕዝብ ለመጠበቅ ደጀሰላሙን **ይጠብቁ** ነበር። ማንኛውም እንግዳ የሆነ ሰው መቅድሱ ወዳለበት ከተጠጋ ይገደል ነበርና። ቀደም ሲል እነደተመለከትነው፤ በቤተመቅደሱና በኤደን የአትክልት ስፍራ መካከል ብዙ ተመሳሳይነት አለ። ልክ ካህናቱ ቤተ መቅደሱን "ከውጪ" ሃይላት **ይጠብቁ** እንደ ነበረው፤ አዳምም የኤድን ገነትን "ከውጪ" ሃይላት **መጠበቅ** ነበረበት። ነገር ግን በዘጥረት 3 ላይ እንደምንመለከትው አንድ የውጪ ሰው (እባቡ) ዘው ብሎ ወደ ገነት እንደመጣ እናነባለን። በዘኁልቁ ለካህናቱ በተሰጠው መመሪያ መሰረት ከሆነ አዳም እባቡን ለመግደል መሞከር ነበረበት ምክንያቱም

16 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡– ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤[48]

---

እባቡ በእግዚአብሔር ላይ ማማፅን እያበረታታ ነበርና። ይህንን በማድረግ ኤደን ገነትን **መጠበቅ** ነበረበት። ነገር ግን አዳም ይህን አላደረገም። በተቃራኒው ግን የአትክልት ቦታውን ከመጠበቅ ይልቅ እባቡ በአትክልቱ ውስጥ እንዲሠራ ፈቀደለት! አዳም ገነትን የ**መጠበቅ** የክህነት ሚናውን አልተውጣም። ነገር ግን የኋለኛው አዳም ጌታ ኢየሱስ በዚህ ሚናውን ተውጥቷል። እንዳውም ከሰይጣን ጋር ተዋግቶ ድል አድርጓል። ኢየሱስ በአሁኑ ጊዜም የእግዚአብሔርን ገነት (ቤተክርስቲያንን) በ**መጠበቅ** እየሰራ ነው! ስለዚህ *ሥራው* ስላልተጠናቀቀ እኛም ከዕርሱ ጋር *መሥራት* አለብን። ሰያጣን በክርስቶስ ተሸንፏል ይሁን እንጂ አሁንም በጣም አደገኛ ነው። እርሱ ሊገድል የሚችል ቁስል እንዳለው እባብ አሁንም የተጣለ ነው (ራዕይ 12 ይመልከቱ)። ክርስቲያኖች የክርስቶስን ድል እንደሚካፈሉ ሁሉ እኛም በ*መሥራት*ና የእግዚአብሔርንም ቦታ በ**መጠበቅ** *ሥራ* እንካፈላለን። ከእነዚህ ሁለት ተግባራት አንዳቸውም ችላ ሊባሉ አይገባም። በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትም ውስጥ ያሉትን ወንዶችና ሴቶች በእግዚአብሔር የተሰጣቸውን አደራ **እንዲጠብቁ** እና **እንዲሰሩ** ማድረግ ይገባል። አጥቢያ ቤተክርስቲያንን ከ**መጠበቅ** ጋር በተያያዘ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሽማግሌዎች ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። በሌላ መልኩ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለመጠበቅ ፈቃደኛ ካልሆኑ እንደ ሽማግሌ ሆነው ማገልገል የለባቸውም። በዚህ ጉዳይ በሐዋሪያት *ሥራ* 20፡17–38 ሐዋሪያው ጳውሎስ ለሽማግሌዎች የተናገረውን ይመልከቱ።

[48] እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በምንም መንገድ አይገድብም። በጣም ለጋስ ነውና። ነገር ግን ሰይጣን በአዳምና በሔዋን ላይ ባደርገው ፈተና ምክንያት የእግዚአብሔርን ቸርነትና ልግስና እንዲጠራጠሩ ለማድረግ ይጥራል (ዘፍጥረት 3፡1 ይመልከቱ)። እግዚአብሔርም መልካሙን እነደከለከላቸው አስመስሎ ሊያሳምን ይፈልጋል።

17 ነገር ግን መልካምንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤[49] ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።[50]

---

[49] መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀው ዛፍ በራሱ ክፉ ዛፍ አልነበረም። ዛፉ ልክ እንደሌላውም የእግዚአብሔር ፍጥረት "እጅግ በጣም መልካም" ነበር (ዘፍጥረት 1፡31 ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ ዛፉን አላግባብ መጠቀም ግን ክፉ ነበር። እግዚአብሔር በገነት ካሉት ዛፎች ሁሉ በተለይም ለአዳም የዚህን ዛፍ ፍሬ እንዲበላ አልፈቀደለትም ነበርና። የዚህ ዛፍ "ስጦታ" መልካም እና ክፉን የማስታወቅ (በፍሬው የተመሰለው) ለአዳም የተከለከለ ሆኖ መቆየት ነበረበት። በሌላ አነጋገር "መልካሙንና ክፉን ማወቅ" በአዳም ውስጥ እንዲኖር ገና አልተፈቀደም ነበርና። ነገር ግን መልካሙንና ክፉን ማወቅ በእግዚአብሔር ውስጥ ብቻ የነበረ ነገር ነበር (ዘፍጥረት 3፡22 ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል ይመልከቱ)። በ 2 ሳሙኤል 14፡17 ላይ "መልካሙንና ክፉ ማወቅ" የሚሉት ቃላት ጥቅም ላይ በዋሉበት መንገድ ላይ ተመስርተን ስንመለከት "መልካሙንና ክፉውን ማወቅ" ማለት "መልካሙንና ክፉውን የመወሰን" መንገድ እንደሆነ መረዳት እንችላለን። ጉዳዩ ደግሞ ይህ ከሆነ ፍርድ እንደ መስጠት ወይም መዳኘት እንደ ማለት ነው። በሌላ አነጋገር አዳም የዚህን ዛፍ ፍሬ ቢበላ የፍርድን ኃይል ከእግዚአብሔር ወስዶ በምትኩ እንደ እግዚአብሔር ትክክል ወይም ስህተት የሆነውን ለራሱ መወሰን መጀመሩ ምሳሌ ነው። እንግዲህ ለዚህ ነው ፍሬውን የበሉ "እንደ እግዚአብሔር" የተባሉት (ዘፍጥረት 3፡22)። አዳም ፍሬውን መብላት አልነበረበትም። እሱ (ከሔዋንና ከዘርማዘሩ ሁሉ ጋር) ይህን እንደ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ኃይል የሚሰጠውን ፍሬ ላለመብላት እንቢ በማለት ሕይወቱን በደስታ መምራትን መምረጥ ነበረበት። አዳምና ከእርሱ በኋላ የተፈጠሩ ሰዎች ሁሉ፣ ይልቁንም በእግዚአብሔር መልካም ፍርድ የሚታመኑ መሆን ነበረባቸው። የኋለኛው አዳም ክርስቶስ ግን ፍርድን ሁሉ ለእግዚአብሔር መስጠቱ አስፈላጊ ነገር ነው (ዮሐንስ 5፡22–27)።

በዘፍጥረት 2፡16–17 ላይ ትእዛዙ ለአዳም ብቻ የተሰጠ ነበር። ይህም ግልጽ ነገር ነው ማለትም በጽሁፉ ውስጥ በእነዚህ ጥቅሶች ሦስት ጊዜ ያህል "አንተ" የሚለውን ነጠላ ቃል ተጠቅሟልና፤ የሚገርመው ግን በጥንቱ ግሪክ አንተ የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር እንዲይዝ ተደርጎ በተለይም በቁጠር 17 ጥቅም ላይ ውሏል። ነገር ግን ሔዋን ከተፈጠረች በኋላ አዳም እርሷም ይህን ትዕዛዝ መታዘዝ እንደ ነበረባት ደጋግሞ ነግሯት ሳይሆን አይቀርም። ይህም ግልጽ ነው ምክንያቱም ሔዋን ይህንን ትዕዛዝ በዘፍጥረት 3፡3 ላይ ስትናግረው "አንተ" የሚለውን በብዙ ቁጥር ለውጣ ስትጠቀም እንመለከታለን። ስለዚህ በዘፍጥረት 3 ላይ ያለው የሔዋን ቃል የሚያመለክተው አዳም ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ትዕዛዝ እንደነገራትና ደግሞም ለእሱ የተሰጡት ተዛዛት ለሚስቱ እንደዚሁም ለዘሮቻቸውም እንደሚሆን ተረድቶ ነበር ማለት ነው።

ትእዛዙ ለአዳም ብቻ መነገሩ ተገቢ ነበር፤ ምክንያቱም የእሱ መታዘዝ (ወይም አለመታዘዝ) ከእርሱ በኋላ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የሚነካ ነበርና። እንደዚሁም በተመሳሳይ መልኩ የኋለኛው አዳም (ኢየሱስ) ታዛዥነትም ሰዎችን ሁሉ ይነካል (ሮሜ 5፡12–21 ይመልከቱ)።

[50] በዘፍጥረት 2፡11–12 የተገለጹት ወርቅና የከበሩ ድንጋዮች ውድ ሲሆኑ፤ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የበለጠ ውድ የሆነ የእግዚአብሔር መልካም ቃል ለሰው ልጆች ሁሉ ተነግሮ እንመለከታለን (መዝሙር 19፡9–11 ይመልከቱ)። ወርቅ ሰውን በሕይወት ማቆየት አይችልም። የግዚአብሔር ቃል ግን ለሰው ሕይወትን መስጠት ይችላል። በዚህ ክፍል የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል የጭካኔ ምልክት ተደርጎ መወሰድ የለበትም፤ ይልቅስ ለአዳምና ለሔዋን ተስፋን የሚሰጥ የጸጋ ስጦታ ነበር እንጂ። ሞትን የሚያመጣው ኃጢአት በተመለከተ ሮሜ 6፡23 እና ኤፌሶን 2፡1–3 ይመልከቱ።

18 እግዚአብሔር አምላክም አለ፡– ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤[51] የሚመቸውን[52] ረዳት[53] እንፍጠርለት።[54]

19 እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከመሬት አደርገ በምን ስም እንደሚጠራቸውም ያይ ዘንድ ወደ አዳም አማጣቸው፤ አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው ስሙ ያው ሆነ።[55]

---

[51] በዘፍጥረት 1፡1–2:3 ሰባት ጊዜ ያህል እግዚአብሔር አንድን ነገር መልካም እንደሆነ ተናግሯል። በዚህ ሥፍራ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ነው አንድን ነገር መልካም አይደለም ብሎ ሲናገር የምንመለከተው። ሰው ብቻውን መሆን የማይጠቅመው አንዱ ምክንያት ሰው የተፈጠረው  በእግዚአብሔር አምሳል በመሆኑ ነው (ዘፍጥረት 1፡26–28 ይመልከቱ)። ይህ ማለት ሰው የተፈጠረው ሕብረት እንዲያደርግ ጭምር ነው። ሌላው ሰው ብቻውን መሆን ጥሩ ያልሆነበት ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ለአዳም ከተሰጠው ተግባር ወይም ሃላፊነት አኳያም ነው። ማለትም የተሰጠው ሃላፊነት ብቻውን መሸከም ለሱ በጣም ብዙ ነው። ስለዚህም ነው እግዚአብሔር የሚመቸውን **ረዳት** እንፍጠርለት ያለው። ለሰው ልጅ የተሰጠውን ተግባር ለማጠናቀቅ እርዳታ ያስፈልገዋልና፤ ሰው በተሰጠው ሥራ እርዳታ ከሌለው መልካም ላይሆን ይችላልና።

[52] ረዳት የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም ግልጽ ነው ምክንያቱም በቁጥር 20 ላይ ተደግሟልና። በመደብኛ ትርጉሙ ረዳት ማለት ከሚረዳው ሰው የተለየ ተግባር የሚሰጠው ሰው ማለት አይደለም። ይልቁንም ረዳቱ በተመሳሳይ ተግባር የሚረዳ ማለት ነው። እንደገና ለመረዳት ያህል ማለት ለሰውዬው የረዳት እጦት “መልካም ያልሆነው” ለምንድር ነው? ቢያንስ ሁለት ምክንያቶች አሉ። **በመጀምሪያ** ሰውዬው ሕብረት እንደሚያስፈልገው አመላካች ነው። ብቻውን እንዲሆን አልተፍጠረምና። በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠሩ ፍጥረታት ከሌሎች በሥላሴ መልክ ከተፈጥሩ ተመሳሳይ ፍጥረታት ጋር ኅብረት ማድረግ የሰዎች ፍላጎትና ደስታም ነው። **በሁለተኛ** ደረጃ ያለ እርዳታ ሥራው ለሰውየው በጣም አስቸጋሪ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ለሰውየው የሚያደርገው ረዳት “ለእሱ ተስማሚ” ተብሎ መገለጹን ልብ ይበሉ። በዕብራይስጡ (አንዳንድ ጊዜ MT ተብሎ የሚጠራው) መጽሐፍ ቅዱስ “ፊትለፍት” ወይም “በተቃራኒው” ብሎ ይገልጸዋል። ሃሳቡ ከተረዳነው ሰው በተልየ ቦታ ማለት “ባለበት ሁኔታ የሚያግዝ” እናም ስለዚህ ሥራው በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የተለያዩ ስጦታዎችንና ችሎታዎችን የሚያመጣ እንደ ማለት ይመስላል። ይህ ደግሞ በእውነት ትልቅና ጠቃሚ ስጦታ ነው።

[53] **ረዳት** የሚለው ቃል የበታች የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ አያንጸባርቅም። እግዚአብሔር ከእሥራኤል ጋር ያለውን ግኑኙነት ለመግለጽ እንኳን ተመሳሳይ ቃል (ወይም ተዛማጅነት ያላቸውን የአንድ ቃል ዓይነቶች) መጠቀሙን ልብ ማለት ያስፈልጋል (ዘፍጥረት 49፡25፤ ዘፀአት 18፡4፤ ዘዳግም 33፡29፤ 1 ሳሙኤል 7፡12 ፤ ኢሳይያስ 41፡ 10፣ 41፡13፣ 44፡2፣ 49፡8፣ 50፡7 እና 50፡9 ይመልከቱ)። እንግዲህ እግዚአብሔር ከእሥራኤል ያላነሰ ከሆነ ሚስትም ከባልዋ አታንስም ማለት ነው። ይልቁንም ሰውየው አንድን ተግባር በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቅ የሚያስፈልገውን እርዳታ በመስጠት የምታግዝ ናት እንጂ።

[54] ሴፕቱጀንት (በድጋሚ ለማስታውስ ያህል፤ አንዳንድ ጊዜ LXX ተብሎ የሚታወቀው ጥንታዊ የግሪኩ ትርጉም) “እንፍጠር” ብሎ ይተረጉመዋል። ይህም ከዘፍጥረት 1፡26–28 ካለው ክፍል ጋር ተመሳሳይ ነው።

[55] እግዚአብሔር እንስሳትን ስለመፍጠሩና ወደ አዳም ማምጣቱ የሚናገሩት ጥቅሶች እግዚአብሔር ለሰው ረዳት በማድረጉ ታሪክ ውስጥ ተካትትዋል (ዘፍጥረት 2፡18–25)። እንስሳቱ የዚህ ልዩ ምንባብ ዋና ነጥብ አይደሉም። ነገር ግን የዚህ ክፍል ዋናው ነጥብ በሙሉ ረዳት የሚለውን ነው። ይህም ግልጽ ነው ምክንያቱም ምንባቡ የሚጀምረውና የሚጨርሰው ስለ ረዳት በማስተዋወቅ ጉዳይ ነው ( ዘፍጥረት 2፡18 እና ዘፍጥረት 2፡20–25 ያለውን ይመልከቱ)። እነዚህ ሁለት የመጽሐፉ መጨረሻ ክፍሎች በረዳት ላይ በማተኮራቸው ምክንያት አጠቃላይ ምንባቡም ስለ ሰውየው ረዳት እንደሆነ ያስገነዝባል፤ (ይህም በስነጽሑፍ አነጋገር እንደ ፓስታ ወረቀት የታሸገ የሚል እንድምታ አለው)።  የእንስሳቱ “ተግባር” በድራማው ውስጥ ላለው ለዋናው ገፀ ባሕሪ ማለት ለረዳቱ የበለጠ ትኩረት ለመሳብ ታስቦ  በድራማው ውስጥ የገቡ ደጋፊ ተዋናዮች ናቸው። ወደ ሰውየው የሚቀርቡት እንስሳት ረጅም መግለጫ የረዳትዋ መምጣት ያዘገየዋል። እኛ አንባቢዎች እግዚአብሔር ለአዳም ያቀደውን ልዩ ረዳት ከአዳም ጋር አብረን እንድንጠባበቅ እንገደዳለን ማለት ነው። እያንዳድንዱንም እንስሳ ከአዳም ጋር እንመለከታለን። በልዩነታቸውም እንገረማለን። ነገር ግን ልክ እንደ አዳም በቁጥር 18 ላይ የተገለጹት እንስሳት ረዳት ሊሆኑ ስለማይችሉ እነርሱን እንደ ረዳት አንቀበላቸውም። እንስሳቶቹ ደግሞ ምንም እንኳን ትልቅነታቸው የታወቀ ቢሆንም ነገር ግን ከእነርሱ የበለጠ ታላቅነት ለተጎናጸፈው ለሚመጣው ረዳት የላቀ ታላቅነት የበለጠ ትኩረት ይሰጣሉ። ሰውየው ወይም

20 አዳምም ለእንስሳት ሁሉ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ ለምድር አራዊትም ሁሉ ስም አወጣላቸው፤ ነገር ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር።[56]

21 እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት አንቀላፋም ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው።[57]

22 እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት።[58]

---

አዳም "ለእሱ ምቹ" የሆነ ያስፈልገዋል። ምንም እንኳን እንስሳቱ ታላቅና ልዩ ቢሆኑም ግን "ለእሱ ምቹ" አልነበሩም። ደግሞም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ አልነበሩም።

የሰው ልጅ የእንስሳትን ስም እንዲያወጣ ተፈቅዶለታል። ይህም እግዚአብሔር አምላክ በጸጋው በመድር ላይ ያለውን አገዛዝ ለሰው ልጆች  ማካፈሉን የሚሳይ ነው። እግዚአብሔር እንደገና በጣም ለጋስ ነው። በአዲስ ኪዳን የመጨረሻው አዳም ተብሎ የተጠራው ኢየሱስ ለነገሮች ስም መስጠቱ ጠቃሚ ነው (ለምሳሌ ዮሐንስ 1፡43 ይመልከቱ)።

[56] እንስሳት ዛሬም ቢሆን ለሰው ልጆች የተሰጠውን ታላቅ ተግባር ማስታወሻዎች ናቸው። እንስሳቱን ስንመለከት የተሰጠንን ተግባር ለመፈጸም ሊረዱን እንደማይችሉ መገመት እንችላለን። ይልቅስ እንስሳቱ ትዳርን ከፍ አድርገን እንድንመለከትና እግዚአብሔር ለሰዎች መጠናቀቅ ያለበትን ሥራ እንደሰጣቸው ማሳሰቢያ ናቸው። ይህንን ተግባር ለማጠናቀቅ የእንስሳቱ ሃላፊነት አይደለም።

[57] ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህንን ክፍል ወንዶችና ሴቶች በትዳር ውስጥ እንዴት እንደሚገናኙና እንደዚሁም በክርስቶስና በቤተክርስቲያን መካከል ስላለው ግኑኝነት ለመናገር ተጠቅሞበታል (ኤፌሶን 5፡22–33 ይመልከቱ)። ይህ የዘፍጥረት ክፍል ክርስቶስን ወይም ቤተ ክርስቲያንን በግልጽ ፈጽሞ አይጠቅስም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ ያለውን ሐሳብ በዚህ ክፍል ይናግራል። አዳም ተግባሩን ለማጠናቀቅ ረዳት ያስፈልገው ነበር። የመጀመሪያው አዳም ሙሽራ ነበረው – ሔዋን። የአዳምና የሔዋን ትዳር በዘፍጥረት 2 ላይ ተገልጿል። ክርስቶስም ደግሞ እንደ ኋለኛው አዳም ሙሽራ አለው እርስዋም ቤተ ክርስቲያን ናት። የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ትዳር በተመለከተ ደግሞ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ላይ ተገልጿል። አዳም በዘፍጥረት 2 ላይ ከባድ እንቅልፍ "ተኛ" እና ሴቲቱ ከእሱ ወጣች በተመሳሳይ መንገድ ክርስቶስም "አንቀላፋ" (ማለትም "ሞተ") እና ቤተ ክርስቲያን ከእርሱ ተገኘች። ስለዚህም ልክ እንደ አዳም ረዳትነት ሔዋን መትጋት እንደ ነበረባት እንደዚሁም ቤተ ክርስቲያንም እንደ ክርስቶስ ሙሽራ የእርሱ ረዳት በመሆን ሚናዋን መወጣት ይኖርባታል።

[58] ሐዋሪያው ጳውሎስ "አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአልና በኋላም ሔዋን ተፈጥረች" (1 ጢሞቴዎስ 2፡13) በሚለው እውነታ ላይ ትልቅ ትርጉም ሰጥቷል። እንደ ጳውሎስ እይታ ከሆነ፤ ይህ እውነታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቀጣይነት ያለው ጠቀሜታ አለው። በአዳምና በሔዋን የአፈጣጠር ቅደም ተከተል ምክንያት ሊሆን ይችላል ጳውሎስ "ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትማር፤ ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሠለጥን አልፈቅድም፤" (1 ጢሞቴዎስ 2፡11–12) ያለው ስለዚህ ጳውሎስ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት ራሳቸውን ማደራጀት እንዳለባቸው የተናገረው በዘፍጥረት ውስጥ ካሉት ጥቅሶች ግንዛቤ የተነሳ ሊሆንም ይችላል። የፍጥረት ሥርዓት (እንደዚሁም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚንፀባረቀው ሥርዓት) አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከሠሩ በኋላ የሆነ ነገር እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል። ይልቁንም ኃጢአት ከመስራታቸው በፊት የሆነ ነው! ይህ ማለት በፍጥረት ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ሥርዓት የሚናቅ ወይም የሚጠላ አይደለም ማለት ነው። ይልቁምንም እንደ መልካም ስጦታዎችም ሁሉ መተግበር ያስፈልጋ።

23 አዳምም አለ፦ ይህች[59] አጥንት ከአጥንቴ ናት *ሥጋም ከሥጋዬ* ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።[60]

---

[59] የእንግሊዝኛው ESV በመባል የሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግልጽ ባይሆንም "ይህች" የሚለው ቃል በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን በግጥሙ በሙሉ ጥቅም ላይ ውሏል። ይሁን እንጂ (ESV የሚጠቀመው አንድ "ይህች" ብቻ ነው፤ እና በዚህ "ይህች" አጠቃቀሙም በዕብራይስጡ ጥቅም ላይ በሚውልበት መንገድ ጥቅም ላይ አልዋለም)። በግጥሙ ውስጥ "ይህች" የሚለው ቃለ የመጀምሪያ ነው፤ ደግሞም በሶስተኛው ስንኝ የመጀመሪያ ቃል ነው እንደገና ደግሞ የመጨረሻው ቃል ነው። ይሁን እንጂ በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ትርጉሞች ደግሞ በመጀመሪያው ስንኝ ላይ አንድ ጊዜ ብቻ ነው ጥቅም ላይ የዋለው። የዕብራይስጡ ግርድፍ ትርጉሙ እንደ ሚከተለው ተቀምጧል፤

> *"**ይህች** አጥንት ከአጥቴ ናት*
>
> *ሥጋም ከሥጋዬ ናት*
>
> ***ይህች** ሴት ትባላለች*
>
> *እርሷ ከውንድ ተገኝታለችና **ይህች** ናት።"*

አዳምም ከሴቲቱ ጎን ቆሞ "በመጨረሻም! ከእነዚያ ጊዜያቶች በኋላ እንስሳት ወደኔ በመጡበት ጊዜ እንኳን ረዳት አልነበረኝም **አሁን ግን** ለእኔ የሚስማማ ረዳት ተሰጥቶኛል! **እርስዋም** ከውንድ ተገኝታለችና ሴት ትባላለች። በዚህ ግጥም ውስጥ "**ይህች**" የሚለው ቃል ለሶስት ለተለያዩ አላማዎች ያገለግላል። በመጀምሪያ በተለያዩ ጊዜያት መካከል እንደ ንጽጽር ሆኖ ያገለግላል፡ "ይህ ጊዜ" የሚለው (ከእነዚያ ሌሎች ጊዜያት በተቃራኒ) የሚገለጽ ነው። ሁለተኛ ከፍጡራን መካከል የትኛው ሴት ተብሎ እንደሚጠራ ለመጠቆም ያገለግላል ("ይህች ሴት ትባላልች") ይላልና። በሦስተኛ ደረጃ ለምን ሴት እንደምትባል ለማብራራት ያገለግላል – ምክንያቱም "ይህች ከአዳም የተወሰደች" ስለሚል ከአዳም ያልተወሰዱ ሌሎች እንስሳት በተቃራኒው) ይገልጻል።

[60] ይህ ግጥም በሰው የተነገረ የመጀመሪያ የግጥም ንግግር ነው። እዚህ ጋ የአድማጮቹ ስም ባይገለጽም አዳም እግዚአብሔርን እያነጋገረ እንደሆነ ግልጽ ይመስላል። ምክንያቱም አዳም ሴቲቱን "ይህች" ብሎ ጠርቷታልና። አዳም የሚናገረው ስለ እሷ ነው እንጂ እሱ የሚናገረው ከእርስዋ ጋር አይደለም። እነዚህ ቃላት የሰርግ ቃል ኪዳን እንደ ማለት ነው! ይህች (በኋላ ሔዋን ተብላለች) ከእርሱ ጋር አንድ እንደሆነች በግልጽ ተናግሯል። ቃሉ ከእርስዋ ጋር አንድ ሥጋ ለመሆን አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ በእግዚአብሔር ፊት ቃል መግባቱን ያመለክታል።

በዚህ ግጥም ውስጥ የመጀመሪያው ቃል ("አጥንት ከአጥንቴ") በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ("ሥጋም ከሥጋዬ") እንዴት እንደ ተስተጋባ ማስተዋል ያስፈልጋል። ይህ እደገና የአረፍተ ነገር ትይዩ ይባላል። ትይዩነት በዕብራይስጡ ግጥም የተለመደ ነው። በዕብራይስጥ ግጥም ሁለተኛው አረፍተ ነገር (አንዳንድ ጊዜ በሊቃውንት እይታ አጭር ጥቅስ ይባላል)፤ ብዙውን ጊዜ በሊቃውንት የመጀመሪያውን አባባል ደግሞ (በድጋሚ አጭር ጥቅስ) ከማስተጋባት ያለፈ ነገር ያደርጋል። እንደዚሁም የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር በሆነ መንገድ ያጠነክረዋል፣ ያጎላዋል ወይም በሃሳቡ ላይ ይጨምራል። በዘፍጥረት 2፡23 ላይ በሁለተኛው አጭር ጥቅስ ላይ ምን ተጨምሯል? በመጀመሪያ ደረጃ "አጥንት ከአጥንቴ" ወደ "ሥጋም ከሥጋዬ" የተሸጋገረ ሲሆን ይህም በሂደት ላይ ከውስጥ የአጥንት መዋቅር ወደ ውጫዊ ቆዳ ግልጽ የሆነ እድገት እንዳለ ያሳያል። ነገር ግን እዚህ ጋ የምናየው ሁሉንም እድገት ነውን? በእርግጠኝነት ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ከስድ ንባብ ይልቅ ግጥምን በተሟላ ሁኔታ ለማብራራት ይከብዳል። ይሁን እንጂ ይህ የግጥም አንዱ የውበት አካል ነው። የግጥም አወቃቀር አንባቢው ቆም ብሎ ምን እንደተባለ እንዲያስብ ያስገድደዋል። በእነዚህ ስንኞች ውስጥ ገጣሚው (አዳም) ከሚስቱ (አጥንት) አካል ካልሆነው አጽም ወጥቶ ስለ እሷ ስለ ቆዳዋ (ሥጋዋ) የበለጠ ግላዊ የሆነ ነገር ለመናገር ተንቀሳቅሷል። አጥንቶች ከባድ ናቸው። ሥጋ ግን ለስላሳና ታዛዥ ነው። በሌላ ሰው ዘንድ ማራኪ ሆኖ የሚገኘው አጥንት ወይም አጽም ሳይሆን ሥጋ ነው። እኛም ከሌላ ሰው አጥንት ጋር ልዩነት የለንም ከሥጋው ጋር ግን ልዩነት አለን። እዚህ ጋ ብዙ በማለት መነጋገር ይቻል ይሆናል (ለምሳሌ አዳም በሁለተኛው አጭር ጥቅስ ላይ በስሜቷ ሜካፕ ላይ ያለውን መስህብ ፍንጭ ይሰጥ ይሆን?) ግን በርግጠኝነት በሁለቱም ስንኞች መካከል የተወሰነ የእድገት ደረጃ ወይም መጠናከር እንዳለ ማስተዋሉ በቂ ነው።

24 ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል፤[61] ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።[62]
25 አዳምና ሚስቱ[63] ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፤[64] አይተፋፈሩም ነበር።[65]

---

ይህ ግጥም የሴቲቱ ክብረ በዓል ቢሆንም ከእንስሳት ጋርም ይዛመዳል ምክንያቱም ሔዋን የምትነጻጸርባቸው ነገሮች ናቸውና። በግጥሙ ውስጥ "ይህች" ተብላ ተጠርታለች። በግጥሙ ውስጥ ስማቸው ባይጠቀስም ሔዋንን እያነጻጸሩ ያሉት "ያ" ናቸው። እንስሳት የተሰጠንን እርዳታ ሊያስታውሱን ይገባል። ፍጡራንን ስናይ በእግዚአብሔር የተፈጥሩ በመሆናቸው እናከብራለን ነገር ግን እጅግ የላቀ እርዳታ አድራጊ ስለተሰጠን ያንን የበለጠ እናከብራለንና!

[61] "አጥብቀህ ያዝ ውይም ተጣበቅ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል እንዲሁ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከእርሱ ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል (ለምሳሌ ዘዳግም 4፡4፣ 10፡20፣ 11፡22፣ 13፡4 እና 30፡20 ይመልከቱ)።

[62] በዚህ ጥቅስ ውስጥ፣ ሙሴ ስለ ጋብቻ አንባቢዎቹን ለማስተማር በማሰብ ትረካውን መተረክ ለጊዜው ገታ አድርጎ እናያለን። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከአዳምና ከሔዋን ውጪ ለሌሎች በግልጽነት የተገለጸው የመጀመሪያው መመሪያ ነው! ሙሴ እነዚህን ቃላት የጻፈው **ከውድቀት** በኋላ የሚኖሩ ሰዎችን ለማስተማር መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል (ውድቀት የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት የአዳምንና የሔዋንን ኃጢአት ወደ ዓለም አቀፋዊ ኃጢአትና ሞት ምክንያት የሆነውን ኃጢአት የሚያመለክቱበት መንገድ ነው)። በዚህ ቃል ሙሴ የሰው ልጅ ኃጢአት ቢሠራም እና ከኤደን ገነት ቢባረርም ቅሉ፤ ጋብቻ ከውድቀት በፊት የነበረውን ትርጉም እንዳላጣ አስገንዝቧል! ይህ የሚያሳየው ለአዳም ረዳት ሲዘጋጅለት የተሰጠው በረከት በወንድና በሴት መካከል በሚደረግ ጋብቻ ሁሉ ውስጥ እንዲንጸባርቅም ጭምር ነው። ሚስት ለባል ስጦታው ነች፤ ስለዚህ እንደ አንድ ሥጋ አንድ በመሆን የተሰጣቸውን ትእዛዝ በመፈጸም የሰው ልጅ ምድርን በእግዚአብሔር መልክና አምሳል እንዲሞላ ነው። ስለዚህ ትዳር ተመሳሳይ ትርጉም ያለው በመሆኑ የሰው ልጅ አሁንም በዘፍጥረት 1፡26–28 የተሰጠውን የመጀመሪያ ተግባር መወጣት አለበት ማለት ነው።

ይህን ክፍል በአግባቡ መረዳት ትልቅ ጠቀሜታ አለው። እነዚህ ጥቅሶች በተለያዩ ወሳኝ ቦታዎች ለክርስቲያናዊ አስተሳሰብ መሰረት ሆነው ያገለግላሉና። በመጀመሪያ፤ ይህ ክፍል ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ስለ ጋብቻና ፍቺ እንዴት ማሰብ እንዳለባቸው ለማብራራት ተጠቅሞበታል (ማቴዎስ 19፡3–12 ማርቆስ 10፡2–12 ይመልከቱ)። በሁለተኛ ደረጃ፤ ይህ ምንባብ ጳውሎስ ለክርስቲያኖች ትክክለኛ እና ተገቢ ያልሆነ የፆታ ሥነ ምግባርን እንዲረዱና መመሪያዎችንም ለመስጠት ተጠቅሞበታል (1 ቆሮንቶስ 6፡12–20 ይመልከቱ)። ሦስተኛ፤ ይህ ምንባብ ጳውሎስ ባሎችና ሚስቶች በትዳር ውስጥ እንዴት እርስ በርስ እንደሚገናኙ ግንዛቤ ለመስጠት ተጠቅሞበታል (ኤፌሶን 5፡22–33 ይመልከቱ)። በአራተኛ ደረጃ ይህ ምንባብ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት መዋቀር እንዳለባት ግንዛቤን ለመፍጠርም ተጠቅሞበታል (1 ጢሞቲዎስ 2፡11–15 ይመልከቱ)።

[63] በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሴትየዋ በስምዋ አለመጠራትዋ እንግዳ ነገር ይመስላል። በእርግጥ ይህ ምዕራፍ ስም የማውጣት ምዕራፍ ነው (አዳም ለሁሉም እንስሳት ስም አውጥቷልና)! ነገር ግን የሴቲቱ ስም እስከ ምዕራፍ 3 ድረስ "ሳይጠቀስ" ቀርቷል። ስሟ ያለተጠቀሰበት ምክንያት ደግሞ በኋላ ግልጽ ተደርጓል።

[64] በምዕራፍ 3፡3 ላይ "ተንኮለኛ" ለሚለው ቃል የተጻፈውን የግርጌ ማስታውሻ ይመልከቱ።

[65] ይህ አስቀድሞ የማሳየት ምሳሌ ነው። ምክንያቱም የሚቀጥለው ምዕራፍ የአዳምና ሔዋን **እራቁትነታቸውን** በተመለከተ ያሳዩትን **ኀፍረት** ላይ ያተኩራልና። ስለዚህ ይህ ጥቅስ በምዕራፍ 3 ላይ ለሚፈጸመው ክንውኖች አንባቢውን ያዘጋጃል ማለት ነው።

## ዘፍጥረት 3

ዘፍጥረት 3 በፍጥረት ታሪክ እና በአለም ታሪክ ውስጥ ትልቅ ለውጥ ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አንባቢው ከእባቡ ጋር ይተዋወቃል እናም እባቡ የእግዚአብሔርን መልካም ቃላትና የእግዚአብሔርንም መልካም ፍጥረት ሲያዛባ ያለውን ሁኔታ ይመለከታል። ይህ እባብ ደግሞ በቀሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ በሚነገረው ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል። አንባቢው ደግሞ ወደ ትዕይንቱ ቀርቦ ሔዋን (ፍጹም የሆነችው የአዳም ረዳት!) ከእባቡ ጋር ስታወራ እያዳመጠ ያለ ይመስላል። ምናልባት አዳም ለምን አንድ ቃል እንኳን እንደማይናገር አንባቢው ያስብ ይሆናል። በመቀጠልም አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን መልካም ትእዛዝ ሲጥሱ እና ፍሬውን ሲበሉ አንባቢው በአግራሞት ወይም በፍርሃት ይመለከታል። ወዲያውኑ ሁሉም ነገር ይለወጣል። አዳምና ሔዋን የዛፎች ቅጠልን ተጠቅመው (የራሳቸው ልብስ) መሥራት ይጀምራሉ። ከእግዚአብሔርም ፊት ለመሰወር ይጥራሉ። እግዚአብሔርም ዘላለማዊ ዳኛ እንደ መሆኑ መጠን፣ በአዳም፣ በሔዋንና በባቡ ላይ ሰማያዊ ፍርድ ሲናገር እንመለከታለን።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አንባቢው ሁለት ሰዎችን ብቻ ነው የሚያየው – አዳምና ሔዋን። ሆኖም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የተገለጸ ሌላ ሰው አለ። ይህም ሰው እንደ አዳምና ሔዋንም ከእባቡ ጋር በቅርበት የሚገናኝ ነው። ነገር ግን እንደ አዳምና ሄዋን የእባቡን ውሸት አይሰማም። ይልቅስ በእባቡ ላይ ድል ይነሳል። ይህ ሰው ጸሐፊው ያስተዋወቀው በግጥም መልክ ነው። ቀጥሎ ያለውን ደማቅ የግጥም ቃላቶች ያስተውሉ።

*“በአንተና በሴቲቱ መካከል*
*በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤*
*እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤*
*አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ።”* **ዘፍጥረት 3፡15**

ይህ ወደፊት እባቡን የሚቀጠቅጥ ጀግና ተዋጊ ማነው? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እባቡን የሚወጋው ወደፊት የሚመጣ ጀግና ተዋጊ የሴቲቱ ዘር ተብሎ ተጠርቷል። በኋለኞቹ የብሉይ ኪዳን ምንባቦች ይህንን የሴቲቱ ዘር በተሻለ ሁኔታ ተግልጿል። እንዲያውም ዘር የሚለው ቃል በብዙ ጉልህ ክፍሎች ውስጥ ጥቅምላይ ውሏል። በብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን የጻፉ ነቢያት የዚህን ዘር መምጣት በጉጉት ይጠባበቁ ነበር። እባቡ የሚሸነፈው መቼ ነው? በዘፍጥረት 3፡15 ላይ የተገለጸው “ዘር” እንደመጣ የአዲስ ኪዳን አንባቢዎች

ያውቃሉ። ስሙም ኢየሱስ ነው። ኢየሱስ አስቀድሞ እባቡን (ማለትም፣ ሰይጣንን) ድል ቢያደርገውም ቅሉ፣ በራዕይ 20፡10 ላይ የተገለጹት ድርጊቶች እስኪፈጸሙ ድረስ ግን የሰይጣን ጥፋት ሙሉ በሙሉ አይተገበርም። እስከዚያ ቀን ድረስ በጌታ በኢየሱስ የሚያምኑቱ በሰይጣን ምክንያት መከራ ይደርስባቸዋል።

# ዘፍጥረት 3 [66]

[66] በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያዎቹ አምስት ተኩል ቁጥሮች ያህል አዳም ግልጽ በሆነ ሁኔታ አልተጠቀሰም። እግዚአብሔር ስለ አዳም ቀደም ብሎ የተናገርውንና የዔድን ገነት **በመንከባከብ** እና **በመጠበቅ** ረገድ ስላለው ሚና ስንመለከት አለመጠቀሱ በጣም የሚያስደንቅ ነገር ነው። ይህ መሆኑ ወዲያውኑ በጣም ስህተት የሆነ አንድ ነገር እንደ ተፈጠረ ለአንባቢው ይነግረዋል። ካለፈው ምዕራፍ በመነሳት አንባቢው አዳም እንዲናገርና እባቡንም ሔዋንን ሲጠይቅ እርምጃ እንዲውስድ መጠበቅ አለበት። ደግሞም ከዚህ ባለፈ ካለፈው ምዕራፍ በመነሳት አንባቢው ሔዋን ከአዳም እርዳታ ስትፈልግ መጠበቅ አለበት! አዳምና ሔዋን አንድ ሥጋ ሊሆኑ ይገባቸዋልና! ይልቁንም አዳም ምንም ሳያደርግ በጸጥታ ከጎንዋ ቆሞ ሳለ ሔዋን ከእባቡ ውሸት ስትታገል አንባቢ ይመለከታል። እግዚአብሔር ለአዳም በሰጠው ትዕዛዝ ላይ በመመስረት አንባቢው አዳምን ከእባቡ ጋር እንዲጋፈጥ፣ ሚስቱንም እንዲጠብቅ እና የኤድን ገነትንም እንዲጠብቅ እየጠበቀ ነው። አዳም ግን ከእነዚህ ነግሮች አንዱንም አያደርግም። ዓለም እስካሁን ድረስ ዋጋ እየከፈለ ያለው በዚያን ጊዜ አዳም ድፍረት በማጣቱና ባለመታዘዙ ምክንያት ነው።

1 እባብም[67] እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው[68] ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ[69] ነበር።

ሴቲቱንም[70]– በውኑ እግዚአብሔር[71] ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ[72] አዝዞአልን?[73] አላት።[74]

---

[67] ይህ እባብ ከተራ እባብ በላይ ነው። በዚህም ምክንያት ይመስላል በእንግሊዝኛዎቹ መጽሐፍ ቅዱሶች "ዘ" የሚለው ቃል "እባብ" ከሚለው ቃል በፊት የሚገኘው። በእንግዝሊዝኛው "ዘ" የሚለው ቃል መታከሉ ሙሴ ስለአንድ የተለየ እባብ እየተናገረ መሆኑን ያሳያል። በኋለኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ በግልጽ እንደተገለጠው፤ ይህ እባብ **ሰይጣን** (ወይም) ዲያብሎስ) ነው – እጅግ ታላቅ ኃይል ያለው ክፉ መንፍሳዊ ፍጡር ነው ( ለምሳሌ ራዕይ 12፡9 ይመልከቱ)። ሰይጣን ማለት "ከሳሽ" ማለት ነው። ኢየሱስ ሰይጣንን "እርሱ ከመጀምሪያ ነፍሰ ገዳይ" እናም "ሐሰተኛ የሐሰትም አባት" ሲል ገልጾታል (ዮሐንስ 8፡44 ይመልከቱ)። ነገር ግን እባቡ ሰይጣን ሆኖ ሳለ በዚህ ክፍል ውስጥ ግን ሰይጣን ተብሎ አልተጠራም። አዳምና ሔዋን ሰይጣንን ልክ እንደ እባብ እንደተገናኙት አንባቢውም ደግሞ እንደ እባብ ይመለከተዋል ማለት ነው። እዚህ ጋ እሱ አደገኛ ከሳሽ አይመስልም። ይልቁንም ሔዋንን ለመርዳት የሚጥር ጓደኛ መስሎ ነው የሚሰራው። ሰይጣን ለእግዚአብሔር ያለውን ጥላቻና እነደዚሁም ደግሞ የእግዚአብሔርን መልካም ቃል ግልጽ በሆነ ሁኔታ አያውጅም። በተቃራኒው ግን እግዚአብሔር የተናገራቸውን ነገሮች እንደ "ማስተካከል" ዓይነት ነገር አድርጎ በማጣመም ይናገራል። ሰይጣን ለአዳምና ለሔዋን የተገለጠበት መንገድ ለሰው ሁሉ "ከመገለጡ" ጋር ተመሳሳይ ነው። ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ቸርነቱ ወይም መልካምነቱ ይዋሻል። ቃሉን መሠረት በማድረግ አዳምና ሔዋን እባቡ ባላጋራ መሆኑን መገንዘብ ነበረባቸው። የእግዚአብሔርን መልካም ቃል እንደማይወድና ደግሞም ለእግዚአብሔር መልካም ቃል መታዘዝን ከፍ አድርጎ እንደሚመለከት ሊገነዘቡት ይገባ ነበር። ይህ የሰይጣን አመለካከት ዛሬም ቢሆን ያው ነው።

አንባቢው በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ ከእባቡ ጋር የሚገናኘው በሦስተኛው ምዕራፍ ላይ ነው። የሚገርመው ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ ድረስ ሳይወገድ ይቀጥላል። በመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያና በመጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ መካከል ደግሞ እባቡ መልኩን ይለውጣል። በመጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ ላይ እባቡ "አድጎ" አስፈሪ ዘንዶ ሆነ። ይህ አንዳንድ መዝሙሮች እግዚአብሔር "የባሕሩን ዘንዶ" እንደሚያሸንፍ የሚናግሩት ለምን እንደሆነ ያብራራል (አንዳንድ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅኔዎች "ረዓብ" የሚለውን ስም ለዚህ አስፈሪ የባሕር አውሬ ዋቢ አድርገው ይጠቀማሉ)።

[68] የነዚህ ቃላት እንድምታ **እግዚአብሔር እባቡንም መፍጠሩ ነው**። ስለዚህ እባቡ በእግዚአብሔር የተፈጥረ ስለሆነ ከግዚአብሔር ጋር እኩል አይደለም። ነገሩ እንዲ ከሆነ ደግሞ ሁሉም ነገር ሲፈጠር መልካም እንደነበር ሁሉ እባቡም ቢሆን መልካም የሆነበት ጊዜ መኖር አለበት ማለት ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ እባቡ ወደ ጥፋት **የወደቀበት** ጊዜ ነበር ማለት ነው። ነገር ግን ይህ በትክክል የሆነው መቼ ነው? ሰይጣንን ለውድቀት የዳረጉት ነገሮችስ ምንድን ናቸው? ሆኖም እዚህ ጋ ሙሴ ያንን ታሪክ ለአንባቢ የመንገር ፍላጎት እንደሌለው ልብ ማለት ያስፈልጋል። ሙሴ እየተናገረ ያለው ስለ ሰዎችና ውድቀታቸው እንጂ ስለ እባቡ ውድቀት አይደለም። ስለዚህ ሰባኪም ወይም አስተማሪም ቢሆን ደራሲው ስለሚያሳስባቸው ነግሮች እንዲጨነቅ ይረዳዋል። በሌላ አነጋገር ደራሲው ባልተጨነቀበት ጉዳይ አንባቢውም ሊቸገርበት አይገባም ማለት ነው። እነዚህ "የተደበቁ ስውር ታሪኮች "አስደሳች ሊሆኑ ይችላሉ ነገር ግን የክፍሉ ዋና ታሪክ ደግሞ አይደሉም። ሌላው ምሳሌ ደግሞ ሙሴ በዘፍጥረት 6፡4 ላይ ስለ ኔፊሊሞች የተናገረው ነገር ነው። ስለእነዚህ "በጥንት ጊዜ የነበሩት ኃያላን ሰዎች" አስደሳች ታሪክ ይመስላል ነገር ግን የክፍሉ ዋና ነጥብ አይደሉም። ዋና ነጥቡ እነዚህ ቢሆኑ ኖሮ ሙሴ ስለእነዚህ ነገሮች የበለጠ ይነግረን ነበር። ነገር ግን ሙሴ ለአንባቢዎቹ እየተናገረ ያለው በጣም አስፈላጊ የሆነውን ብቻ ነው። ስለዚህ የሰባኪው ደስታና ግዴታ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ያሉትን ጠቃሚ መልዕክቶችን ማወቅ እና እነዚያንም ነገሮች ማወጅ ነው።

[69] በዘፍጥረት 2፡25 ላይ ያለው "ራቁት" የሚለው ቃልና በዘፍጥረት 3፡1 ላይ ያለው "ተንኮለኛ" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ በጣም ተመሳሳይ ነው። ይህ ሆን ተብሎ የተደረገ ይመስላል። ይህ በአዳምና በሔዋን ንጽህና እና በእባቡ ተንኮል መካከል ያለውን ግኑኝነት ያቀርባል። አዳምና ሔዋን ለሰይጣን ሸንገላ የተጋለጡ ናቸው። ሰይጣን ፍላጎቱ ሰዎች እፍረትን እንዲለብሱ ነው። የኢየሱስ ፍላጎት ደግሞ ሰዎች እንደ ካህናትና ነገሥታት እንዲለብሱ ነው (መዝሙረ 110፡3፤ ኢሳይያስ 61፡10፤ራዕይ 3፡5፣ 4፡4፣ 7፡9 እና 7፡13 ይመልከቱ)።

[70] እባቡ ከአዳም ይልቅ ለምን ሔዋንን መናገር እንደመረጠ መረዳት ጠቃሚ ነው። የእግዚአብሔርን የአፈጣጠር ሥርዓት ለማቃለል የሚሞክር ይመስላል። ያስታውሱ መጀመሪያ የተፈጠረው አዳም ነው፤ በኋላ ሔዋን ለእርሱ ረዳት ትሆነው ዘንድ እግዚአብሔር ፈጠራት። እባቡ ግን የእግዚአብሔርን የሥልጣን ሥርዓት የማስወገድ ክፉ ሐሳብ እንዳለው ለአንባቢው ፍንጭ ይሰጣል። ይህም በእርግጥ የሰይጣን አላማ ነው። የእግዚአብሔርን መልካም ሥርዓት በማወክ ይደሰታልና።

2 ሴቲቱም ለእባቡ አለችው፦ በገነት  ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፤

3 ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፤ እግዚአብሔር አለ፦ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም።[75]

4 እባብም ለሴቲቱ አላት፦ ሞትን አትሞቱም፤[76]

---

[71] ሰይጣን ለሴቲቱ በተናገረበት ጊዜ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ስም (ያህዌ ኤሎሂም) የሚለውን አልተጠቀመም። ይልቁንም አጠቃላይ የሆነውን የእግዚአብሔርን ስም (ኤሎሂም) የሚለውን ነው የተጠቀመው። ይህም እባቡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን "ወዳጅ" እንዳልሆነ ለአንባቢው ፍንጭ ይሰጣል። የግል ስሙን ሳይሆን የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ስም በመጠቀም ሴቲቱን በስሜትዋ ከእግዚአብብሔር ርቃ እንድትቆይ በሚያስችል መልኩ ስለ እግዚአብሔር ሲናገራት እንመለከታለን። ሰይጣን ሰዎችን የሚያታልለው እንደዚህ በማድረግ ነው። ሰይጣን እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ይጠላል ስለዚህ ሰዎችን ከቃሉ ለማራቅ የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ሴቲቱ በምትሰጠው መልስ ውስጥም እግዚአብሔርን በተመሳሳይ መንገድ ማመልከቷ ጠቃሚ ነው። በሰይጣን ግራ በሚያጋባ ንግግር ምክንያት እግዚአብሔር በተወሰነ መልኩ  ከሰዎች ርቆ ነበርና።

[72] በዚህ ጥቅስ (እና በሚቅጥሉት ትቅሶች ውስጥ) ጥቅም ላይ የዋለው "እንዳትበሉ" የሚለው የብዙ ቁጥር ነው። በወቅቱ ሰይጣንን እየተነጋገረ የነበረው ከሔዋን ጋር ቢሆንም ነገር ግን እሱ እየተናገረ የነበረው ስለሁለቱም ማለትም ስለ ሔዋንና ስለ አዳም ነው።

[73] LXX ወይም ሱፕታጁንት (የመጀምሪያ የዕብራይስጥ ጥንታዊ የግሪክ ትርጉም)  እንዲህ ይነበባል፤ ከገነት ዛፍ ሁሉ አትብሉ "እግዚአብሔር ለምን አለ?

[74] ሰይጣን ከሴቲቱ ጋር የተነጋገረበት መንገድ ለሁሉም ሰዎች "እንዴት" እንደሚናገር ተመሳሳይ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። እሱ ሁል ጊዜ ውሸትን ይናገራል (እንደገና ዮሐንስ 8፡44 ይመልከቱ)። ክርስቲያን እንደዚህ ዓይነት ፈተና በሚያጋጥመው ጊዜ ጸንቶ ለመቆም የእግዚአብሔርን መልካም ቃል **ማወቅ** አለበት፤ ቃሉንም **ማስታወስ**ና ፈተና ሲመጣ ደግሞ በቃሉ ጸንቶ **መቃወም** አለበት (ያዕቆብ 4፡7 እና 1 ጴጥሮስ 5፡8–9 ይመልከቱ)።

[75] ሴትየዋ ያህዌ የተናገረውን ጠቅሳ ተናገረች ሆኖም የተናገረችው ቃል በቃል ጠቅሳ አይደለም **። ያህዌ አዳምና ሔዋን ዛፉን መንካት አይችሉም አላለም**። የተነገረው ግን ከዛፉ መብላት እንደማይችሉ ብቻ ነው። እሷ ግን ያልታዘዘውን በማለት ሕጎቹን የበለጠ ጥብቅ አደረገቻቸው። የእግዚአብሔርን ትክክለኛ ትእዛዝ በተመለከተ ግልጽ የሆነ መረዳት ስላልነበራት ለሰይጣን ማታለል እንድትጋለጥ አድርጓታል። በርግጠኛነትም የሆነው ይኸው ነው። በሰይጣን ተታላለችና (1 ጢሞቴዎስ 2፡ 14 ይመልከቱ)። እግዚአብሔር የተናገራቸውን አብዛኞቹን የምታውቅ ቢመስልም ሔዋን ተታለለች። ይህ የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ ግዴለሽ ለሆኑት ሁሉ እንደ ማስጠንቀቂያ ነው። በተጨማሪም የግዚአብሔር ሕጎች ከተባለው የበለጠ ጥብቅ አድርገን እንዳንመለከትም ማስጠንቀቂያም ነው።

[76] የእባቡ መልስ ልክ መጀመሪያ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ትዕዛዝ አጽንዖት የሚሰጥ ነው። እንደማትሞት አጽንዖት በመስጠት አጥብቆ እንደ ማስገደድ ዓይነት ይናገራታል። ራሱንም ከእግዚአብሔር እኩል እንደሆነ ወይም ከእግዚአብሔር እንደ ሚበልጥ ባለሥልጣን አድርጎ ይሰይማል!

5 ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ፤ እንደ እግዚአብሔርም[77] መልካሙንና ክፉውን የምታውቁ[78] እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ[79] ነው እንጂ።

[77] የ LXX ወይም ሴፕታጁንት ትርጉም በብዙ ቃል "እነደ አማልክት ትሆናላችሁ" ይለዋል።

[78] በዚህ ጊዜ አዳም እባቡ ጠላት መሆኑን አውቆ ከእባቡ ጋር ሊዋጋ ይገባ ነበር። የዔድን ገነትን "እንዲጠብቅ" ታዞ ነበርና። ልክ ካህናቱ የመገናኛው ድንኳን እንዲጠብቁ (በኋለኛው ዘመን ደግሞ ቤተ መቅደሱ) ከክፉ ነገር እንዲጠብቁ በታዘዙበት መንገድ አዳምም የዔድን ገነት ከክፉ ነገር እንዲጠብቅ ታዞ ነበር። በተቃራኒው ግን አዳም ሚስቱ እንድትታለል ፈቀደ። የኋለኛው አዳም ኢየሱስ ግን ይህን አላደርገም አያደርግምም። ኢየሱስ ሙሽራዋ (ቤተክርስቲያን) እንዳትታለል ከሰይጣን ጋር ተዋጋ።

ሰይጣን ውሸታም ነው። ሆኖም እንደ ሁሉም ውሸታሞች ቃላቶቹ በውስጣቸው ትንሽ እውነት አላቸው። አዳምና ሔዋን ፍሬውን ሲበሉ፤ ቢያንስ በተወሰነ መልኩ እንደ አምላክ ሆኑ። የእውነተኛውን አምላክ ዳኝነት በመተው ትክክልና ስህተት የሆነውን ነገር በተመለከተ በራሳቸው ውሳኔ የማድረግ መብት እንዳላቸው ማመን ጀመሩ። በመሠረቱ በዚህ መንገድም የራሳቸው አምላክ ሆኑ። አዳምና ሔዋን ከዚህ በፊት እንዲህ አድርገው አያውቁም ነበር። ይልቅስ በእግዚአብሔር ሕግ በመመራት በእርሱ ዳኝነት ላይ ይመረኮዙ ነበርና። በዘፍጥረት 1፡4፣ 1፡10፣ 1፡12፣ 1፡18፣ 1፡21፣ 1፡25 እና 1፡31 እግዚአብሔር ዳኝነት ሲሰጥ አንባቢው አስቀድሞ አንብቧል። በእነዚህ ሁሉ ጥቅሶች ውስጥ እግዚአብሔር አንድን ነገር መልካም መሆኑን ወስኗል። አንድን ነገር መልካም የሆነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱ መልካም ነው ብሎ ስለሰየመው ነው። እሱ ትክክለኛው ዳኛ ነውና። ስለዚህ መልካሙንና ክፍውን መወሰን ለእግዚአብሔር ብቻ የተሰጠ መብት ነው። ይህ በዘፍጥረት 1 እና 2 ግልጽ ተደርጎዋል። እባቡ ግን አዳምና ሚስቱ ይህ መብት እንዳልተሰጣቸው ያውቅ ነበር። **በዛፉ ላይ የነበረው የማይበላው ፍሬ እግዚአብሔር ፍርድን ወይም ዳኝነትን ለራሱ እንዳደረገ ለምስክርነት የቆመ ፍሬ ነበር።** አዳም ግን ከዛፉ የሚገኘውን የማወቅ ኃይል በርሱ ውስጥ እንዲሆን ይፈልግ ነበር! የአዳም አመጽ ዛሬም በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ይታያል። ከኃጢአት ውጤቶች አንዱ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍርድ ወይም ዳኝነት ለማክበር አለመፈለጋቸውን ነው። ይልቁንም እንደ ትናንሽ አማልክቶች ሰዎች ራሳቸው ፍርድ ይሰጣሉ።ከዚህም የተነሳ ሰዎች እግዚአብሔር ክፉ ብሎ ያወጀባቸውን ነገሮች "መልካም" እና መልካም ብሎ ያወጀባቸውን ነገሮች ደግሞ "ክፉ" ይሏቸዋል።

[79] እንደ እግዚአብሔር ሃሳብ ከሆነ አዳምና ሔዋን እንዳይሞቱ ይህን ትዛዝ እንደሰጣቸው ይመስላል። ነገር ግን ትዕዛዙ የሰጣቸው ከፍቅሩ የተነሳ ለጥቅማቸው ነበር። እንደ ሰይጣን ገለጻ ከሆነ ግን እግዚአብሔር ይህን ትዕዛዝ ለመስጠት ያነሳሳው የተለየ ምክንያት ነበርው ማለት ነው። እግዚአብሔር ራስ ወዳድ እነደሆነና ሊሎች እንደ እሱ እንዲሆኑ እንደማይፈልግ አድርጎ ነው ያቀረበው። ሰይጣን ዛሬም ቢሆን እንዲሁ ያደርጋል። የእግዚአብሔርን ባሕርይ ጥያቄ ውስጥ ለመጣል ይጣጣራል።

6 ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፤ ለጥበብም መልካም እንደሆነ
አየች፤[80] ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው[81] እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ።[82]
7 የሁለቱም ዓይኖች ተከፍቱ፤[83] እነርሱም ራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ፤ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው
ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ።[84]

---

[80] ይህ ጥቅስ ሴትየዋ እግዚአብሔርን አለመታዘዝና ከዛፉ ፍሬ መብላት ትክክል እንደሆነ የተሰማትን ሦስት ምክንያቶች ይገልጻል። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የሔዋን ምክንያቶች በዘፍጥረት 2፡9 ላይ የተጠቀሱት ናቸው፤ እነዚህም ዛፉ ለዓይን ያማረና ለምብል ደግሞ መልካም ነበር የሚሉት ናቸው ። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ፍሬው መልካም ፍሬ ሊሆን ቢችልም ቅሉ ለእሷ ግን ጥሩ ምግብ አልነበረም። ሊገላት የሚችል ምግብ ነበርና። ሌላኛው ሔዋን ከሰይጣን የተማረችው ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ በሰይጣን ማታለል በመመስረት ከዛፉ መብላት ጥበበኛ እንደሚያደርግ አምናለችና። ነገረ ግን የተከለከለ ፍሬ መብላት ማንንም ጥበበኛ አያደርግም። የባሰውኑ ያሰው ሞኝ መሆኑን ያሳያል እንጂ ። ይልቅስ ጥበበኛ የሚያደርገው እግዚአብብሔርን መፍራትና መልካሙን ቃሉን (ትዕዛዛቱንም) መስማትና መጠበቅ ነው እንጂ። ሔዋን ፍሬውን እንድትበላ ያሳመኗት ሦስቱ ምክንያቶች በ 1 ዮሐንስ 2፡16 ላይ ከተነገሩት "ምኞቶች" ጋር በጣም ተመሳሳይ ናቸው፡፡ "በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ስለሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም" ይላልና። ስለዚህ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ለምን ተቀባይነት እንዳለው ምክንያት ከመደርደር ዝንባሌያችን መጠንቀቅ ይኖርብናል።

የሔዋን ታሪክ በተለያዩ ገፀ-ባሕሪያት እና በተለያዩ መንገዶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሷል። ለምሳሌ በታሪኩ ውስጥ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ በገቡበት ወቅት ኢያሪኮን ድል ያደረጉት እሥራኤላውያን (ኢያሱ 7፡ 18–24 ይመልከቱ) እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን ዘረፋውን (የከተማውን ሀብት) ለራሳቸው መውሰድ እንደ ማይችሉ ነግሮዋቸው ነበርና። ነገር ግን የተነገራቸውን በመተላለፍ አካን የሚባል ሰው "በዘረፋ መካከል አንድ ያማረ የሰናዖር ካባ፣ ሁለት መቶም ሰቅል ብር፣ ሚዛኑም አምሳ ሰቅል የሆነ ወርቅ አይቶ **ተመኝቶ ወሰደ።**" ይሁን እንጂ የአካን የአለመታዘዝ ኃጢአት ለመላው እሥራኤላውያን ቅጣት አስከትሏል። ነገር ግን እንደ ሔዋንና አካን ፈተናውን ተፈትኖ ያለፍ ደግሞ አንድ አለ። እሱም ኢየሱስ ነው፤ በሰይጣን ተፈትኗልና (ማቴዎስ 4፡1–11 ይመልከቱ)። ኢየሱስ ግን የእግዚአብሔርን መልካም ቃል ከሰይጣን ውሸቶች የተሻለና ውድ ሀብት አድርጎ በመመልከት ሰይጣንን ድል አድርጎታል።

[81] አዳም ያለምንም ተቃውሞ ወይም አስተያየት ከባለቤቱ አጠገብ ቆሞ ነበር። ነገር ግን የዔድን ገነት እንዲጠብቅ በታዘዘው መሠረት ዳግመኛ ከእባቡ ጋር ወደ ጦርነት በመግባት ከገነት ውስጥ ሊያስወጣው በተገባ ነበር። ልክ እግዚአብሔር ምድርን መኖሪያ ለመሆን እንድትችል የጋረዳትን ጨለማ (ማለትም "ምድርም ባዶ ነበርች አንዳችም አልነበረባትም") እንደሚል እግዚአብብሔር ግን ያንን ጨለማና ባዶነት ለውጦ ምቹ መኖሪያ አደረጋት ( ዘፍጥረት 1፡2 ይመልከቱ)። እንደዚሁም አዳምም የዔድን ገነት ለመኖሪያነት እንዳይሆን የሚከለክለውን መንፍሳዊ ጨለማ ማሸነፍና ማስወገድ ነበረበት።

[82] በ 1 ጢሞቴዎስ 2፡4 ጳውሎስ "የተታለለም አዳም አይደለም" ሲል ተናግሯል። ይህም ማለት አዳም እያወቀ በእግዚአብሔር ላይ **አመፀ** ማለት ነው!

[83] አዳማና ሔዋን ዓይኖቻቸው ተከፍቶና ጠቢባን እንዲሆኑ ጠብቀው ነበር። ነገር ግን ዓይኖቻቸው ሲከፈቱ ያዩት ራቁታቸውን መሆናቸውን ነው። በሰይጣን "ተንኮል" ምክንያት (ዘፍጥረት 3፡1) የአዳምና የሔዋን "ዕራቁትነት" ተገለጠ (ዘፍጥረት 2፡25)።

[84] በዓለም ታሪክም ውስጥ ሰዎች የሚያደርጉት የመጀመሪያው ነገር እንደዚህ ዓይነቱን ነገር ነው። እንደ አንባቢያን እግዚአብሔር ነገሮችን እንደሚሠራ በመጠባበቅ እዚህ ድረስ መጥተናል። አዳምና ሔዋን መልበስ ቢኖርባቸው ኖሮ እግዚአብብሔር ልብሳቸውን መሥራትና ልብሱንም ለእነርሱ መስጠቱን ተገቢው ያ ነበር። ሆኖም እዚህ ጋ አዳምና ሔዋን ራሳቸው ነውራቸውን ለመሸፈን ሲሞክሩ ይታያል። ይሁን እንጂ ልብሳቸው ኃጢአታቸውን ሊሰውርላቸው አልቻለም።

8 እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምጽ ከገነት ውስጥ ሲመላላስ ሰሙ፤[85] አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ።[86]

9[87] እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ[88] ወዴት ነህ? አለው።[89]

10 እርሱም አለ፡– በገነት ድምጽህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፤[90] ተሸሸግሁም።[91]

---

[85] በ LXX ወይም በሱፐታጁንት "በቀን ነፋስ" ተብሎ ነው የተተረጎመው። የዚህ የዕብራይስጡ ትርጉም እግዚአብብሔር በቀኑ ቀዝቃዛ ክፍል ውስጥ በአትክልቱ ውስጥ መመላለሱን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ "የቀኑ ነፋስ" እግዚአብሔር በዐውሎ ነፋስ ወደ አዳምና ሚስቱ እንደ ቀረበ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል! እንግዲህ ነገሩ እንደዛ ከሆነ ይህ ነፋስ ደግሞ ተራ ነፋስ አልነበረም ማለት ነው። ምናልባትም ደግሞ በነጎድጓድ፣ በመብረቅ፣ በጨለማ እና በዝናብ የታጀበ አውሎ ነፋስ ሊሆን ይችላል። በማዕበል መታጀቡ ደግሞ በኃጢአት ምክንያት ለተገለጠው ለእግዚአብሔር ቁጣ ትክክለኛ አመጣጥ ነው። ደግሞም የ "አውሎ ነፋስ" ትርጓሜ የእግዚአብሔር ቁጣ በውጫዊ ሁኔታ ከሚታይባቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ጋር በጥሩ ሁኔታ ይስማማል ወይም ይገጥማል። ለምሳሌ ያህል ኢየሱስ በተሰቀለበት ወቅት የነበረውን ጨለማ እና የመሬት መንቀጥቀጥ ተመልከት (ማቴዎስ 27፡45–56 ተመልከት)።

[86] ኃጢአት ሰዎች ኃጢአታቸውን በራሳቸው ዘዴ ወይም መንገድ እንዲሸፍኑና ከእግዚአብሔር ፊት እንዲሰወሩ ያደርጋቸዋል። እግዚአብሔር ግን ቸር ነውና አዳምና ሔዋን ኃጢአት በመስራታቸው ምክንያት ሊሸሹ ቢፈልጉም መጥቶ አገኛቸው። እግዚአብሔር ዛሬም ከኃጢአተኞች ጋር ይህንኑ ያደርጋል።

[87] በቁጥር 9 እና 11 ላይ ያሉትን የእግዚአብሔር ጥያቄዎች ያነጣጠሩት በአዳም ላይ ብቻ ነው።

[88] ሰውየው ማለት አዳም መሪ ነው የነበርው። ሰይጣን ደግሞ የእግዚአብሔርን የሥልጣን ተዋረድ ገና አላወቀም ነበርና። ለዚህም ይመስላል ሰውዬውን ችላ ብሎ ሴቲቱን የፈተነው። እግዚአብብሔር ግን የሥልጣን መዋቅሩን አይለውጠውም። እግዚአብብሔር በመጀምሪያ ለአዳም የተናገረበት ምክንያት አዳም የመጨረሻው ኃላፊነት የነበረው ሰው ስለነበረ ነው።

[89] እግዚአብሔር ግራ አይጋባም። እርሱ ሁሉንም ያውቃልና። ይህን ጥያቄ የጠየቀው ግን የአዳምን መልስ መስማት ስለሚፈልግ ነው። የእግዚአብሔር ጥያቄ ደግሞ አንባቢው የአዳምን መልስ እንዲሰማ ዕድል ይሰጠዋልና።

"ወዴት ነህ?" የሚለው የተነገረው ለአዳም ብቻ ነው። ይህም ግልጽ ነው ምክንያቱም "አንተ" የሚለው ቃል በዕብራይስጡ (MT ወይም ማዞረቲክ ቴክስት) እና በግሪኩም LXX (ሱፐታጁንት) ነጣላ ነው። ይህም ደግሞ እግዚአብብሔር አዳምን እንደ መሪ አድርጎ እንደሚቆጥረውና አሁን ለተፈጠረው ነገር ተጠያቂ እንደሚሆን የሚያሳይ ተጨማሪ ማስረጃ ነው።

[90] ኃጢአትና ፍራሃት የተያያዙ ነገሮች ናቸው። ይህም በአዳምም ጊዜ እውነት ነበር። ዛሬም ደግሞ እውነት ነው።

[91] አዳም "እኔ" የሚለውን ተውላጠ ስም እዚህ ላይ ደጋግሞ መጠቀሙ ትኩረት የሚስብ ነው። አዳምና ሔዋን አንድ የሆኑ ቢሆን ኖሮ "እራቁታችን ስለሆንን" ይል ነበር። ነገር ግን ኃጢአት ሰውየውን ከሚስቱ ለየው። ይህም ደግሞ ሁልጊዜ የሚከሰት ነው። ኃጢአት አንድን ሰው ከግዚአብብሔር ጋር ያለውን ግኑኝነት ማበላሸት ብቻ ሳይሆን አንድን ሰው ከሌሎችም ሰዎች ጋር ያለውን ግኑኝነት ያበላሻልና።

11[92] እግዚአብሔርም አለው፡— ዕራቁትህን እንደሆንህ ማን ነገረህ?[93] ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን?[94]

12 አዳምም አለ፡— ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ።[95]

13 እግዚአብሔር አምላክ ሴቲቱን፡— ይህ ያደረግሽው ምንድር ነው? አላት። ሴቲቱም አለች፡— እባብ አሳተኝና[96] በላሁ።

---

[92] ልክ በቁጥር 9 ላይ እንዳለውም ሁሉ በቁጥር 11 ላይም ያሉትን የእግዚአብሔር ጥያቄዎች ለአዳም ብቻ የቀረቡ ናቸው። "አንተ" በሚል የተገለጸው በዕብራይስጡም (MT ወይም ማዞረቲክ ቴክስት) እና በግሪኩም LXX (ሱፐታጁንት) በነጠላነት ነው የተገለጸው። እንደገና አዳም በገነት ውስጥ ለሆነው ነገር ተጠያቂው እሱ መሆኑን ያመለክታል። የተፈጸመውም ድርጊት ለሰው ልጆች ሁሉ ሞትን አስከትሏል። በአዎንታዊ መልኩ ደግሞ እግዚአብሔር የኋለኛውንም አዳም (ኢየሱስ) ላደረገው ነገር ተጣያቂ አድርጎ ይቆጥረዋል ማለት ነው! በተመሳሳይ መልኩ የአዳም አመፅ "በእርሱ" ላሉት ሁሉ ሞትን እንዳመጣ፤ የኢየሱስ ታዛዥነት  ደግሞ "በእርሱ" ላሉት ሁሉ ወደ ሕይወት ይመራል ማለት ነው።

[93] እግዚአብሔር የዚህን ጥያቄ መልስ ያውቃል። ደግሞም የእግዚአብሔር ጥያቄዎች አንባቢው የአዳምን መልስ እንዲሰማ ያስችለዋል።እሱ ምን እያሰበ እንዳለ እንድናውቅ ያስችሉናል።

[94] ይህ በዘፍጥረት 2፡17 ላይ እግዚአብብሔር ለአዳም የሰጠውን ትዕዛዝ የሚያመለክት ነው።

[95] አዳምም በዘፈጥርት 2፡23 ላይ ውብና የፍቅር ቅኔን ከመናገር ወደ እነዚህ ስንኞች ጭካኔ የተሞላበት ውንጀላ ደረሰ። አዳም ሚስቱን ሔዋንን ስለሰጠው እግዚአብብሔርን ወቀሰው! ከዚያም ለሰራው ኃጢአት ሚስቱን ተጠያቂ አደረገ። ስለኃጢአቱም ንስሐ አይገባም ወይም ከፋት እንዳደረገ ምንም መጸጸት አያሳይም። እንዳውም አዳም ስለኃጢአቱ እንደመከራከር ቃጣው። ይህ የአዳም ንግግር በሁለት ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት እንድናወዳድር ይረዳናል፤ በዘፍጥረት 2፡23 እግዚአብሔር ያሰበው ሕይወት እና ደግሞ በዘፍጥረት 3፡12 ሕይወት ሰይጣን በሚፈልገው መንገድ መካከል ሲያስኬደው ያለውን ልዩነት የሚያሳይ ፍጹም ስዕላዊ ነው።

[96] እዚህ ጋ ሔዋን እውነቱን ተናገረች። በትትክልም ተታላለች (1 ጢሞቴዎስ 2፡14 ይመልከቱ)። ጳውሎስ "ሔዋን መታለልዋን ከአማኞች ሀሳብ መበላሸት ጋር እንዲህ በማለት ያነጻጽራል "እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራሉ" (2 ቆሮስንቶስ 11፡3)። ጳውሎስ "ሔዋን ተታለለች" የሚለውን ታሪክ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍላቸው መጠቀሙ በዛሬውም ጊዜ ሰባኪዎች ክርስቲያኖችን በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ለመርዳት እነዚህን ቀደምት ታሪኮች እንዴት እንደ ምሳሌ ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ ያሳያል።

14 እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው፦[97] ይህን ስላደረግህ[98] ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ትሆናለህ፣ በሆድህም ትሄዳለህ፣ አፈርንም በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ትበላለህ።[99]

---

[97] እዚህ ጋ በክስ ላይ ያሉትን ሶስቱ "ገጸ-ባህሪያት" በእግዚአብሔር ፊት እኩል አይደሉም። ሰውየውና ሴትየዋ እንዲናገሩ ተፈቅዶላቸዋል። ይህም በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ዋጋ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። እባቡ ግን እንዲናገር አልተፈቀደለትም ምክንያቱም እግዚአብሔር እባቡ ራሱን እንዲከላከል እድል በመስጠት እንዲያከብረው አልፈለገምና። እንደዚሁም ደግሞ እግዚአብሔር ሰዎችን መጀመሪያ እንዳናገረ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይህም ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ዋጋ እንዳላቸው መረዳት የሚያስችል ሌላ ማሳያ ነው። የእግዚአብሔርም ፍርድ መጀመሪያ የተነገረው በእባቡ ላይ ነው። ምሕረት አይደረግለትምና። ለሰዎች ግን ታላቅ ምሕረት ይደርጋል። ይህ ምሕረት በቁጥር 15 እና በተቀረው የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍልም ውስጥ ይታያል።

[98] ይህ ማለት ሴቲቱን በማታለል ሰውየውን ወደ አመጽ መርተሃል ማለት ነው።

[99] በተጨማሪም ኢሳይያስ 65፡25 ይመልከቱ። በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር ውስጥም እንኳን እባቡ በኤድን ገነት ውስጥ የተጫወተውን አስከፊ ሚና የሚገልጽ ማስታወሻ ይኖራል! በአሁኑ ጊዜም ሁሉም እባቦች የሚጋሩት በሆድ እየተሳቡ አቧራ መጠጣት፣ ሰይጣን በእግዚአብሔር ፊት ያለውን ስፍራ እና የእሱን ጥፋት የማያቋርጥ ማሳሰቢያ ሆኖ ያገለግላል።

15 በአንተና በሴቲቱ መካከል[100] በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤[101] እርሱ[102] ራስህን ይቀጠቅጣል፤[103] አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ።[104]

---

[100] እነዚህ ቃላት የተነገሩት ለሔዋን ነው። ሆኖም በኋላ ላይ ያሉትን ምንባቦች በግልጽ እንደሚያሳዩት፣ "ሴቲቱ" ማለት ሔዋንን ብቻ ከመጥቀስ በላይ ነው። ይህም በመጨረሻ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሰዎች (ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች) ትንቢታዊ ማጣቀሻ ነው። ከእግዚአብብሔር ታማኝ ሰዎች በኩል ነውና ክርስቶስ የመጣው (ራዕይ 12፡1–6 ይመልከቱ)። ከእግዚአብሔር የሆኑ ሁሉ በሰይጣን ይጠላሉ። ይሁን እንጂ "በዘርህና በዘሯ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ" የሚለው ቃል አንባቢውን በተስፋ እንዲሞላ ማድረግ ይኖርበታል። ይህ ማለት እግዚአብሔር ሕዝቦቹን ሰይጣንንና ሥራዎቹን እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል ማለት ነው። ይህም የሚሆነው በእግዚአብሔር ፀጋ ነው! እንደ ሔዋን እንዳንታለል እግዚአብብሔር ጸጋን እየሰጠን ነው። የእግዚአብብሔር ሰዎች ለሰይጣንና ለሥራዎቹ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ጥላቻ አላቸው!

[101] **ዘር የሚለው ቃል ብዙ ቃል ሊሆን ይችላል** (ብዙ ዘሮችን የሚያመለክት) **ወይም ነጠላ ቃል** (አንድን ዘር የሚያመለክት) ሊሆን ይችላል። በዚህ ግጥም ሁለቱንም ሊያመለክት ይችላል ማለት ነው! በመጀመሪያ ሰባኪ ይህንን እንደ ነጠላ ነው ማየት ያለበት። ዘሩ የሚያመለክተው የሴቲቱ የወንድ ዘር "የእባቡን ጭንቅላት የሚቀጠቅጥ" መሆኑን ነው። ይህም ኢየሱስን የሚያመለክት ነው። ኢየሱስ ደግሞ እንደ ኋለኛው አዳም መዋጋት እና እባቡንም ማሸነፍ የእርሱ ኃላፊነትና ክብር ነው። በሁለተኛ ደረጃ ሰባኪው ዘር የሚለውን ቃል ብዙ ቁጥር አድርጎ ማየት ይኖርበታል። አማኞች "በክርስቶስ" እንዳሉ ስለሚቆጠሩና የክርስቶስም ተከታዮች ስለሆኑም እንደ ዘር ደግሞ ይቆጠራሉ ማለት ነው (ዘፍጥረት 15፡5፣ ሮሜ 16፡ 20 እና ገላትያ 3፡29 ይመልከቱ)! እንግዲህ ዘር የሚለው ቃል ነጠላም ነው (ክርስቶስን ያመለክታል) እንደዚሁም ደግሞ ብዙ ነው (የክርስቶስ የሆኑትንም ያመልከታልና)። ለዚህም ነው ሰይጣን ኢየሱስንና የኢየሱስ የሆኑትን የሚጠላው። ሰይጣን ነጠላ የሆነው ዘር (ክርስቶስን) እና ብዙ ዘር የሆኑትን (በክርስቶስ የሚያምኑትን) ለማጥፋት ያለውን ፍላጎት በተመለከተ ራዕይ 12፡ 1–5 ይመልከቱ (እነዚህ ጥቅሶች ሰይጣን ለክርስቶስ ያለውን ጥላቻ የሚያመለክቱ ናቸው) እና ራዕይ 12፡7–17 (በተጨማሪ እነዚህም ጥቅሶች ደግሞ ሰይጣን በክርስቶስ ለሚያምኑት ያለውን ጥላቻ የሚያመለክቱ ናቸው)። እንደዚሁም ደግሞ በገላትያ 3፡16 እና 29 ላይ የሚገኘውን የጳውሎስን ቃላት ከዘፍጥረት 13፡15፣ 17፡8 እና 24፡7 ጋር በማነጻጸር ያንብቡ። በተጨማሪም ኢሳይያስ 6፡13 ይመልከቱ። ይህ የኢሳይያስ ክፍል ስለ ክርስቶስ የተነገረ ትንቢት ነው። የእንግሊዝኛው (ESV) ኢኤስቪ ትርጉም "ጉቶው የተቀደሰ **ዘር** ነው" ይላል። በዘፍጥረት 3፡15 ላይ "ዘር" ተብሎ የተተረጎመው እዚህ ጋ "ዘር" ተብሎ ከተጻፈው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ ይህ የኢሳይያስ ክፍል በዘፍጥረት 3፡15 የተነገረውን ዘር የሚያመለክት ነው ማለት ነው!

በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሰው የሴቲቱ ዘር ብቻ አይደለም። እባቡም ዘር አለው። የሴቲቱ ዘር ነጠላ (ክርስቶስ) እና ብዙ (በክርስቶስ የሚያምኑቱ) እንደሆኑ ሁሉ የእባቡም ዘር እንደ ነጠላ እና ብዙ መቆጠር አለበት። ይህ ክፍል ደግሞ **የክርስቶስ ተቃዋሚን** ሃሳብ ያስተዋውቃል (ምንም እንኳን ይህ ቃል በዚህ ክፍል በቀጥታ ጥቅም ላይ ባይውልም ማለት ነው)። ይህ እግዚአብሔርን የሚጠላ ክርስቶስ ደግሞ የሚክድ የእባቡ ዘር የሴቲቱን ዘር በመጥላት ይታውቃል። በ 1 ዮሐንስ 2፡18–25 ላይ እንደተጻፈው ይህ ቃል ነጠላ ሊሆን ይችላል ("የክርስቶስ ***ተቃዋሚ***" እንደሚል) እና ብዙ ቁጥርም ሊሆን ይችላል ("የክርስቶስ ***ተቃቃሚዎች***" እንደሚልም) ማለት ነው። በተጨማሪም 2 ተሰሎንቄ 2፡3–4 እና ራዕይ 13፡1–10 ይመልከቱ። እስከ ፍጻሜው ዘመን ድረስ የሴቲቱ ዘር (ክርስቶስና በክርስቶስ የሆኑት ሁሉ) እና የእባቡ ዘር (የክርስቶስ ተቃዋሚ–ነጠላም ሆነ ብዙ ቁጥር) ውጊያ ማድረጋቸውን ይቀጥላሉ። ሆኖም በመጨረሻም የሴቲቱ ዘር ያሸንፋል (ራዕይ 20፡7–10 ይመልከቱ)።

[102] እዚህ ላይ "እርሱ" የተባለው ክርስቶስን ነው። የእባቡን ራስ "የሚቀጠቅጠው" ከሴቲቱ የተወለደው ወንድ ዘር ነው። ደግሞም "እርሱ" የሚለው በክርስቶስም ያሉትን ሁሉ የሚያጠቃልል ቃል ነው።

[103] ይህ ክፍል ክርስቶስ ሰይጣንን እንዳደቀቀ የሚያመለክት ነው። ነገር ግን እኛ አማኞች ደግሞ በክርስቶስ ስላለን እኛ ደግሞ እንደ ክርስቶስ ሰይጣንን ለማድቀቅ የጌታን ስም እንጠቀማለን። ለዚህም ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮሜ 16፡20 ላይ ሰይጣን ከእግራችን በታች እንደሚቀጠቀጥ መናገር የቻለው!

[104] በመርዛማ እባብ ሰኮና ወይም ተረከዝ ላይ መነደፍ ገዳይ ነገር ነው። ስለዚህ እባቡ የሴቲቱን "ዘር" ሰኮና "ይቀጠቅጣል" የሚለው እውነታ በቀላሉ ሊወሰድ አይገባም። ይህ ገዳይ ቁስል ነውና! የሴቲቱ ዘር (ኢየሱስ) ከእባቡ ጋር ለመዋጋት ሲሄድ በጣም ይሠቃያል ማለት ነው። ይሁን እንጂ አዳም ሊያደርገው ያልቻለውን ደግሞ ኢየሱስ አደረገ። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል እንዲከበር እና የእግዚአብሔር ሕዝብ ያለ ፍርሃት እግዚአብሔር ባዘጋጀለት ሥፍራ እንዲኖር እንዲያጠፋው ከእባቡ

16 ለሴቲቱም አለ፡– በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ[105] ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤[106] እርሱም ገዥሽ ይሆናል።[107]
17 አዳምንም አለው፡– የሚስትህንም ቃል ሰምተሃልና[108] ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገምች ትሁን፤[109] በሕይወትህ ዘምን ሁሉ ከድካምህ ከእርስዋ ትበላልህ፤

---

ጋር ይዋጋል። ይህም የወንጌል ታሪክ ነው! ኢየሱስ የሞተው የሰይጣን ሥራ እንዲያፈርስና ሰዎች ከዲያብሎስ ወጥመድ ኃይል ነፃ እንዲወጡ ነው (ለምሳሌ የሐዋሪያት ሥራ 10፡38 ይመለከቱ)። ኢየሱስ ሞቶ አልቀረም። ከሞት ተነስቷልና። የእግዚአብብሔር ሕዝብም እንደ ኢየሱስም ሁሉ በሰይጣን ምክንያት በእጅጉ ይሠቃያሉ። በመሆኑም በክርስቶስ ያሉቱ ሁሉ በሰይጣን ምክንያት "የተረከዝ መቀጥቀጥ" ይደርስባቸዋል። ደግሞ በክርስቶስ ያሉት ሁሉ ግን የሰይጣንን ራስ የመቀጥቀጡ አካል ናቸው! እንደገና ሮሜ 16፡20 እና ራዕይ 12 ይመልከቱ።

105 በአንድ በኩል ይህ ከእያንዳንዱ የመውለድ ሂደት ጋር አብሮ የሚመጡ የተለመዱ የወሊድ ህመሞችን የሚያመለክት ነው። እያንዳንዱ ሴት በምትወልድበት ጊዜ የሚደርስባት አካላዊ የወሊድ ሕመም ከታላቁ መወለድ ማለትም ከክርስቶስ መወለድ ጋር የተያያዘውን ሥቃይ ለማስታወስ ያገለግላል! ሆኖም ግን ይህ የወሊድ ህመምን የሚመለከት ብቸኛ ምክንያት አይደለም። በመሆኑም በዚህ ግጥም አወድ መሠረት የወሊዱን ህመም እባቡን የሚያጠፋውን "ዘር" ለመውለድ በሚደረገው ትግል ሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚከፍለውን ታላቅ ሥቃይ የሚያመለክትም ነው። የክርስቶስን መወለድ ለማየት ባደርጉት ተጋድሎ በጣም ብዙ ሰዎች ሞተዋል። ከዚህ በመነሳትም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ቅዱሳን ሁሉ "በምጥ ትታግል የነበረች ሴት" ተብለው ሊቆጠሩ ይችላሉ። ከዘፍጥረት 3፡15 ጋር ስናገናኘውም እባቡን የሚቀጠቅጠው ዘር ከግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ብዙ ዋጋ እንደሚከፍል ማየት እንችላልን። እንደገና ራዕይ 12 ይመልከቱ። የእግዚአብሔር ሕዝቦች "ዘርን" ለመውለድ (እዚህ ጋ አዲስ የክርስቶስ ተከታይ የማፍራትን ሂድት ያመለክታል) በሚታገሉበት ወቅት "የመውለድ ሥቃይ" አሁንም እየደረሰባቸው ነው!

106 የ ESV (ኢኤስቪ) የ 2017 የመጽሐፍ ቅዱስ ዕትም "ፈቃድሽ ከባልሽ ጋር ተቃራኒ ይሆናል" ብሎ አስቀምጦታል። ይሁን እንጂ ቀደም ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ደግሞ "ፈቃድሽም **ወደ** ባልሽ ይሆናል" የሚለውን ነው ያስቀመጡት። እንግዲህ የ ESV (ኢኤስቪ) የ 2017 ዕትም ላይ የሚታየው የቃላት ምርጫ የታሰበበት እንደሆነ ግልጽ ይመስላል፤ ይህም ሴትየዋ ለባልዋ ያላት ፍላጎት አዎንታዊ እንደማይሆን የበለጠ በግልጽ ለማሳየት ነው። ስለዚህ የ 2017 ESV (ኢኤስቪ) ዕትም ፍላጎትዋ **ከባልዋ ጋር ተቃራኒ** እንደሚሆን ይናገራል። እንዲህ አይነቱ አሉታዊ "ምኞት" በዘፍጥረት 4፡7 ላይም ይታያል። በዚያ ጥቅስ ላይ ኃጢአት ቃየንን ለመግዛት ሲፈልግ ነው የምንመለከተው። ማለት ኃጢአት በቃየን ላይ ለመግዛት ሲፈልግ ነው ክፍሉ የሚያትተው። ስለዚህም እዚህም የዘፍጥረት 3 ላይ ተመሳሳይ መልዕክት ያዘለ ይመስላል። ማለትም ሃሳቡ የሔዋን በኃጢአት ምክንያት ባልዋን ለመግዛት የምታሳየው ፍላጎት ይመስላል። በሌላ አነጋገር ከእግዚአብሔር የፍጥረት ሥርዓት ፍጹም የተለየ አካሄድ ማለት ነው! የባልዋን የሥልጣን ቦታ ትመኛለች ማለት ነው። የሱ ረዳት ከመሆን ይልቅ እሷ ግን የሱን የአመራር ቦታውን ትመኛለች ነው። ስለዚህም ኃጢአት ሴቲቱን ከወንዱ ጋር መጀመሪያ ባልታሰበ መንገድ እንድትገናኝ ያደርጋታል። የእንግሊዝኛው New Living Translation (ኒው ሊቪንግ ትርጉም) ይህንን በሚገባ ያንጸባርቃል "ባልሽን ልትቆጣጠሪ ትፈልጊያለሽ እሱ ግን ገዥሽ ይሆናል" ይላልና። ይህ የሔውንና የአዳም ጋብቻ ብቻ የሚነካ አይደለም። ይልቅስ በሁሉም ትዳሮች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው እንጂ። ኃጢአት ትዳርን በእጅጉ ጎድቷልና!

107 በኃጢአት ምክንያት ወንዱ ከሴቲቱ ጋር የሚኖረው ግኑኙነት ከመጀመሪያውኑ ባልታሰበው መንገድ ይሆናል ማለት ነው። እንደ እግዚአብሔር ስጦታና እግዚአብሔር በሰጣቸው ሥራ እንደ እኩል አጋር አድርጎ አይመለከታትም ማለት ነው። ይልቁንም ኃጢአት በአዳም አመራር ሰጪነት ሚናው ላይ የበላይ እንዲሆን አድርጎታል። እንዲህ ዓይነቱ የነገሮች ቅደም ተከተል ለውጥ የሚነካው የአዳምና የሔዋንን ጋብቻ ብቻ አይደለም። ነገር ግን በሁሉም ትዳሮች ላይ ተጽእኖ ለማድረግ የሚተላልፍ ጉዳይ ነው እንጂ። ደግመን ለማስታውስ ያህል ኃጢአት ትዳርን በእጅጉ ጎድቷል!

108 አዳም እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ የሚስቱን ቃል ሰማ።

109 ሮሜ 8፡20–22 ይመልከቱ።

18 እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ።[110]

19 ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤[111] አፈር ነህና ወደ አፈርህ ትመለሳለህና[112]

20 አዳምም ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም አወጣ፤[113] የህያዋን ሁሉ እናት ናትና።[114]

21 እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደርገላቸው፤ አለበሳቸውም።[115]

---

110 በኃጢአት ከመውደቁ በፊት በኤደን ገነት መሥራት ለአዳም ቀላል ነበር። አሁን መሬቱ ለአዳም ቀላል አይሆንም። በሆነ መልኩ መሬቱ መልሶ ይታገለዋል ማለት ነው። በፍጥረት ሁሉ እየደረሰ ያለው እርግማን (ምድሪቱን ጨምሮ!) በክርስቶስ ዳግም ምጻዓት ሙሉ በሙሉ ይነሳል። በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት የክርስቲያን ይፋዊ "ልጅነት" ፍጥረት ራሱ ከመለወጥ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ የጳውሎስን ማብራሪያ በሮሜ 8 ይመለከቱ።

111 ይህ የግጥም ይዘት ያለው ነው፦ "ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ማለት በመጀመሪያ ከታሰበው በተቃራኒው መበስበስ ይሆናል"ይላል።

112 አዳም ከአፈር እንደመጣ ቢያስታውስ ኖሮ የእግዚአብሔርን ቃል በቁም ነገር የሚመለከት ትክክለኛ ትህትና ይኖረው ነበር እናም አዳምና ሔዋን ወደ አፍር ባልተመለሱም ነበር። አዳም ጥገኛ ፍጡር መሆኑን የዘነጋ ይመስላል። በመሆኑም የአዳም ምድራዊ ተፈጥሮ እዚህ ጋ አፅንዖት ተሰጥቶት እንመለከታለን። ንጉሥና ካህን ከመሆን ይልቅ አሁን ተከራይ ገበሬ ሆነ።

113 በመጀመሪያ ዕይታ ሲታይ ሔዋን የሚለው ስያሜ ከቦታው በተያያዘ የወጣ ይመስላል። የሌሎች ፍጥረታት ስም በዘፈጥረት ምዕራፍ 2 ላይ ተከናውኗል። ያ ደግሞ አዳም ከሔዋን ጋር ከመተዋወቁ በፊት ነበር። ከዚህ ውጭ ኣዳም ኃጢአት አልሰራም ነበር። ሔዋንም ስሟ በዚያኑ ጊዜ ማግኘት የነበረባት ይመስላል። ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ ሔዋን አልተሰየመችም። እንዳውም እስከ ዘፈጥረት ምዕራፍ 3 ድረስ አልተሰየመችም ነበር። አዳም ኃጢአት ከሰራም በኋላ ቢሆን የእግዚአብብሔርን ፍጥረታት ስም እዲያወጣ መፈቀዱ አስደናቂ ነው! ይህ የጸጋው ምሳሌ ነው! ከዚህም ባሻገር ሔዋን ከተታለለችም በኋላ "የሕያዋን ሁሉ እናት" የሚል ክብር ያለው ስም መሰጠቷ በሕይወቷ ውስጥ ጸጋን ያሳያል። በግልጽ መረዳት የሚቻለው ምንም እንኳን ኃጢአት ቢሠሩም እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን ፍቅርም ሆነ ኣላማ አለማስወገዱን ነው።

114 የሔዋን ስም ከአዳም የመጣ እንደ እምነት መግለጫ ነው። አዳም ለራሱ ለሚስቱ እና ለእባቡ የተናገረውን የያሕዌን (የእግዚአብሔርን) ቃል ከሰማ በኋላ የሰማውን አንድ ተስፋ ያዘ። እባቡን ስለሚያጠፋ ዘር ሰምቷል። ደግሞም ይህም ዘር ከሔዋን እንደሚመጣ ተረድቷል! ምንም እንኳን ሞት የመጣው በኃጢአት ምክንያት ቢሆንም ሕይወት ደግሞ በሔዋን ዘር በኩል እንደሚመጣ ተገንዝቧል– ሔዋንም "የሕያዋን ሁሉ እናት" እንደምትሆን ገብቶታል! የሔዋን ስም ለአዳም በወንጌል ላይ ያለውን የእምነት ዘር ምሳሌ ነው። አትብሉ የተባልውን ፍሬ በመብላት ሟቾች ቢሆኑም አዳም ግን ሔዋን የሕያዋን እናት እንደሆነች ተገንዝቧል።

የሔዋን ስም ለሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ተስፋ ሊሰጥ ይገባል። በሴቲቱ ዘር ምክንያት (ኢየሱስ!) ሕይወት በእርሱ ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ይመጣልና።

115 አዳምና ሔዋን ቀደም ሲል በራሳቸው መንገድ እንደለበሱ አንባቢው ማስታውስ ይኖርበታል (ዘፍጥረት 3፡7 ይመልከቱ)። ነገር ግን እግዚአብሔር በቸርነቱ ሌላ አዲስ ልብስ ሰጣቸው።እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን **ከእንስሳት ቆዳ የተሠሩ ልብሶችን** እንዳለበሳቸው ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ነው። አዳምና ሔዋን በትክክል እንዲለብሱ አንድ ነገር መሞት ነበረበት! ይህ የወንጌል ታሪክ ምሳሌ ነው። ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ነውና። ኢሳይያስ 1፡18 እና ዮሐንስ 1፡29 ይመልከቱ።

22 እግዚአብሔር አምላክም አለ፡— እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤[116]
አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ ለዘላልም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፤[117]
23 ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክም ከዔድን ገነት አስወጣው፤ የተገኘበትን መሬት ያርስ ዘንድ።[118]
24 አዳምንም አስወጣው ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና
የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ።[119]

---

116 ይህ ጥቅስ “መልካሙንና ክፉውን ማወቅ” ማለት ትክክልና ስህተት የሆነውን ነገር በራስ የመወሰን ችሎታን ለማመልከት ተጨማሪ ማስረጃ ነው። አዳም “እንደ” እግዚአብሔር ነበር ምክንያቱም እሱ ራሱ ስለ ደግና ክፉ ውሳኔ ለመውሰን ችሎ ነበርና። ይህ ደግሞ ሌላ አስከፊ ውሳኔ እንዲወስድ ይገፋፋዋል። ለዚህም ይመስላል እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከገነት ያባረራቸው። አዳማና ሔዋን በራሳቸው መንገድ እንደሚነዱና ከሕይወትም ዛፍ ሊበሉ እነደሚችሉ ደግሞም በዚሁ ምክንያት ለዘላለም በአመፅ እንደሚኖሩ እግዚአብሔር ያውቅ ነበርና። ነገር ግን እግዚአብሔር ከአመጸኛነት ጠበቃቸው!

117 እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከገነት ማባረሩ የጭካኔ ምሳሌ አይደለም። ይልቁንም የምሕረት ምሳሌ ነው እንጂ። እደገና እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በኤደን ገነት ውስጥ እንዲቆዩ ቢፈቅድላቸው ኖሮ በአዲሱ አመጸኛ ተፈጥሮአቸው ምክንያት ከሕይወት ዛፍ ለመብላት ይፈተኑ ነበር (ስለዚህ ይህን እንዲያደርጉ ጊዜው ሳይደርስ በፊት) እንደዚሁም ደግሞ ራሳቸውን በዘላቂና በቋሚ ስብራት በማስገባት ከመጠላልፋቸው በፊት ነው እንዲወጡ የተደርጉት። ስለዚህ ከገነት መወጣታቸው የእግዚአብሔር ጸጋ ምሳሌ ነው።

118 በገነት ውስጥ የአዳምና የሔዋን ታሪክ በዚህ እንዴት እንደ ተጠናቀቀ ልብ በል። “በኤደን ገነት” ታሪክ ውስጥ ከመጀመሪያ መግለጫዎች (ከእኛ እንደ አንዱ” እና “ከመሬት መገኘቱን”) የመሳስሉት እዚህም መጨረሻ ላይ ተደጋግሟል። ይህ የታሪኩ የተደጋገመ መግጫዎች “ማዕቀፍ” የታሪኩ ክፍል ማብቃቱን የሚያሳይ ጽሑፋዊ ፍንጭ ነው። አዳምና ሔዋን አሁን ከገነት ውጪ ናቸው። ስለዚህ አዲስ ታሪክ እየጀመረ ነው። ይህም አዲስ ታሪክ የሚያትተው የሰው ልጅ በግዚአብሔር ላይ ማመጽ መቀጠሉን የሚያሳይ ታሪክ እና ለሰዎች እንደገና ወደ እግዚአብሔር መልካም ቦታ በነፃነት የሚገቡበት መንገድ የሚፈጥር ዘርን ለማምጣት የተደረገ ትግል ነው።

119 አሁን የዔድን ገነት በኪሩቤሎች እየተጠበቀ ነው። እንግዲህ ኪሩቤሎች ቢያንስ ለጊዜውም ቢሆን የዓኤድን ገነትን የመጠበቁን የአዳምን ሥራ ተሰጥቷቸዋል። ኪሩቤል በመገናኛው ድንኳን (እና በቤተ መቅደሱ) መጋረጃ ላይ በጥልፍ መልክ እንደተደረጉ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ስለዚህ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ አሁንም ኪሩቤል ቅድስተ ቅዱሳኑን እየጠበቁ ነበር ማለት ነው። ሆኖም በኢየሱስ ሞት የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ለሁለት ተቀደደ (ማርቆስ 15፡38 ይመልከቱ)። በዚህም ምክንያት ሰዎች በኢየሱስ የእግዚአብሔርን መልካም የጥልፍ ሥራ እንደገና እንዲመለከቱ መደርጉ ምሳሌያዊ ነው። አሁን ኪሩቤል ወደ እግዚአብሔር መገኘት የሚወስደውን መንገድ ወይም ወደ ገነት የሚውስደውን መንገድ እየጠበቁ አይደለም!

# ዘፍጥረት 4

በዘፍጥረት 2 እና 3 አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት የአትክልት ሥፍራ ውስጥ ይኖሩ ነበር። ከገነት ወጪ የሰው ልጆች እንዴት እንደ ኖሩ የተገለጠው በዘፍጥረት 4 ላይ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችንም የፈጥረው በዚህ ቦታ አይደለም! ሰዎች የተፈጠሩት ከርሱ ጋር እንዲኖሩና እንዲያመልኩት ነበርና። በኤደን የነበረው የአትክልት ቦታ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግኑኝነት እንዲያድጉ የሚያደርግ እንደ ቤተመቅደስ ነበር። ይሁን እንጂ በኃጢአት ምክንያት ከዚያ ቦታ ማለትም ከቤተ መቅደሱና ከእግዚአብሔር ፊት ተባርረዋል። አዳምና ሔዋን ከገነት ውጭ እንዲኖሩም መፈቀዱ የእግዚአብሔር ጸጋ (ምሕረት) ማረጋገጫ ነው። ሰዎቹ ምንም እንኳን በእግዚአብሔር ላይ ቢያምጹም እግዚአብሔር ግን በቸርነቱ ከእነርሱ ጋር የነበርውን ግኑኝነት አላቋረጠም። በዘፍጥረት 3 ላይ እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ከተናገረው ቃል በመነሳት አንባቢው ከገነት ውጪ ያለውን ሕይወት አስቸጋሪ እንደሚሆን መገመት ይኖርበታል። ይሁን እንጂ ይህ ምዕራፍ አንባቢው ሊገምተው ከሚችለው በላይ እጅግ የከፉ ሁኔታዎችን ይገልጻል!

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሁለት ዓይነት አምልኮዎችን እንመለከታለ– እውነተኛ አምልኮ (አቤል) እና የሐሰት አምልኮ (ቃየን)። ደግሞም ኃጢአት በሰውና ብሎም በቤተሰብ ላይ የሚያስከትለውን አስከፊ ወጤት እናያለን፤ ቃየን ወንድሙን አቤልን ገድሏልና። በዚህም ምክንያት ቃየን በምድር ላይ ተቅበዝባዥ ሆኖ ለምኖር ተገዷል። እንደዚሁም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተወለዱ ብዙ ሰዎች ከመመልከታችንም በላይ ስለ አንዳንድ ስኬቶቻቸውንም እናነባለን። አንዳንዶች ሙዚቀኞች ናቸው። አናዳንዶች ደግሞ የብረታ ብረት ሠረተኞች ናቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር ስለስኬቶቻችው ምንም አስተያየት ሲሰጥ አንመለከትም። ሰዎች ያለ እግዚአብሔር የሚኖሩ ያህል ነው የሚመስለው! በኋላ በምዕራፉ ውስጥ ስለአንድ ወንድ ልጅ መገደል የሚዘክር ግጥም አለ! ተናጋሪው ሁለት ሚስቶች ያሉት ሰው ነው! ይህ በዘፍጥረት 2 ላይ ከሚታየው የእግዚአብሔር ለአንድ ወንድና ለአንዲት ሚስቱ ካለው የመጀመሪያ ሐሳብ በጣም የተለየ ነው! ደግሞም ይህ በሞት ስለሚደሰተው አስደናቂ ግጥም ከገነት ውጭ በስዎች የተነገረ የመጀምሪያ ግጥም ነው! በዘፈጥረት 3፡15 ላይ የተነገርው የእባቡ ዘር የሚቀጠቀጥበት ተስፋ ሊከስም እንዳለእው ነበልባል ሊጠፋ ተቃርቧል! ሆኖም በምዕራፉ መጨረሻ ላይ አንባቢው የተስፋ ጭላንጭል ይታየው ይሆናል። በመሆኑም የሴትን መወለድ ዜና በዘፍጥረት 3፡15 የተባለውን ዘር ለአንባቢው ሊያስታውሰው ይችላል። እግዚአብሔር የገባውን ኪዳን አልዘነጋም–በመሆኑም በአቤል ምትክ ሌላ ዘር ተተክቷልና! በሰዎች ዘንድ ክፋት ቢኖርም የእግዚአብሔር እቅድ ግን አሁንም አለ። በሙሴ ገለፃ መሠረት አንባቢው ተስፋውን በሴት እና በሴት

ልጆች ላይ እንዲያደርግ ይረዳዋል። ደግሞም የእባቡን ጭንቅላት የሚያደቅቀው ዘር መሆኑንም ያምን ይሆናል። ይሁን እንጂ የሚያሳዝነው ደግሞ ዘሩ ከመምጣቱ በፊት ለረጅም ጊዜ መጠበቅ ይሆናል። በዘፍጥረት 3፡15 ላይ የተገለጸው ዘር በመጨረሻ ከመምጣቱ በፊት በግዚአብሔር ሕዝብ የሚደርስባቸው ብዙ አስከፊ የምጥ ጣር ህመም ይኖራሉ (ይህንን ከዘሩ –ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት የሚሆነው አስከፊ የምጥ ጣር ህመም በተመለከ ራዕይ 12፡1–6 ይመልከቱ)።

# ዘፍጥረት 4[120]

1 አዳምም ሚስቱን ሔዋንን አወቀ ፀነሰችም ቃየንንም ወለደች። እርስዋም፦ ወንድ ልጅ ከግዚአብሔር አገኘሁ አለች።[121]

2 ደግሞም ወንድሙን አቤልን ወለደች። አቤልም በግ ጠባቂ ነበር፤[122] ቃየንም ምድርን የሚያርስ ነበረ።

---

[120] ይህ ምዕራፍ በእባቡ ዘር እና በሴቲቱ ዘር ማካከል በሚካሄደው ረጅሙ ጦርነት ውስጥ ስለመጀመሪያውን ፍልሚያ ይናገራል (ዘፍጥረት 3፡15 ይመልከቱ)። ቀድሞውንም "ጠላትነት" በእባቡ ዘር እና በሴቲቱ ዘር መካከል ባለው ግኙኝነት ውስጥ ይታያል። ሙሴ አቤል የሴቲቱ ዘር ነው ቃየን ደግሞ የእባቡ ዘር ነው አላለም። አንባቢው ይህንን በራሱ ማወቅ አለበት። ሆኖም ግን አንባቢው ከሁለቱ **የትኛው እንደ እባብ እንደሆነ ወይም የትኛው የእግዚአብሔር አምሳል እንደተሸከም ማወቅ እንዲችል ፍንጮች አሉ**። (1) ለአንባቢው ያሕዌ "ለቃየንና ለመሥዋዕቱ ደንታ እንደሌለው" ተነግሮታል፣ (2) እግዚአብሔር ቃየንን ኃጢአት በደጅ እንደ ምታድባ ነገር ግን ሊቆጣጠረው እንደሚገባ ነግሮታል፣ (3) እግዚአብሔር ቃየንን "መልካም ቢያደርግ" እንደሚቀበለው ነግሮታል፤ ይህም ማለት ደግሞ ቃየን ከዚህ በፊት መልካም ሲያደርግ አልነበርም ማለት ነው፣ (4) ምንም እንኳን እግዚአብሔር ምንማድረግ እንዳለበት ቢነግረውም ቃየን ግን የእግዚአብሔርን መመሪያ ለመታዘዝ አልሞከረም፣ (5) ቃየን ወንድሙን ዋሽቶ ነው የገደለው፣ (6) ቃየን ወድሙንም መግደሉን ደግሞ ዋሽቷል። እነዚህ ነገሮች ሁሉ ስናገናዝብ በጣም እባባዊ ናቸው! ቃየን የእባቡ ዘር ነው ተብሎ የሚታሰብበት ተጨማሪ ማስረጃ በአዲስ ኪዳንም ውስጥ ይገኛል (1 ዮሐንስ 3፡12 እና ይሁዳ 11 ይመለከቱ)። **አቤል ደግሞ የሴቲቱ ዘር መሆኑን የሚያሳዩ ፍንጮች የሚከተሉት ናቸው**፦ (1) አቤል "ከመንጋው በኩሩና ከስቡ" አቀረበ፤ ይህም አቤል ሆን ብሎ ከሁሉ የተሻለውን እንደመረጠ የሚያመለክት ይመስላል። (2) ጽሑፉ የሚያመለክተው እግዚአብሔር "ለአቤልና ለመሥዋዕቱ ግድ እንደነበረው" ነው። አቤል በእግዚአብሔር ፊት መልካም ያደርግ ነበር። አቤል የሴቲቱ ዘር እንደሆነ የሚያሳዩ ተጨማሪ ማስረጃዎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ (ማቴዎስ 23፡ 35፣ ሉቃስ 11፡51፣ ዕብራውያን 11፡4 እና 1 ዮሐንስ 3፡12 ይመልከቱ)። በዚህ ምዕራፍ የእባቡ ዘር (ቃየን) የሴቲቱን ዘር (አቤልን) ድል አድርጓል። አንባቢው የምዕራፉ መጨረሻ እስኪደርስ ድረስ የተውሰነ ተስፋ እንኳን አያገኝም። ይሁን እንጂ ይህ በእባቡ ዘርና በሴቲቱ ዘር መካከል ያለው ጦርነት በእጅጉ ከዚህ ምዕራፍ በላይ ይዘልቃል።

[121] ሔዋን በቃየን መወለድ በጣም ተደንቃ ነበር። በዘፍጥረት 3፡15 ላይ ዘርን በተመለከተ በተነገረው ተስፋ መሰረት፣ ቃየን ምናልባት ስለ ዘር የተነገረው ተስፋ ቃል ፍጻሜ ሊሆን ይችላል ብላ አስባ ይሆናል። ለዚህም ይመስላል **"ወንድ ልጅ ከግዚአብሔር አገኘሁ"** ያለቸው። እንደገና የእባቡን ራስ የሚቀጠቅጥው ዘር ይሆናል ብላ አስባም ሊሆን ይችላል። ሔዋን ወደፊት የሚሆነውን አታውቅም ነበርና። ማለትም ቃየን እንደ ዘርዋ እንደማይቆጠር አታውቅም ነበር ማለት ነው። እንደ እባቡ ዘር የሚቆጠር ነበርና (1 ዮሐንስ 3፡12 ይመልከቱ)። ከዚህ በተጨማሪ እባቡ የሚቀጠቅጠው ዘር (ኢየሱስ) ከመወለዱ በፊት እጅግ ብዙ ትውልዶች እንደሚኖሩ አታውቅም ነበር። እውነተኛውን ዘር ከመወለዱ በፊት ብዙ ስቃይና መከራ ገና መምጣት ነበረበትና።

በዘፍጥረት 4፡1 ላይ ያለውን ሔዋን ቃየንን መውለድዋን የገለጸችው **"ወንድ ልጅ ወይም ሰው"** ብላ ጠራችው ደግሞም በዘፍጥረት 4፡25 ላይ ሔዋን የሴትን መወለድ ስትናገር የሰጠችውን መግለጫ **"ሌላ ዘር"** የሚለውን ይመልከቱ። ይህ ለአንባቢው ፍንጭ የሚሰጥ ነው። በቃየን ድርጊት ላይ በመመስረት ሔዋን ስለ ቃየን ያላትን አስተያየት እንደተለወጠ ግልጽ ነው። በዘፍጥረት 4፡25 ላይ ግን ሔዋን አቤልንና ሴትን ሁለቱም "ዘር" ብላ ጠራቻቸው። **ይህ ማለት ቃየንን እንደ ዘርዋ አልቆጠረችውም ነበር ማለት ነው። እስዋም የእባቡ ዘር እንደሆነ አድርጋ የቆጠረችው ይመስላል።**

እዚህ ጋ የእግዚአብሔርን ስም ደግሞ ማስተዋል ያስፈልጋል። እሱ በቀላሉ "ያህዌ" (እግዚአብሔር) ተብሎ ይጠራል። ነገር ግን በዘፍጥረት 2፡4–3፡24 ላይ በነበረው መሠረት ያህዌ አሎሂም (እግዚአብሔር አምላክ) ተብሎ ከመጠራት ይልቅ አሁን አንባቢው ለዚህ አጭር ስም ተዘጋጅቷል እና አዲስ እና የተለየ አምላክን እንደሚያመለክት ያውቃል ማለት ነው።

[122] አቤል እረኛ ነው። በጎችና እረኞች በኋለኞቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። የኋለኞቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ደግሞ የእግዚአብሔር ሰዎች እንደ በጎች እንደሆኑ ይናገራሉ። እንደ በጎችም የእግዚአብሔር ሰዎች ሊሰቃዩ

3 ከብዙ ቀን በኋላም ቃየን ከምድር ፍሬ ለግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረበ፤

4 አቤልም ደግሞ ከበጎቹ በኩራትና ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፤

5 ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም።[123] ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ።

6 እግዚአብብሔርም ቃየንን አለው ለምን ተናደድህ? ለምንስ ፊትህ ጠቆረ?

7 መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች፤ ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት።[124]

8 ቃየንም ወንድሙን አቤልን፦ ና ወደ ሜዳ እንሂድ አለው በሜዳም ሳሉ ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሣበት ገደለውም።[125]

9 እግዚአብሔርም ቃየንን አለው። ወንድምህ አቤል ወዴት ነው?[126] እርሱም አለ፦ አላውቅም የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን?

10 አለውም፦ ምን አደረግህ? የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል።[127]

11 አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድርም ላይ አንተ የተረገምህ ነህ።

---

ተዘጋጅተዋል። እንዳውም "ወደ መታረድ የሚነዱ" በጎች ተብለው ተገልጸዋል። ኢየሱስ በርግጥም "ወደ መታረድ የተነዳ" የመጨረሻው በግ ነውና (ራዕይ 5፡6–14 ይመልከቱ)። ከዚህም ባሻገር የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች ከእረኞች ጋር ተመሳስለዋል። ይህ በድጋሚ በኋለኞቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ዋና ጭብጥ በመሆን የሚጫወተው የጭብጦች የመጀመሪያ ፍንጭ ነው። መዝሙር 44፡11፤ ኢሳይያስ 53፡7፤ ሮሜ 8፡36 እና 1 ጴጥሮስ 5፡1–5 ይመልከቱ።

123 እግዚአብሔር የቃየንን መስዋዕት ለምን "እንዳልተመለከተ" ደግሞም ለምን እንደሆነ ለአንባቢ አልተነገረም። ሙሴ ይህ የሆነው ለምን እንደሆነ ለአንባቢዎቹ መንገር አልመረጠም። ይሁን እንጂ አዲስ ኪዳን ግን ምክንያቱን ይነግረናል። ቃየን መስዋዕቱን በእምነት አላቀረበም (ዕብራውያን 11፡4 ይመልከቱ)። አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር የቃየንን መስዋዕት ያለተመለከተው ደም ያላካተተ መስዋዕት ስለሆነ ነው ይላሉ። ይሁን እንጂ መታወቅ ያለበት ነገር ቢኖር ደምም ሳይጨምር በእሥራኤላውያን ዘንድ የቀረበ የእህል ቁርባን ነበረና።

124 ይህ ጸጋ ነው! ቃየን ኃጢአት መሥራት አያስፈልገውምና እግዚአብሔር ደግሞ መውጫውን እያስተካከለለት ነበር። ይሁን እንጂ እሱ ግን ከኃጢአቱ መውጫ መንገድ አይፈልግም። ኃጢአት በመስራት መቀጠል የሚፈልግ ይመስላል።

125 ዕብራውያን 11፡4 ይመልከቱ። የዕብራውያን ጸሐፊ አቤል ቢሞትም እንኳን አሁንም እየተናገረ መሆኑን አንባቢዎቹ እንዲያውቁ ይፈልጋል። እምነቱ የዘላለም ሕይወት እንደ ሰጠው (ዮሐንስ 3፡16 ይመልከቱ) ለዚህ ማሳያ ይመስላል እንደዚሁም ደግሞ እሱ በተግባሩ አሁንም ለሰዎች ስለ ጽድቅ እየተናገረ ይገኛል። በዚያ ዘመን የአቤል ሕይወት አጭር ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ አሁን ግን በክርስቶስ ለዘላለም ይኖራል።

126 ያህዌ (እግዚአብሔር) አዳምና ሔዋን ሲበድሉ አንድ ጥያቄ ጠየቃቸው። አሁንም እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እያወቀ ነው የጠየቃቸው። ሆኖም ግን ሰዎቹ ለእግዚአብሔር ምላሽ ሲሰጡ የሚሰጡትን መልስ መስማት ለአንባቢ ደግሞ ይጠቅማል። ኃጢአት በሰዎች ላይ በማታለል እንዴት እንደሚሰራ እነመለከታለ።

127 የዕብራውያን ጸሐፊ የክርስቶስ ደም ከአቤል ደም የተሻለ ቃል መናገሩን ይናገራል (ዕብራውያን 12፡24 ይመልከቱ)። በዚህም የዕብራውያን ደራሲ የአቤል ደም ለፍርድ ወደ እግዚአብሔር እየጮኸ እንደ ነበረ ያመለክታል። የክረስቶስ ደም ግን ስለ ምሕረት ወደ እግዚአብሔር እየጮኸ ነው። ምሕረት ደግሞ ከፍርድ ይልቅ "የሚሻል ቃል" ነውና።

12 ምድርም ባረስህ ጊዜ እንግዲህ ኃይልዋን አትሰጥህም፤ በምድርም ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ
ትሆናለህ[128]
13 ቃየንም እግዚአብሔርን አለው። ኃጢአቴ ልሸከማት የማልችላት ታላቅ ናት።
14 እነሆ ዛሬ ከምድር ፊት አሳደድኸኝ ከፊትህም እሰወራለሁ፤ በምድርም ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ
እሆናለሁ፤ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገለኛል።
15 እግዚአብሔርም እርሱን አለው፦ እንግዲህ ቃየንን የገደለ ሁሉ ሰባት እጥፍ ይበቀልበታል።
እግዚአብሔርም ቃየንን ያገኘው ሁሉ እንዳይገለው ምልክት አደረገለት።
16 ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፤ ከዔድንም ወደ ምሥራቅ በኖድ ምድር ተቀመጠ።[129]
17 ቃየንም ሚስቱን አወቀ ፀነሰችም ሄኖሕንም ወለደች።[130] ከተማም ሠራ የከተማይቱንም ስም በልጁ ስም
ሄኖሕ አላት።[131]
18 ሄኖሕም ጋይዳድን ወለደ፤ ጋይዳድም ሜኤልም ወለደ፤ ሜኤልም ማቱሣኤልን ወለደ፤ ማቱሣኤልም
ላሜሕን ወለደ።
19 ላሜሕም ለራሱ ሁለት ሚስቶችን አገባ፤[132] የአንዲቱ ስም ዓዳ የሁለተኛይቱም ስም ሴላ ነበረ።
20 ዓዳም ያባልን ወለደች፤ እርሱም በድንኳን የሚቀመጡት የዘላኖች አባት ነበረ።
21 የወንድሙም ስም ዩባል ነበረ፤ እርሱም በገናንና መለከትን ለሚይዙ አባት ነበረ።[133]

---

128 ቃየን እንደ ወላጆቹም በእግዚአብሔር ፍርድ ተላልፎበታል። እግዲህ እዚህ ከኤደን ገነት ውጭ ያለው ሕይወት ምንም እንኳን አስቸጋሪ ቢሆንም፤ በእግዚአብሔር ቸርነት ምክንያት ዘላቂ እንደሆነ እንመለከታለን። አስቸጋሪነቱ የምናወቀው እግዚአብሔር ለቃየን ምድር ባረሰ ጊዜ ኃይልዋን እንደማትሰጠው (የእግዚአብሔር በረከት) ከቃየል እንደተከለከለ ስለሚናገር ነው። ሆኖም እግዚአብሔር ከኤደን ገነት ውጪ ለሚኖሩ ሰዎች አሁንም ቸር ነው።

129 ኖድ የሚለው ስም አንድ ሰው እንዳይያዝ ሸሽቶ የሚደበቅበት ሥፍራ እንደማለት ነው።

130 በቃየን ሕይወት ላይ እንደሚታየው ሁሉ አንባቢ የቃየን ዘሮች የእግዚአብሔርን መልክ እንዲመስሉ መጠበቅ የለበትም (ዘፍጥረት 1፡28 ይመልከቱ)። የቃየን ዘሮች ልክ እንደ ቅድመ አያታቸው የአባቡን መልክ መምሰላቸው ምንም አያስደንቅም። ምንም እንኳን የቃየን ዘሮች ከምድራዊ እይታ አንጻር ታላላቅ ነገሮችን ቢያከናውኑም ፍሬያማ እንዲሆኑና እንዲበዙ እንዲሁም ምድርን በአምሳሉ እንዲሞሏት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተልዕኮ አይታዘዙምና።

131 ሰዎቹ ፍሬያማ እየሆኑና እየበዙም ነው (ዘፍጥረት 1፡28 ይመልከቱ)። ነገር ግን እነሱ እግዚአብሔር ባላቸው መንገድ እየተጓዙ አይደለም። በመሆኑም እግዚአብሔርን መምሰል በእነርሱ እየተባዛ አይደለም ማለት ነው። ይልቁንም እባቡ የመምሰል ማንነት እየበዛ ነው። ይህም በግልጽ የሚታየው ከቃየል ዘሮች ጋር የተያያዘው ግድያና ክፋት ልብ ማለት ያስፈልጋል።

132 ቀደም ሲል ሰው ረዳት እንደሚያስፈልገው አይተናል። እዚህ ጋ ደግሞ እግዚአብሔር ለጋብቻ ያለውን የመጀመሪያውን ንድፍ ከተብራራና ከተከበረ ከሁለት ምዕራፎች በኋላ ጋብቻ ውስጥ የግዚአብሔርን መልካም ዓላማዎች የሚያጣምሙ ሰዎች ተከሰቱ። ስለዚህ ሰዎች በትዳር ውስጥ ሁለት ሚስቶችን ማግባት ጀመሩ ማለት ነው!

133 በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የተከናወኑ ታላላቅ ስኬቶች– የእርሻ፣ የሙዚቃ እና የብረታ ብረት ስራዎች እድገት– በሦስት አጫጭር ቁጥሮች ውስጥ ተጠቅሰዋል። ደራሲው (ሙሴ)ብዙም አስፈላጊ ስላልሆኑ በእነርሱ ላይ እምብዛም አያተኩርም።

22 ሴላም ደግሞ ከናስና ከብረት የሚቀጠቀጥ ዕቃን የሚሠራውን ቱባልቃይንን ወለደች። የቱልባቃይንም
እኅት ናዕማ ነበረች።
23 ላሜሕም ለሚስቶቹ ለዓዳና ለሴላ አላቸው፡-[134] እናንት የላሜሕ ሚስቶች ቃሌን ስሙ ነገሬንም
አድምጡ፤ እኔ ጎልማሳውን ለቁስሌ ብላቴናውንም ለመወጋቴ ገድዬወለሁና፤
24 ቃየንን ሰባት እጥፍ ይበቀሉታል፤ ላሜሕን ግን ሰባ ሰባት እጥፍ ይበቀሉታል።[135]
25 አዳም ደግሞ ሚስቱን አወቀ ወንድ ልጅንም ወለደች። ስሙንም፡- ቃየን በገደለው በአቤል ፋንታ
እግዚአብሔር ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል ሴት አለችው።[136]
26 ለሴት ደግሞ ወንድ ልጅ ተወለደለት ስሙንም ሄኖስ አለው በዚያን ጊዜም በእግዚአብሔር ስም
መጠራት ተጀመረ።[137]

---

እንግዲህ አንባቢ ደራሲው በሚያተኩርባቸው ነገሮች ላይ እሱም ትኩርት ሊያደርግ ይገባል። የደራሲው ትኩረት በአብዛኛው ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖራቸው ግኑኝነትና እርሱንም በማምለካቸው ላይ የሚያተኩር ነው።

134 ይህ ከኤደን ገነት ውጪ በሰዎች የተነገረ የመጀመሪያ ግጥም ነው። ከወድቀት በፊት ከተነገረው ከመጀመሪያ ግጥም (ዘፍጥረት 2፡23) ጋር ያወዳድሩ። በመጀመሪያው ግጥም አዳም በሔዋን ደስ ተሰኝቶ እንደሥጋው ቆጥሯት እንደሚንከባከባት ቃል ገባ። በዚህ ግጥም ግን ላሜህ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ጎልማሳውን ገድሎ ሲኩራራ እና በዚህ ምክንያትም እግዚአብሔር እንደ ጠበቀው ሲናገር ይስተዋላል!

135 ሰዎች በኃጢአት ምክንያት ምን ያህል እንደዘቀጡ የሚያሳይ ሌላ ምሳሌ ነው። ላሜህ ትክክልና ስህተት በሆነው ነገር ግራ ገብቶታል፤ ጎልማሳውንም በመግደሉ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር አብሮ ደስ ያለውና የሚጠብቀውም መስሎታል።

136 አንባቢው ሙሉ ምዕራፍ እኪያነብ ምንም የተስፋ ጭላንጭል አይታየውም ነበር። እዚህ ጋ ግን ተስፋ ይታያል። ሔዋን ሌላ ዘር ልትወልድ ነውና። አሁንም ቃሉን የሚጠብቅ እና እባቡንም የሚያደቅቀውን እንደዚሁም አለምን ከክፉ የሚያድነውንም ዘር እንዲሰጥ እግዚአብሔርን እንደምትፈልግ አሳይታለች። በሔዋንም ቃል ላይ በመመስረት ሔዋን ቃየንን እንደ እውነተኛ ዘር እንደማትቆጥረው ግልጽ አድርጋለች። ይልቅስ ቃየንን የእባቡ ዘር እንደሆነ አድርጋ ቆጥራዋለች (ዘፍጥረት 3፡15 ይመልከቱ)።

137 ይህ ጥቅስ ለሴት ዘሮች ትኩረት እንድንሰጥ ፍንጭ የሚሰጥ ነው ምክንያቱም የሴቲቱ ዘር ተደርገው ይቆጠራሉና። ይህም በዘፍጥረት 3፡15 ላይ ካለው እባቡን ከሚቀጠቅጠው የሴቲቱ ዘር ቃል ኪዳን ጋር ያገናኛቸዋልና። ደግሞም የምዕራፍ 4 መጨረሻ (በዚያን ጊዜ) በምድር ላይ ከነበሩት ሰዎች እግዚአብሔርን የሚፈልገው የትኛው እንደሆነ ያሳየናል። የቃየን ዘሮች እግዚአብሔርን አይፈልጉም ነበር። በአንጻሩ ደግሞ ሰውን እየገደሉ ግጥም በመግጠም ይኩራሩ ነበር! እዚህ ጋ ልክ እንደ ሔዋንም አንባቤው የሔዋንን አዲሱ ዘር በተስፋ እየተመለከተ ነው የሚያነበው። እንግዲህ የሴቲቱ ዘር ከዚህኛው ማለትም ከሴት ወገን ከሆኑቱ ይመጣል።

ደግሞም ይህ ጥቅስ ምንም እንኳን አሁን ምድርን እየሞላ ያለ ግድያ እና ጥላቻ ቢኖርም እግዚአብሔር ግን ከሰዎች ልጆች ጋር ያለውን ጉዳይ አሁንም እንዳልጨረሰ ያሳያል። እንደዚሁም ደግሞ ምንም ትንሽ ቁጥር ቢሆንም እንኳን አሁንም ግን እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ሰዎች አሉ፤ ጸጋው እስከ አሁን እየሰራ ነውና።

## ራእይ 21–22:5
## አዲስ ሰማይና ምድር እና
## አዲሲቱ ኢየሩሳሌም

ይህ የራእይ ክፍል በብዙ መልኩ ከዘፍጥረት 1–3 ካለው ጋር የተያያዘ ነው። እንዲያውም ሰባኪ ወይም አስተማሪ የሆነ ሰው ይህን የዮሐንስ ራእይ ክፍል ከማንበቡ በፊት የመጀምሪያዎቹን ሦስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ቢያነብ ትልቅ እገዛ ይሆንለታል። ይሁን እንጂ ይህን የራእይ ክፍል ከዘፍጥረት 1–3 ጋር የተያያዘ ቢመስለም በሌላ በኩል ደግሞ ከዘፍጥረት 1–3 ካለው ክፍል ጋር በጣም የተለያየም ነው። በዚህ በራእይ ላይ አዲሱ አዳም (ኢየሱስ) እና ሙሽራይቱ (ቤተክርስቲያን) በአዲስ ኤደን ገነት ተቀምጠዋል። እዚህ ጋ የተገለጸው ገነት ትንሽ ቦታ አይደለም። ይልቁንም በጣም ትልቅ ነው! አዲሱ አዳምና ሙሽራዋ እባቡን አሸንፈዋል! እዚህ እርግማን የለም። እንባ የለም። ሞት የለም። ሁሉም ነገር የሚያብብ ነው። የእግዚአብሔርም ማደሪያ በሰዎች መካከል ነው!

ይህ ስለምጽዓት የተጻፈ ጽሑፍ መሆኑን አንባቢው መረዳት ይኖርበታል። ዮሐንስ አሁንም በጽሁፉ ውስጥ ምልክቶችን እየተጠቀመ ነው። ስለዚህ አንባቢው ስለ ምልክቶቹና እንደዚሁም ምልክቶቹ ምን ሊወክሉ እንደሚችሉ በጥንቃቄ ማሰብ ያስፈልገዋል። ከእነዚህም ምክልክቶች መካከል አብዛኛዎቹ የተወሰዱት ከፍጥረት 1–2 ካለው ክፍል ነው። ሌሎች ደግሞ የተውሰዱት ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች (በተለይም ከብሉይ ኪዳን) ነው።

ለምሳሌ ዮሐንስ ከተማ ሲለካ እንመለከታልን እሷም ፍጹም የሆነች የወርቅ ኪዩብ ናት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ብቸኛው ፍጹም የወርቅ ኪዩብ የነበረው በጥንታዊቷ ቤተመቅደስ ውስጥ ቅድስተ ቅዱሳን ነበር! ያ ትንሽ የተቀደሰ "ሥፍራ" ነበረ፤ ነገር ግን ዙሪያው ደግሞ የተከበበው ብዙ ባልተቀደሰ ሥፍራ ነበር። በአዲሱ ሰምይና በአዲሱ ምድር ግን ሁሉም ነገር የተቀደሰ ነው! እግዚአብሔርም በሁሉም ሥፍራ ይከበራልና!

በጥንቱ ዋናው ቅድሰተ ቅዱሳን ውስጥ ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነበር የሚገባው። በዚህ አዲሱ ቅድስተ ቅዱሳን ግን ሁሉም ሰዎች ቅዱሳን ስለሆኑ ሁሉም ሰዎች መግባት ይችላሉ! ምክንያቱም ሰዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር በነፃነት መገናኘት ይችላሉና። በዚህ በራዕይ ክፍል ውስጥ ያሉትን ምልክቶች ለአብያተ ክርስቲያናት እርዳታ፣ ማበረታቻ እና ጥንካሬ ለማምጣት የታሰቡ ናቸው። ይህ ማለት ሰባኪዎች ወይም አስተማሪዎች

እነዚህን ምልክቶች በጥንቃቄ ማጥናት እና ሕዝቡንም ከምልክቶቹ በስተጀርባ ያለውን ትርጉም በጥልቀት እንዲያስብ መርዳት ይኖርባቸዋል። በዚህ ጥቅሶች ውስጥ ያሉትን ምልክቶች ከእግዚአብሔር ለአብያተ ክርስቲያናት የተሰጡ ጸጋዎች ናቸው። በእነዚህ ከባድ የመከራ ጊዜያት አንባቢው እንዲጸና ይረዱታልና።

## ራእይ 21

1 አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፤ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፤[138] ባሕርም
ወደ ፊት የለም።[139]

2 ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ[140] ተዘጋጅታ ከሰማይ
ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።[141]

---

[138] ኢሳይያስ 65፡17–25፣ 66፡22–23 እና 2 ጴጥሮስ 3፡13 ይመልከቱ። ፊተኛው ሰማይና ምድር ሲያልፉ እርግማኑም ያልፋል (ዘፍጥረት 3፡17 እና ራእይ 22፡3 ይመልከቱ)! በተጨማሪም ሮሜ 8፡18–25 ይመልከቱ። በዚህ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ "የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በናፍቆት" ስለሚጠባበቁት አሁን ስላለው ፍጥረት ይናገራል። ይህ ክስተት ሲከሰት (በዳግም ምጽአት) ያን ጊዜ "ፍጥረት ራሱ ድግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃ ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው።"

ራእይ 21–22ን ከማንበብ በፊት ዘፍጥረት 1–3ን ማንበብ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም እነዚህ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጣም ተመሳሳይ ቢሆኑም ደግሞ በጣም የተለያዩ ናቸውና።

[139] ይህ ምሳሌያዊ አባባል ነው። ባሕር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከፍርድ ትርምስ እና አደጋ ጋር የተያያዘ ነው። ከባሕር ጋር የተያያዘው አደጋ አንዱ ምሳሌ አውሬው "ከባሕር መውጣቱ" ነው (ራእይ 13፡1)። በአዲሱ ሰማይና ምድር አደገኛ ነገሮች የሚኖሩበትና የሚደበቁበት ቦታ አይኖርም። ምድር ሁሉ በመልካምነት ትሞላላችና። እንደዚሁም ደግሞ ባሕር ከኃጢአት ጋር የተያያዘ ነው። በራእይ ውስጥ የባቢሎንን ምርቶች የሚነግዱ ነጋዴዎች በባህር ላይ ይጓጓዙ ነበር (ራእይ 18፡15–19 ይመልከቱ)። በአዲሱ ሰማይና አዲስ ምድር ከባቢሎን ጋር የንግድ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች አይኖሩም። ባቢሎንና ከባቢሎን ጋር የተገናኘ ነገር ሁሉ ይጠፋልና።

[140] ኢሳይያስ 61፡10 ይመልከቱ።

[141] ዮሐንስ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ወደ ምድር ስትወርድ አይቷል። ይህ የሚያሳየው ከዳግም ምጻት በኋላ "ሰማይ" ከዚህ ምድር ርቆ እንደማይገኝ ነው። ይህም ማለት ሰማይም በምድር ላይ ይሆናል ማለት ነው። እንዳውም ሰማይና ምድር ይጣመራሉ። እግዚአብሔርም ከሕዝቡ ጋር ያድራልና! እውነተኛይቱ የእግዚአብሔር ከተማ ከክርስቶስ ዘመን በፊትም የቅዱሳን ተስፋ ነበረች። ዕብራውያን 11፡10–16 ን ይመልከቱ። የዕብራውያን ጸሐፊ እንደገለጸው አብርሃም "መሠረት ያላትን እግዚአብሔር የሠራትና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና። ደራሲው በመቀጠል "በእምነት ስለሞቱ" ስለሌሎች ይናገራል። እነዚህ ሰዎች እንደ ጸሐፊው ከሆነ "የትውልድ አገር ይፈልጉ ነበር።" ጸሐፊው በመቀጠል "የተሻለ አገር ማለትም ሰማያዊ አገር ይመኙ ነበር ይላል። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ አያፍርም፤ ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና። ነቢያትም ስለዚህ ቦታ ጽፈዋል (ኢሳይያስ 2፡2–5፣60፡15–22፣ ሕዝቅኤል 20፡40–44፣ ሶፎኒያስ 3፡14–20 እና ዘካሪያስ 1፡14–17 ይመልከቱ)። የዛሬ ቅዱሳንም ቢሆን እነዚህን የቀደሙት ቅዱሳን ሊመስሉና አዲሲቷንም ኢየሩሳሌም መናፈቅ ይኖርባቸዋል (ዕብራውያን 13፡14 ይመልከቱ)። እነዚህ ስለ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚናገሩ ጥቅሶች ቤተ ክርስቲያንን በቅድስና እንድትመላለስና ከባቢሎን እንድትርቅ ሊያደርጓት ይገባል። አሁንም ቢሆን ቅዱሳን ራሳቸውን የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ዜጎች እንደሆኑ ይቁጠሩ (ገላትያ 4፡26፣ ፊልጵሲዩስ 3፡17–21 እና ዕብራውያን 12፡22–24 ይመልከቱ)። መዝሙር 107 የእግዚአብሔር ሕዝብ "ከምሥራቅና ከምዕራብ ከሰሜንና ከደቡብ" (መዝሙር 107፡3) ወደ "ሚኖሩበት ከተማ (መዝሙር 107፡ 7) እንደ ሄዱ ታሪክ ይናገራል።

3 ታላቅም ድምጽ ከሰማይ፡- እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል
እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤[142]
4 እንባዎችንም ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ኀዘንም ቢሆን ወይም
ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም የቀደመው ሥራዓት አላፎአልና ብሎ
ሲናገር ሰማሁ።[143]
5 በዙፋኑም የተቀመጠው፡- እነሆ ሁሉን አዲስ አድርጋልሁ አለ።[144] ለእኔም፡- እነዚህ ቃሎች የታመኑና
እውነተኛዎች ናቸውና ጻፍ አለኝ።
6 አለኝም፡- ተፈጽሞአል። አልፋና ያሜጋ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ
ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣልሁ።[145]
7 ድል የሚነሣ[146] ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።[147]
8 ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍሰ ገዳዮችንም የሴሰኛዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ
የሐሰተኛዎችንም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለትኛ ሞት ነው።[148]

---

142 እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር እንደሚኖር የገባው ቃል የእግዚአብሔርን ሕዝብ በቅድስና እንዲሄዱ ሊያበረታታ ይገባል። ዘሌዋውያን 26፡ 11–12፤ ኤርሚያስ 31፡1፤ ሕዝቃኤል 37፡27፤ ዘካሪያስ 2፡6–12 እና 2 ቆሮንቶስ 6፡16–18 ይመልከቱ)።

143 ራእይ 7፡17 እና ኢሳይያስ 25፡8 ይመልከቱ። "የቀደመው ሥራዓት አላፎአልና" ማለት ከኃጢአት እና እርግማን ጋር የተያያዘው ሁሉ በዚህ ጊዜ ያልፋል ማለት ነው።

144 2 ቆሮስቶስ 5፡17 ይመልከቱ። በክርስቶስ የሚታመኑ ሁሉ አዲስ ፍጥረት ናቸው። ነገር ግን በውስጥ ያለው አዲስነት የእግዚአብሔር ከፊል ስጦታ ብቻ ናቸው። ገና ሁሉንም ነገር አዲስ ለማድረግ ቃል ገብቷልና።

145 ስለ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም የሚናገረው ይህ ክፍል ሰዎች እግዚአብሔርን "እንዲጠሙ" ያድርጋል ተብሎ ይጠበቃል። እግዚአብሔር ደግሞ የተጠሙ ሁሉ እንደሚረኩ ቃል ገብቷል። ኢሳይያስ 55፡1 እና ዮሐንስ 7፡37 ይመልከቱ።

146 አብያተ ክርስቲያናት ማሸነፍ አለባቸው። ራእይ 2፡7፣ 11፣ 17፣ 26 እና 3፡5፣ 12፣ 21 ይመልከቱ።

147 ይህ ከ 2 ሳሙኤል 7፡14 የተወሰደ ማጣቀሻ ነው። አንባቢ ማስታወስ ያለበት ለጌታ ለኢየሱስ የተገቡት ተስፋዎች ቅዱሳንም "በእርሱ ስላሉ" ለእነርሱም ተፈጻሚ መሆናቸውን ነው። አንባቢ 2 ሳሙኤል 7፡1–17 ን በጥንቃቄ በማንበብ መመርመር ይገባዋል።

148 በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ውስጥ ኃጢአተኞች ሥፍራ የላቸውም። በዚህ ጥቅስ ውስጥ እንደ ኃጢአተኛ የተቆጠሩትን ሰዎች ሁሉ በጥንቃቄ ማጤን አስፈላጊ ነው። "ነፍሰ ገዳዮች" ብቻ አይደሉም ከአዲሲቷ ኢየሩሳሌም የተገለሉት። ሌሎችም ትንንሽ ኃጢአት የሰሩ የሚመስሉ እንደ "የሚፈሩ" እና "የማያምኑም" የመሳሰሉት አይካተቱምና። ይህ የእግዚአብሔር ቸር የሆነ ማስጠንቀቂያ ነው። **እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በትኩረት ይከተታላልና።** ራሳቸውን ቅዱሳን ብለው የሚጠሩ ሰዎች በራእይ መጽሐፍ በተገለጸው መሠረት በእውነት እያሸነፉ እንደሆነ ሕይወታቸውን መመርመር አለባቸው። **ድል ለሚነሱ ብቻ** አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ርስታቸው ይሆናልና (ራእይ 2፡7፣ 11፣ 17፣26፤ 3፡5፣ 12 እና 21 ይመልከቱ)። ሌላው የተቀረው ሁሉ ወደ እሳት ባሕር ይጣላል ማለት ነው (ራእይ 20፡11–15 ይመልከቱ)። በተጨማሪም ማቴዎስ 25፡31–46 ይመልከቱ።

9 ሰባቱም ኋለኛዎች መቅሰፍቶች የሞሉባቸውን ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ፡- ወደዚህ ና የበጉንም ሚስት ሙሽራይቱን አሳይሃለሁ ብሎ ተናገረኝ።[149]

10–11 በመንፍስም ወደ ታላቅና ረጅም ተራራ ወሰደኝ፤[150] የእግዚአብሔርም ክብር ያለባትን ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አሳየኝ፤[151] ብርሃንዋም እጅግ እንደ ከበረ ድንጋይ እንደ ኢያስጲድ ድንጋይ ሆኖ እንደ ብርሌ የጠራ ነበረ፤

12 ታላቅና ረጅም ቅጥር ነበራት አሥራ ሁለት ደጆች ነበሩአት በደጆቹም አሥራ ሁለት መላእክት ቆሙ የአሥራ ሁለቱም የእሥራኤል ልጆች ነገዶች ስሞች ተጽፈውባቸው ነበር።

13 በምሥራቅ ሦስት ደጆች በሰሜንም ሦስት ደጆች በደቡብም ሦስት ደጆች በምዕራብ ሦስት ደጆች ነበሩ።

14 ለከተማይቱም ቅጥር አሥራ ሁለት መሠረቶች ነበሩአት በእነርሱም ውስጥ የአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋሪያት ስሞች ተጽፈው ነበር።[152]

---

[149] **"ወደዚህ ና . . . አሳይሃለሁ"** ። የሙሽራዋ ታሪክ ልክ እንደ ጋለሞታዋ ባቢሎን ታሪክ ይጀምራል (ራዕይ 17፡1 ይመልከቱ)። በተመሳሳይ ቋንቋ በመጠቀም ዮሐንስ አንባቢዎቹን ሁለቱንም ከተሞች እንዲያወዳድሩ እና የትኛውን ከተማ መኖር እንደሚፈልጉ እና የየትኛውን ከተማ እንደመኖሪያቸው ማድረግ እንዳለባቸው እንዲወስኑ እንደሚፈልግ ግልጽ ነው።

እዚህ ላይ "ሙሽሪትዋ" በከተማ ተመስላ ተገልጻለች። ነገር ግን በራእይ 19፡7–8 ደግሞ ሙሽራይቱ የእግዚአብሔርን ሕዘብ የምትወክል ነች። ታዲያ ሙሽራይቱ ከተማ ናት ወይስ ሕዝብ? **ሙሽራይቱ ፍጹም በሆነ ሁኔታ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው።** የእግዚአብሔር ሕዝብ ደግሞ በራእይ 2 እና 3 እንደ ተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት ዓይነት አይደሉም። አሁን ነጭ ልብስ የለበሱ ናቸውና። እደዚሁም ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ ባቢሎን ሰይጣንንና አውሬውን የሚከተሉ የክፉ ሰዎች ምሳሌ እንደመሆኗ መጠን አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ክርስቶስን የሚከተሉ የጻድቃን ሰዎች ምሳሌ ናት። ቅዱሳንን የክርስቶስ ሙሽራ መሆናቸውን በተመለከተ ኤፌሶን 5፡22–23 ይመልከቱ)።

[150] ዮሐንስ ወደ "ታላቅና ረጅም ተራራ" መውሰዱ ምናልባት ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር የተያያዙ ቁልፍ የብሉይ ኪዳን ምንባቦችን አንባቢን ለማስታውስ ታስቦ ይሆናል። ለምሳሌ በዳናኤል 2 ላይ ተመዝግቦ በሚገኘው የናቡከደነፆር ራእይ ላይ አንድ ግዙፍ ምስል (የተለያዩ የምድር መንግሥታትን የሚወክል) ከተራራ ተፈንቅሎ በተወረወረ ድንጋይ ወድሟል። ምስሉ እንደ ደቀቀ ገለባ በነፋስ ተጠርጎ ተውስዷል (ይህም በመዝሙር 1፡4 ላይ የተጻፈውን አንባቢ እንዲያስታውስ ታስቦ ይመስላል)። በዚህ ጊዜ የአንባቢው ትኩረት በምስሉ ላይ አይደለም። ይልቁስ የአንባቢው ትኩረቱ የሚመሰጥው በድንጋዩ ላይ ነው፤ "ምስሉንም የመታው ድንጋይ ደግሞ ታላቅ ተራራ ሆነ ምድርንም ሁሉ ሞላ" (ዳናኤል 2፡35 ይመልከቱ)። ድንጋዩ ክርስቶስን የሚወክል ነው። ተራራው ክርስቶስን እና የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚወክል ይመስላል። ዮሐንስ በራእይ 21 ላይ ስለ "ታላቅና ረጅም ተራራ" መናገሩ በዳናኤል 2 ላይ የተገለጹት ክንውኖች መፈጸማቸውን ያሳያል! እግዚአብሔርን በመቃወም ጸንተው ሊቆሙ የሚችሉ ምድራዊ መንግሥታት የሉም። የእግዚአብሔር መንግሥት ብቸኛው ጽኑ መንግሥት ነው! በተጨማሪም ዘፃአት 15፡17፤ መዝሙር 48፡1፤ ኢሳይያስ 2፡2–3 ይመልከቱ።

[151] ራእይ 3፡12 ይመልከቱ።

[152] ቁጥር 12 የሚያመለክተው "አሥራ ሁለቱን የእሥራኤል ልጆች ነገድ ነው። ስማቸውንም በከተማይቱ በሮች ላይ ተጽፏል። ቁጥር 14 ደግሞ የሚያመለክተው "አሥራ ሁለቱን የበጉ ሐዋሪያት" ነው። ስማቸውንም በከተማይቱ ቅጥር ላይ ተጽፏል። እነዚህ 24 ስሞች የእግዚአብሔርን ሕዝብ አንድነት የሚያመለክቱ ናቸው። ሁለት የእግዚአብብሔር ሕዝብ የለም (ማለትም እሥራኤል ከብሉይ ኪዳን እና ደግሞ ቤተክርስቲያን ከሐዲስ ኪዳን)። አንድ የግዚአብሔር ሕዝብ ነው ያለው። ኤፌሶን 2፡11–22 ይመልከቱ።

15 የተናገረኝም ከተማይቱንና ደጆችዋን ቅጥርዋንም ይለካ ዘንድ የወርቅ ዘንግ ነበረው።[153]
16 ከተማይቱም አራት ማዕዘን ነበራት ርዝመትዋንም እንደ ስፋትዋ ልክ ነበረ። ከተማይቱንም በዘንግ
ለካት አሥራ ሁለት ሺህ ምዕራፍ ሆነች ርዝመትዋና ስፋትዋ ከፍታዋንም ትክክል ነው።[154]
17 ቅጥርዋንም ለካ መቶ አርባ አራት ክንድ በሰው ልክ እርሱም በመልአክ ልክ።[155]
18 ቅጥርዋም ከኢያስጲድ የተሠራ ነበረ ከተማይቱም ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረች።[156]
19 የከተማይቱም ቅጥር መሠረት በከበረ ድንጋይ ሁሉ ተጌጦ ነበር፤ ፊተኛውም መሠረት ኢያስጲድ
ሁለተኛው ሰንፔር ሦስተኛው ኬልቄዶን አራተኛው መረግድ፤
20 አምስተኛው ሰርዶንክስ ስድስተኛው ሰርድዮን ሰባተኛው ክርስቲሎቤ ስምንተኛው ቢረሌ ዘጠነኛው
ወራውሬ አሥረኛው ክርስጵራስስ አሥራ አንደኛው ያክንት አሥራ ሁለተኛው አሜቴስጢኖስ ነበረ።[157]
21 አሥራ ሁለቱም ደጆች አሥራ ሁለት ዕንቆች ነበሩ፤ እየአንዳንዱ ደጅ ከአንድ እንቁ የተሠራ ነበረ ።
የከተማይቱም አደባባይ ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረ።
22 ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስዋ ናቸውና መቅደስ በእርስዋ ዘንድ አላየሁም።[158]

---

153 መቅድሱ የተለካው በራእይ 11፡1–3 እና በሕዝቅኤል 40–48 ላይ ነው። በሁለቱ ምንባቦች ውስጥ የመቅደሱ መለካት ምሳሌያዊ ነበር። የአሁኑም ቢሆን ምሳሌያዊ ነው።

154 አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በዚህ ራእይ ውስጥ ፍጽም የሆነች ኪዩብ ናት። ይህ ምሳሌያዊ ቋንቋ ነው። በጥንታዊቱም ቤተ መቅደስ የነበረው ቅድስት ቅዱሳን ፍጹም ኪዩብ እንደነበረ ልብ ማለት ያስፈልጋል (1 ነገሥት 6፡20 ይመልከቱ)። አዲሲቱ ኢየሪሳሌም በጣም ትልቅ ቅድስተ ቅዱሳን ናት! ምድር ሁሉ እንደ ቅድስተ ቅዱሳን ሆናለችና! ሁለተኛው አዳም (ኢየሱስ) የፊተኛው አዳም ያላደረገውን አድርጓል። የእግዚአብሔርን መገኘት ወደ ምድር ሁሉ አምጥቷል! ዘፍጥረት 1፡26–28 ይመልከቱ።

155 የከተማዋም ግንቦች ግዙፍ ናቸው። ይህም የሚያስረዳው የከተማዋ ታላቅ ጥንካሬን ነው።

156 በጥንቱም ቤተ መቅደስ ውስጥ የነበረው ቅድስተ ቅዱሳን ንፁህ ወርቅ ነበር። ይህም ደግሞ ዳግመኛም ምድር ሁሉ እንደ ቅድስተ ቅዱሳን የመሆኑ እውነታ ምሳሌ ነው።

157 በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናቱ አሮን 12 ድንጋዮች ያለበት ልብስ ይለብስ ነበር። 12ቱ ድንጋዮች የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚወክሉ ነበሩ (ዘፃአት 28፡ 15–29 ይመልከቱ)። ይህም የእግዚአብሔር ሕዝብ ውድ ዋጋ ያለው መሆኑን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ደግሞም ምናልባት እነዚህ ድንጋዮች የተለያዩ መሆናቸው በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያለውን ልዩነት ሊያመለክት ይችላል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሕዝብ ከነገድና ከቋንቋ ሁሉ የመጣ ነውና። ከተለያየ አቅጣጫ የመጡ ቢሆኑም ቅሉ ግን ወድ ናቸው።

158 በግዚአብሔና በሰው መካከል ያለው የመሰብሰቢያ ቦታ ከእንግዲህ ወዲያ በሰው እጅ የተሰራ ሕንፃ አይሆንም። ይልቅስ ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት መገናኘት ይሆናልና! ደግሞም በዚህችም ከተማ የሚኖሩ ዜጎች እያንዳንዳቸው ካህናት ይሆናሉ!

23 ለከተማይቱም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት መብራትዋም በጉ ስለ ሆነ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጓትም ነበር።[159]

24 አሕዛብም በብርሃንዋ ይመላለሳሉ የምድርም ነገሥታት ክብራቸውን ወደ እርስዋ ያመጣሉ፤

25 በዚያም ሌሊት ስለሌለ[160] ደጆችዋ በቀን ከቶ አይዘጉም፤[161]

26 የአሕዛብንም ግርማና ክብር ወደ እርስዋ ያመጣሉ።[162]

27 ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም።[163]

---

159 እንደገና ይህ ምሳሌያዊ ቋንቋ ነው። ይህ ማለት ግን በአዲሲቷ ምድር ላይ ምንም ዓይነት ፀሐይ አይኖርም ማለት አይደለም። ደግሞም ይህ ማለት ዳግመኛ በፀሐይ መውጣት ወይም መጥለቅ አንደሰትም ማለትም አይደለም። ይልቅስ ብሩህነት ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይመጣል ማለት ነው። ራእይ 22፡5 ይመልከቱ። ደግሞም እንደ ኢሳይያስ 30፡26 ያሉትን ምንባቦች ፀሐይን በተመለከተ የሚናገረው ቋንቋ ምሳሌያዊ መሆኑን ያሳያሉ። በጉ ራሱ ደግሞ እንደ ፀሐይ ብርሃን ስለመሆኑ ራእይ 1፡16 ይመልከቱ።

160 በተጨማሪም ራእይ 22፡5 ይመልከቱ። ይህ ምሳሌያዊ ነው። በመንግስተ ሰማይ ውስጥ የፀሐይ መጥለቅ አይኖርም ማለት አይደለም። እንደዚሁም ዳግመኛ ሙሉ ጨረቃ አይኖርም ማለትም አይደለም። ጨለማ ከአደጋና ከወንጀል ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ክፍል ከዚህ በኋላ ክፉት ወይም አደጋ እንደማይኖር አንጽዖት የሚሰጥ ነው።

161 በጥንት ከተሞች ክፉ አድራጊዎች ወደ ከተማዋ እንዳይገቡ የከተማዋን በሮች በቀን ሊዘጉ ይችላሉ። እንደዚሁም ደግሞ በከተማው ውስጥ ያሉ ሰዎች ተኝተው ሳለ ክፉ ነገር ወደ ከተማዋ እንዳይገባ የከተማው በሮች በሌሊት ይዘጋሉ። በቀንም በሌሊትም በሮቹ መከፈታቸው ደግሞ ወደዚህች ከተማ ሊመጣ የሚችል ምንም ዓይነት ክፋት እንደማይኖር የሚያስረዳ ነው። ሁሉም ሁልጊዜ ደህና ይሆናሉ።

162 ይህም ደግሞ ምሳሌያዊ ነው። ማለት ሕዝቦች ራሳቸውን ክፍ ለማድረግ አይሞክሩም። ይልቁንም ሁሉንም ሰዎች ለእግዚአብሔር ስልጣን ይገዛሉና።

163 ይህ ሌላ የእግዚአብሔር ቸር ማስጠንቀቂያ ነው። አዲሲቱን ኢየሩሳሌም የሚያዩት በሕይወት መጽሐፍ ስማቸው የተጥጻፉትን ብቻ ናቸው። ፊልጵስዩስ 4፡4 እና ራእይ 20፡ 11–15 ይመልከቱ።

## ራእይ 22፡1–5

1 በአደባባይዋም መካከል ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀውን
የሕይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ።
2 በወንዙም ወዲያና ወዲህ በየውሩ እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ፤[164] የዛፉም
ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ።[165]
3 ከእንግዲህም ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም።[166] የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን በእርስዋ ውስጥ
ይሆናል፤ ባሪያዎቹም ያመልኩታል ፊቱንም ያያሉ።[167]
4 ስሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል።[168]

---

[164] ራእይ 22፡1–2 ላይ ሁለት ምልክቶች አሉ፤ **የሕይወት ውሃ ወንዝ** እና **የሕይወት ዛፍ**። እዚህ ላይ በግልጽ እንደ ሚታየው የኤደን ገነትን ለአንባቢው ለማስታውስ ይመስላል። በዘፍጥረት 2፡9 የሕይወት ዛፍ ከተጠቀሰ በኋላ ወዲያው ከዔደን የሚፈሰው ወንዝም መጠቀሱ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው (ዘፍጥረት 2፡10 ይመልከቱ)። አሁንም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በኤደን ገነት ውስጥ የታቀደው ፍጻሜ ናት! ወንዙና የሕይወት ዛፉም በመዝሙር 1 እና በሕዝቅኤል 47፡1–12 እንድገና አንድ ላይ ተጠቅሰዋል። እነዚህ ሁለቱም ምንባቦች ክርስቲያኖች በክርስቶስ ካላቸው ሕይወት እና ራእይ 22 እንደሚያስተምረን ከሚመጣው ዘመን ጋር የተቆራኙ በመሆናቸው በጥንቃቄ መጠናት አለባቸው። በዮሐንስ ራእይ 22 ላይ ስለ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም የተናገረው ቃል ከኢየሱስ ዳግም ምጽአት በኋላ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ቢሆንም በዮሐንስ 4፡7–15 እና 37–39 ላይ ኢየሱስ ከተናገረው ቃል መረዳት እንደሚቻለው አማኞች የሕይወትን ውሃ ቀድመው መካፈል ይችላሉ። በዮሐንስ 15፡1–11 ላይ ባለው የኢየሱስ ቃል እና በገላትያ 5፡22–23 ላይ ባለው የጳውሎስ ቃል መሰረት አማኞች የመጪውን ዘመን ፍሬ አሁኑኑ መቅመስ ችለዋል። ፍሬያማነት አስቀድሞ በአማኞች ሕይወት ውስጥ መታየት ጀመሯልና! ከእነዚህ ምስሎች ጋር የተያያዙ ሌሎች ምንባቦች በራእይ 22፡1–2፤ መዝሙር 46፡4፤ ኢዩኤል 3፡18፤ ዘካሪያስ 14፡8 እና ራእይ 2፡7 የመሳሰሉትን ያካትታል። እነዚህ ክፍሎች በጥንቃቄ መጠናት ይኖርባቸዋል።

[165] ሕዝቅኤል 47፡12 ይመለከቱ።

[166] ዘፍጥረት 3፡17 እና ሮሜ 8፡18–25 ይመልከቱ።

[167] በዘፀአት 33፡20 ላይ እግዚአብሔር ሙሴን “. . . ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም” ብሎት ነበር። በዘዳግም 18 ላይ ደግሞ ሙሴ “አምላክህ እግዚአብሔር እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሳልሃል” ብሎ ነበር። እግዚአብሔር ፊት ለፊት ማየት የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው! ነገር ግን በመጨረሻው ዘመን እኛ ራሳችን ፊት ለፊት ስለምናውቀው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ምንም ነገር አይኖርም። በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ልዩነት ይወገዳልና! ዮሐንስ 1፡18 ይመልከቱ።

[168] ራእይ 3፡12 እና 14፡1 ይመልከቱ።

5 ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይሆንም፤[169] ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና
የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤[170] ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ።[171]

---

[169] ይህም ምሳሌያዊ አባባል ነው። ይህ ማለት ቅዱሳን ዳግመኛ ውብ በሆነችው ጀምበር ስትጠልቅ አይደሰቱም ወይም ጨረቃ በውሃ ላይ ሲያንጸባርቅ አያዩም ማለት አይደለም። አንባቢ ማስታውስ ያለበት፤ በዚህ እኛ ባለንበት ዘመን ሌሊት ብዙ ጊዜ ከኃጢአት እና ከአደጋ ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው። ለምሳሌ ይህ የሌሊት ጊዜ ሌቦች እንኳን የሰው ቤት ሰብረው የሚገቡበት ጊዜ ነው። ጨለማ ከወንጀል ጋር የተያያዘ ነውና። ስለዚህ ሌላ ሌሊት የለም ማለት የትም ሌላ አደጋ አይኖርም ማለት ሊሆን ይችላል።

[170] ይህም እንደገና ምሳሌያዊ ቋንቋ ነው። ለምሳሌ ያህል ሞቅ ባለውና በሚንበለበለው የሻማው ብርሃን ዳግመኛ አይድሰቱም እንደ ማለት አይደለም። ይልቅስ ይህ የእግዚአብሔር መገኘት በሁሉም ሥፍራ እንደሚሆን የሚያሳይ ምሳሌ ነው።

[171] ዳንኤል 7፡27 ይመልከቱ። ያስታውሉ፤ ዋናው ትኩረት በክርስቶስ መግዛት ላይ አይደለም። ይልቅስ በነገሡት ቅዱሳን ላይ ነው እንጂ። የዮሐናስ ጥብቁ መልዕክት ሰዎች ስለራሳቸው እጣ ፋንታ አጥበቀው እንዲያስቡ ማድረግ ነው። ከክርስቶስ ጋር ይነግሣሉ ወይስ በእሳት ባሕር ውስጥ ይጣላሉ?

ማስታወሻ

ማስታወሻ

ማስታወሻ

# ሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ አገልግሎት

Hands To ThePlow.org

ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

መርጃዎች ከሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ አገልግሎት

Hands To ThePlow.org

እነዚህ መጣጥፎችንም ያካትታሉ . . .

- **የሰባኪ መመሪያ**

  **መዝሙረ ዳዊት (መዝሙር 1–19)**
- **የሰባኪ መመሪያ**

  **የማርቆስ ወንጌል**
- **የሰባኪ መመሪያ**

  **የ 1ኛ ጴጥሮስ መልዕክት**
- **የሰባኪ መመሪያ**

  **የራእይ መጽሐፍ**

የቅጂ መብት 2017 ሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ
Copyright© 2017 by Hands to the Plow, Inc.